# እንቅልፍ፣ ለምኔ።

ከባላምባራስ፡ ማኅተመ፡ ሥላሴ፡ ወ፡ መ፤
ተዘጋጀ

አዲስ፡ አበባ፡ ሐምሌ፡ ፲፯ ቀን፡ ፲፱፻፶፰ ዓ.ም፡

ያለደራሲው ፡ፈቃድ ፡መልሶ ፡ማተም፡
ክልክል ነው።

**All Right reserved**

ግንቦት ፲፱፻፺፰ ዓ.ም እንደገና ታተመ።

አሳታሚዎች፡- እነ ወ/ሮ ጌጤነሽ ማኅተመ ሥላሴ
ዋና አከፋፋይ፡- ዓይናለም መጽሐፍት መደብር
አድራሻ፡- ከብሔራዊ ቴአትር ጀርባ
ስልክ 011 550 58 45
ሞባይል 0911 62 49 10

## ማውጫ ፡

ገጽ ፡

| | |
|---|---|
| መግቢያ ፡ ... ... ... ... ... ... ... | 5 |
| ስንዝሮ ፡ ... ... ... ... ... ... ... | 9 |
| ስለ ፡ አንዲት ፡ የቆቅ ፡ ልጅ ፡ በወጥመድ ፡ መያዝ ፡ ... ... | 18 |
| ስለ ፡ አንድ ፡ አባት ፡ ኑዛዜ ፡ ... ... ... ... ... | 19 |
| አንድ ፡ መነኩሴና ፡ ነብር ፡ ... ... ... ... ... | 25 |
| ስለ ፡ አንዲት ፡ ገበያተኛ ፡ ሴት ፡ ... ... ... ... | 27 |
| የሰው ፡ ገንዘብ ፡ የወሰዱና ፡ ሰው ፡ በግፍ ፡ የገደሉ ፡ ወንበዴዎች ፡ . | 30 |
| ያንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ምርቃት ፡ ... ... ... ... ... | 33 |
| ያንድ ፡ ኸርብ ፡ ሞት ፡ ... ... ... .. ... | 36 |
| ወታደርና ፡ ተማሪ ፡ ... ... ... ... ... ... | 38 |
| ባልና ፡ ሚስትን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንዳታለላቸው ፡ ... ... | 40 |
| የኸርብ ፡ ልጅ ፡ ሞት ፡ ... ... ... ... ... ... | 43 |
| ሚስቱ ፡ የጐሽ ፡ ወተት ፡ አምጣ ፡ ስላለችው ፡ ሰው ፡ ... ... | 45 |
| ሁለት ፡ ሌቦች ፡ .. ... ... ... ... ... | 48 |
| አንድ ፡ በሬ ፡ ስለ ፡ ነበራቸው ፡ ቂሎች ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ... ... | 50 |
| አንድ ፡ ሚስቱ ፡ የተጫወተችበት ፡ ሰው ፡ ... ... ... | 53 |
| የባልና ፡ ሚስት ፡ በተስቦ ፡ መታመም ፡ ... ... ... | 56 |
| ያንድ ፡ ድኻ ፡ ሰው ፡ ኑዛዜ ፡ ... ... ... ... ... | 58 |
| ሦስት ፡ ቂል ፡ ወንድማማቾች ፡ ... ... ... ... | 62 |
| የእሳትና ፡ ውሃ ፡ በሬ ፡ መግዛት ፡ ... ... .. ... | 63 |
| የዝንጀሮ ፡ ገደል ፡ መግባት ፡ ... ... ... .. ... | 64 |
| ድኻ ፡ ጥጃ ፡ ... .. ... ... ... ... ... | 66 |
| አንበሳና ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ... ... ... ... ... | 72 |
| የዶሮ ፡ ዘመቻ ፡ .. ... ... ... ... ... ... | 74 |

ያውሬ ፡ ሁሉ ፡ ገበያ ፡ ... ... ... ... ... ... 76
የኸብና ፡ የነብር ፡ ንስሐ ፡ አባት ፡ መያዝ ፡ ... ... ... 80
አንዲት ፡ ባሏን ፡ የናቀች ፡ ሴት ፡ ... ... ... ... ... 86
አንበሳና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ... ... ... ... ... 88
የሦስት ፡ ሌቦች ፡ ምክር ፡ ... ... ... ... ... 91
ሴቶች ፡ ሹመት ፡ እንደ ፡ ለመኑ ፡ ... ... ... ... 95
በነውር ፡ የተሰደዱ ፡ ሦስት ፡ ጓደኞች ፡ ... ... ... ... 96
የኸብና ፡ የዝንጀሮ ፡ መጣላት ፡ ... ... ... ... ... 102
የአራዊት ፡ ለአንበሳ ፡ሎሌነት ፡ ማደር ፡ ... ... ... 105
ስለ ፡ አንዲት ፡ የጌታ ፡ ልጅ ፡ መሰነስ ፡ ... ... ... ... 114
ስለ ፡ አንድ ፡ ታማኝ ፡ አሽከር ፡ ... ... ... ... ... 117
ሁለት ፡ አታላዮች ፡ ... ... ... ... ... ... 122
ስለ ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ምርቃት ፡ ... ... ... ... 128
ስለ ፡ ዘጠኝ ፡ ቂሎች ፡ ወንድማማቾች ፡ ... ... ... ... 131
ስለ ፡ ሦስት ፡ ሴቶች ፡ ... ... ... ... ... ... 133
እግዜር ፡ ሞትና ፡ ክረምት ፡ ማደሪያ ፡ እንደ ፡ ለመኑ ፡ ... ... 138
ስለ ፡ አንድ ፡ መሀይምን ፡ መነኰሴ ፡ ጸሎት ፡ ... ... ... 140
የመልከም ፡ ሥራ ፡ ዋጋ ፡ ... ... ... ... ... 142
ስለ ፡ አንድ ፡ መንገድ ፡ የሄደ ፡ ሰው ፡ ... ... ... ... 145
ስለ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ መተነኳኰል ፡ ... ... ... ... 146
ስለ ፡ ሁለት ፡ ቂሎች ፡ ልጅ ፡ መውለድ ፡ ... ... ... 151
የሚስት ፡ ዐይነቷ ፡ ሦስት ፡ ነው ፡ ... ... ... ... 156
ወላድ ፡ እንደ ፡ ተመከችና ፡ መክንን ፡ እንደ ፡ ናቀች ፡ ... ... 161
ስለ ፡ አንድ ፡ ንጉሥ ፡ የዘመን ፡ ሁናቴ ፡ መጠየቅ ፡ ... ... 164
ስለ ፡ አንዲት ፡ ልጃገረድ ፡ መታጨት ፡ ... ... ... ... 170
የሁለት ፡ ድመቶች ፡ ፍቅርና ፡ ጠብ ፡ ... .. ... .. 171
ስለ ፡ ሁለት ፡ ጓደኞች ፡ ... ... ... ... ... 174
አንድ ፡ አሮጌ ፡ ውሻና ፡ ቀበሮ ፡ .. .. .. ... 175
ክብር ፡ ለማግኘት ፡ አስቦ ፡ አደን ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ ሰው ፡ ... .. 177
በጎረ ፡ ቤት ፡ ያለውን ፡ ሌባ ፡ ያሸነፈ ፡ ዐይነ ፡ ስውር ፡ ... .. 178
ሕመምተኛ ፡ ሰውና ፡ ሚስቱ ፡ ... ... ... ... ... 180
አንድ ፡ ቀላዋጭ ፡ ሰው ፡ ... ... ... ... ... 182
የታማኝ ፡ ወዳጆች ፡ መከዳዳት ፡ ... ... ... ... 184
ስለ ፡ ሦስት ፡ ደንቆሮዎች ፡ ... ... ... ... ... 186
ሲሰማ ፡ የገባን ፡ ሲያይ ፡ ቀበረው ፡ ... ... ... ... 189
ያንድ ፡ ተማሪ ፡ በብልኅት ፡ ዳቦ ፡ ማግኘት ፡ ... ... ... 192
አራዊትን ፡ በጓደኝነት ፡ ስላስከተለ ፡ ሰው ፡ ... ... ... 195
ስለ ፡ አንድ ፡ አንበሳና ፡ ዝንጀሮ ፡ ... ... ... ... 200
ስለ ፡ አንድ ፡ ሰውና ፡ አንበሳ ፡ ... ... ... ... 203
ጠበል ፡ የሄዱች ፡ ፍየል ፡ ... ... ... ... ... 206
ስለ ፡ አንድ ፡ ተንኰለኛ ፡ ሰውና ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ገበሬ ፡ ጓደኝነት ፡ ... 209
በወፍ ፡ ፍቅር ፡ የሞተ ፡ እረኛ ፡ ... ... ... ... ... 213

# መግቢያ ።

ያንድ ፡ አገር ፡ ታሪክ ፡ የሚታወቀው ፡ በሕንጻዎቹና ፡ በሐውልቶቹ ፡ በጽሑፎቹና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የኪነ ፡ ጥበብ ፡ ሥራዎቹ ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ በመሳሰሉት ፡ መሆኑ ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ በጽሑፍም ፡ በይሆን ፡ ከባት ፡ ለልጅ ፡ ሲወራረሱ ፡ የመጡት ፡ በምሳሌ ፡ እንደ ፡ ወግ ፡ ልማድ ፡ እድር ፡ ባህል ፡ እንደነዚህም ፡ ያሉት ፡ ሁሉ ፡ ሲመረመሩ ፡ ያንድን ፡ አገር ፡ ታሪክና ፡ ሥልጣኔ ፡ ለመግለጥ ፡ ምክንያት ፡ ከሚሆኑት ፡ ከሐውልቶችና ፡ ከእጅ ፡ ብልኀት ፡ ሥራዎች ፡ ጋራ ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ሆነው ፡ የሚገመቱ ፡ አስረጂዎች ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ።

ታሪክ ፡ እንደሚነግረን ፡ አገራችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ በቀደምትነት ፡ ከሚታወቁት ፡ አገሮች ፡ አንዷ ፡ ናት ። በመንግሥትነትም ፡ መታወቅ ፡ የጀመረችበት ፡ ዘመን ፡ ሲቈጠር ፡ ከጌታ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፲፻፰ ፡ ዓመት ፡ ታመጣለች ። የነገሥታቱም ፡ ቍጥር ፡ ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ እስከ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ፪፻፳፯ ፡ ሆኗል ። ይኸውም ፡ ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ በፊት ፡ ያለው ፡ ቀርቶ ፡ ነው ።

ኢትዮጵያም ፡ ገና ፡ ስትወጠን ፡ ዠምሩ ፡ ትውልዷንና ፡ ግዛቷን ፡ ለማስፋፋት ፡ የአእምሮና ፡ የዕውቀት ፡ መንፈሷን ፡ ለማደርጀት ፡ የቦዘነችበት ፡ ጊዜ ፡ እንዳልነበረ ፡ በየመጻሕፍቱ ፡ ተነግሯል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በየዘመኑ ፡ ከውስጥም ፡ ሆነ ፡ ከውጭ ፡ በሚደርስባት ፡ ሁከት ፡ (ጦርነት) ፡ ምክንያት ፡ እንዳሰበችውና ፡ እንደ ፡ ተመኘችው ፡ ሥልጣኔና ፡ ኀይል ፡ ልታገኝ ፡ አልቻለችም ፡ ነበር ።

እንዲህም ፡ ስለ ፡ ተባለ ፡ የሽማግሎቿና ፡ ያዋቆቿ ፡ የመንፈስ ፡ ብርታት ፡ ጋሻና ፡ መከታ ፡ ሆኗት ፡ ሥልጣኔዋ ፡ ፈጽሞ ፡ ሳይደመሰስ ፡ ካባት ፡ ለልጅ ፡ እየተላለፈ ፡ እስካለንበት ፡ ጊዜ ፡ ሊደርስ ፡ ችሏል ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ እንደ ፡ ዘመኑ ፡ ብዛትና ፡ እንዳገሪቱም ፡ ጥንታዊትነት ፡ መጠን ፡ ለሥልጣኔዋ ፡ ማስረጃ ፡ የሚሆኑት ፡ ሐውልቶችና ፡ ሕንጻዎች ፡ በብዛት ፡ ባይገኙ ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ እስከ ፡ ዛሬው ፡ ትውልድ ፡ የደረሰው ፡ የአእምሮ ፡ እድገት ፡ ሲመረመር ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ የበሰለ ፡ አስተያየት ፡ ያላቸው ፡ ሽማግሎችና ፡ ዐዋቆች ፡ እንደ ፡ ነበሯት ፡ አሁንም ፡ እንዳሏት ፡ ያስ

ረዳል። ሕዝቡም ፡ አስተዋይነትና ፡ አመዛዛኝነት ፡ ከተፈጥሮው ፡ የታደለ ፡ ስለሆን ፡ የተማረው ፡ ቀርቶ ፡ ንባብና ፡ ጽሕፈት ፡ እንኳ ፡ የማያውቀው ፡ ባስተዳደርና ፡ በዳኝነትም ፡ ላይ ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ትችቶችና ፡ አስተያየቶች ፡ እንዲሁም ፡ ደስታውንም ፡ ሆነ ፡ ሐዘኑን ፡ የሚገልጥባቸው ፡ ያማርኛዎቹ ፡ ዐርቀቅና ፡ ጥልቅ ፡ መሆን ፡ በእውነቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ያዋቂነት ፡ ግምት ፡ የሚያሰጠው ፡ ነው ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ለተመለከተውና ፡ አርቆም ፡ ላስተዋለው ፡ አላፊውን ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ፎቶግራፍ ፡ ወይም ፡ መስተዋት ፡ ገልጦና ፡ አጣርቶ ፡ ያባቶቻችንን ፡ ችሎታና ፡ ዝና ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ።

ብዙ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ኢትዮጵያን ፡ እየተዘዋወሩ ፡ በመጐብኘት ፡ በየጊዜው ፡ የመሰላቸውን ፡ ጽፈዋል ፤ ይኸውም ፡ በዐይን ፡ የሚታየውን ፡ ይህም ፡ ባይሆን ፡ በቋንቋ ፡ ችግር ፡ ምክንያት ፡ ሁኔታውን ፡ ጠንቅቆ ፡ ለመረዳት ፡ በማያስችል ፡ ባስተርጓሚ ፡ እርዳታ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ትክክለኛውንና ፡ እውነተኛውን ፡ ጽፈዋል ፡ ለማለት ፡ እምብዛም ፡ አያስደፍርም ።

በእውነትም ፡ ቅኔዎቻችንን ፡ አማርኛ ፡ አነጋገራችንን ፡ ምሳሌዎቻችንን ፡ (ተረቶችን) ፡ ለመረዳትና ፡ ለማስረዳት ፡ ግእዝንም ፡ ሆነ ፡ አማርኛን ፡ አጣርቶ ፡ ማወቅ ፡ ያስፈልጋል ። ያለዚያ ፡ ከነወዙ ፤ ከነለዛው ፤ ከነጣዕሙ ፡ ለመተርጐም ፡ ይቅርና ፡ ለመረዳት ፡ እንኳ ፡ አስቸጋሪ ፡ እንደሚሆን ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

ስለዚህም ፡ እኛ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አገራችን ፡ ጥንታዊት ፡ መሆኗን ፡ ሥልጣኔንም ፡ በመሻት ፡ ዐዋቆችና ፡ አስተዋዮች ፡ አባቶቻችን ፡ በብዙ ፡ የደከሙ ፡ መሆናቸውን ፡ በመገንዘብ ፡ ላገራችን ፡ ወጣቶችም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ እውነተኛውንና ፡ ምስክርም ፡ ሊሆን ፡ የሚገባውን ፡ ሁሉ ፡ እየሰበሰብን ፡ ማዘጋጀት ፤ ለመጭውም ፡ ትውልድ ፡ እንዲተላለፍ ፡ ማድረግ ፡ አለብን ።

ከዚህ ፡ በፊት ፡ ይህንኑ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ እኔ ፡ በበኩሌ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የሥልጣኔ ፡ ሥራዎች ፡ ለመግለጥ ፡ ስል ፡ «ዝክረ ፡ ነገር» ፡ «ያበቶች ፡ ቅርስ» ፡ «አማርኛ ፡ ቅኔ» ፡ የተባሉ ፡ መጻሕፍት ፡ አዘጋጅቼ ፡ ስለታተሙ ፡ ይኸው ፡ ዛሬ ፡ በትምህርት ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ የሚገኙትና ፡ ሌሎችም ፡ ያገራችንን ፡ ታሪክ ፡ ለመረዳት ፡ የሚሹ ፡ ሁሉ ፡ ሲያነቧቸውና ፡ ሲጠቀሙባቸው ፡ ይታያል ።



አሁን ፡ ደግሞ ፡ በዚህ ፡ «እንቅልፍ ፡ ለምኔ» ፡ ተብሎ ፡ በተሰየመው ፡ መጽሐፍ ፡ አባቶቻችን ፡ በጠለቀ ፡ አስተያየታቸው ፡ ሕፃናቱ ፡ ሰይሰለቹ ፡ በመደሰት ፡ የግብረ ፡ ገብነትና ፡ የመመራመር ፡ (ፌሎዞፊ) ፡ ትምህርት ፡ ገና ፡ ከልጅነታቸው ፡ ዠምሮ ፡ እንዲዋሐዳቸው ፡ ለማድረግ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ፈሊጥ ፡ ያደራጁዋቸውን ፡ ተረቶች ፡ ወይም ፡ ምሳሌዎች ፡ ሰብስቤ ፡ አቅርቢያለሁ ።

ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ምንም ፡ እንደ ፡ ቧልት ፡ አነጋገር ፡ ቢጻፍ ፡ መነሻና ፡ መድረሻ ፡ ያለው ፡ አንዳንድ ፡ ሙሉ ፡ ታሪክ ፡ የያዘ ፡ ነው ። ሕፃናቱም ፡ ሳይሰለቹ ፡ ማንበብ ፡ እንዲደፍሩ ፡ ከግቡም ፡ ሳይደርሱ ፡ እንዳያርፉ ፡ በማሰብ ፡ የተቻለኝን ፡ ያኽል ፡ ባቀራረቡ ፡ ላይ ፡ ደክሜበታለሁ ።

ያገራችን ፡ ሽማግሎችና ፡ ባልቴቶች ፡ ለሕፃናት ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ አስደሳች ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ እንቆቅልሽ ፡ ተረት ፡ ያሉትን ፡ ማውጋት ፡ ልማዳቸው ፡ ነው ፤ ስለዚህም ፡ የያንዳንዱን ፡ ታሪክ ፡ ከሥር ፡ ዠምረው ፡ በፈገግታና ፡ ደስ ፡ በሚያሰኝ ፡ አነጋገር ፡ ሲተርኩ ፡ ይታያሉ ።

ሕፃናቱም ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ መንፈሳቸውን ፡ የሚያስደስትና ፡ አእምሯቸውን ፡ የሚቀሰቅስ ፡ ነገር ፡ ስለሚያገኙበት ፡ ከሌላው ፡ ጨዋታ ፡ ይልቅ ፡ ሽማግሎቹን ፡ ከበው ፡ እንደ ፡ ማርና ፡ ወተት ፡ የጣፈጠ ፡ ምክራቸውን ፡ ለመቀበልና ፡ ለመስማት ፡ የተዘጋጁ ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ። የሰሙትንም ፡ በሙሉ ፡ ልባቸው ፡ ስለሚቀበሉት ፡ በጠየቋቸው ፡ ጊዜ ፡ ያላንድ ፡ ችግር ፡ ያዳመጡትን ፡ ከዳር ፡ እዳር ፡ ይወጡታል ።

እኔም ፡ ምንም ፡ ከዛሬ ፡ ፵፰ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የሰማሁት ፡ ቢሆን ፡ ይኸው ፡ ዛሬ ፡ አንዳንዱን ፡ ከሞላ ፡ ጐደሉን ፡ ለማስታወስና ፡ ለመጻፍ ፡ ችያለሁ ። ይህነንም ፡ መጽሐፍ ፡ እንቅልፍ ፡ ለምኔ ፡ ብዬ ፡ ሰይሜዋለሁ ። እንዲህም ፡ ለማለት ፡ ያሳሰበኝ ፡ ሕፃናቱ ፡ ወይም ፡ ወጣቶቹ ፡ ከጨዋታ ፡ መርጠው ፡ ከእኽልና ፡ ከውሃም ፡ አብልጠው ፡ እንቅልፍ ፡ ሳያምራቸው ፡ ለመኝታም ፡ ሳይጓጉ ፡ ተረት ፡ ለመስማት ፡ ያላቸውን ፡ ፍላጎት ፡ በመመልከት ፡ ነው ።

መጽሐፉንም ፡ ሳዘጋጅ ፡ የተቻለኝን ፡ ያኽል ፡ ሐሳቡ ፡ የተያያዘ ፡ ማሰሪያም ፡ ያለው ፡ እንዲሆን ፡ ተጣጥሬያለሁ ።

ከዚህም ፡ ሌላ ፡ የሕፃናቱን ፡ መንፈስ ፡ ለመሳብና ፡ ለመሰብሰብ ፡ መጽሐፉ ፡ የሚያሰለች ፡ እንዳይሆን ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ በታየኝ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ለታሪኩ ፡ ተስማሚ ፡ የሆኑትን ፡ ሥዕሎች ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ አግብቻለሁ ።

በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ወጣቶቹ ፡ ጽሑፉ ፡ በእጃቸው ፡ ሲገባ ፡ የያንዳንዱን ፡ ሥዕል ፡ ታሪክ ፡ ለመረዳት ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ ካላነበቡትና ፡ ካልተገነዘቡት ፡ መንፈሳቸው ፡ እንደማያርፍ ፡ አምናለሁ ።

ይህም ፡ ሲሆን ፡ መጽሐፉን ፡ ለማንበብ ፡ ስለማይበዝኑ ፡ ንባብ ፡ ከመማራቸውም ፡ በላይ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ በማስተዋል ፡ ለመረዳት ፡ ቻሉ ፡ ማለት ፡ ነው ።

በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ተረቶች ፡ ቍጥራቸው አነስተኛ ፡ ቢሆንም ፡ በገራችን ፡ ይህን ፡ የመሰለው ፡ ታሪክና ፡ ምሳሌ ፡ በብዛት ፡ ስለሚገኝ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚያዘጋጁት ፡ ሰዎች ፡ የጐደለውን ፡ በመሰብሰብ ፡ የተሟላ ፡ እንደሚያደርጉት ፡ አምኃለሁ ።

በዚህ ፡ ዐይነት ፡ መንፈስ ፡ ተመርተው ፡ ከሁን ፡ በፊት ፡ ያቦቶቻችንን ፡ ዝና ፡ የሚያስነሣ ፡ አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ለጻፉ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ምስጋና ፡ ሳላደርግላቸው ፡ አላልፍም ። ምንም ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ቍጥራቸው ፡ የበዛ ፡ ዐይነታቸው ፡ የተለያየ ፡ ምስጢራቸው ፡ የዘለቀና ፡ የጠለቀ ፡ ተረቶች ፡ ከታላላቅ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ሊቆችና ፡ ዐዋቆች ፡ የተደረሱ ፡ መኖራቸውን ፡ ባውቅ ፡ ይህንን ፡ መጽሐፍ ፡ በማዘጋጀቴ ፡ የሚሰማኝን ፡ ደስታ ፡ ከፍ ፡ አድርጌ ፡ የምመለከተው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የሆነውን ፡ ያቦቶች ፡ ተረት ፡ ሰብስቤ ፡ ለዛሬዎቹ ፡ ሕፃናት ፡ ለነገዎቹ ፡ ወጣቶች ፡ ማስታወሻ ፡ እንዲሆናቸው ፡ በማበርከቴ ፡ ነው ።

ክቡር ፡ የትምህርትና ፡ ሥነ ፡ ጥበብ ፡ ሚኒስቴርም ፡ ጠቃሚነቱን ፡ በመረዳት ፡ መጽሐፉ ፡ በቶሎ ፡ ታትሞ ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ በማድረጉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋና ፡ አቀርብለታለሁ ።

ባላምባራስ ፡ ማኅተመ ፡ ሥላሴ ፡ ወልደ ፡ መስቀል ።



# ስንዝሮ ።

አንዲት ፡ ድኻ ፡ ሴት ፡ ስድስት ፡ ወንድ ፡ ልጆች ፡ ወልዳ ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ እየለመነችና ፡ የሞያተኛ ፡ እየሠራች ፡ በምታገኘው ፡ ገንዘብ ፡ አሳደገቻቸው ። እነሱ ፡ ግን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ የሌላቸውና ፡ ሀኬት ፡ የበዛባቸው ፡ ሆኑ ። አድገውም ፡ ለሥራ ፡ ስለ ፡ ደረሱ ፡ አርሰውና ፡ ቈፍረው ፡ ከችግር ፡ ያድኑኛል ፡ በማለት ፡ በእርሻ ፡ ሰዓት ፡ ሰው ፡ ሲዘራ ፡ አይታ ፡ እሷም ፡ ስንዴ ፡ ባቄላ ፡ ዐተርና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የእኽል ፡ ዐይነት ፡ ከባለጸጋ ፡ ተበድራ ፡ አምጥታ «በሉ ፡ እናንተም ፡ እንደ ፡ ሰዎቹ ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ እረሱና ፡ ዝሩ» ብላ ፡ ዘሩን ፡ ሰጠቻቸው ። እነሱ ፡ ግን ፡ የተቀበሉትን ፡ እኽል ፡ እየቈሉ ፡ ይበሉና ፡ የማታ ፡ ማታ ፡ እግራቸውን ፡ ጭቃ ፡ ቀብተው ፡ እምዬ ፡ ቍፋሮው ፡ ገደለን ፡ አገር ፡ ምድሩን ፡ ዘርተነው ፡ ዋልን ፡ እያሉ ፡ ለናታቸው ፡ ሐሰት ፡ ወሬ ፡ ይነግሯታል ።

እሷም ፡ ሳትጠራጠር ፡ እውነት ፡ በሥራ ፡ የዋሉ ፡ እየመሰላት ፡ ልጆቼ ፡ ተጐዱብኝ ፡ በማለት ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ለእግራቸው ፡ ውሃ ፡ በኰስኰስት ፡ አሙቃ ፡ እንዲታጠቡ ፡ ትሰጣቸዋለች ። የሚተኙበትንም ፡ ቈጥ ፡ እሷው ፡ ራሷ ፡ ታነጥፍላቸዋለች ።

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ሲያታልሏት ፡ ከቈዩ ፡ በኋላ ፡ የዘሩ ፡ ወቅት ፡ አልፎ ፡ የሸት ፡ ወራት ፡ ሲደርስ ፡ የየሰዎቹ ፡ ልጆች ፡ ለወላጆቻቸው ፡ እሸት ፡ ሲያመጡላቸው ፡ አይታ ፡ እኔም ፡ አምሮኛል ፡ ምነው ፡ ከእርሻችሁ ፡ ብታመጡልኝ ፡ ስትል ፡ ጠየቀቻቸው ። ተንኰለኞቹ ፡ ልጆቿም ፡ እቤት ፡ ድረስ ፡ ያላመጣንልሽ ፡ ዐይንሽ ፡ ያየውን ፡ መርጠሽ ፡ እንድትበይ ፡ በማለት ፡ ነው ። እርሻችንም ፡ ያውልሽ ፡ እዚያ ፡ ማዶ ፡ ከላይ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ የሚታየው ፡ በሙሉ ፡ የኛው ፡ ነው ። ማንም ፡ ከልካይ ፡ የለብሽም ፡ ሂደሽ ፡ እንደ ፡ ልብሽ ፡ የፈለግሽውን ፡ ዐይነት ፡ እሸት ፡ ቀጥፈሽ ፡ መብላት ፡ ትቺያለሽ ፡ ሲሉ ፡ ያንዱን ፡ ሀብታም ፡ ገበሬ ፡ ሰብል ፡ አሳዩዋት ። እናታቸውም ፡ የልጆቿን ፡ ጕልበት ፡ እያመሰገነች ፡ ወደ ፡ አመለከቷት ፡ ዝሪት ፡ ሄደችና ፡ ከባለጸጋው ፡ ሰብል ፡ መካከል ፡ አንፈራጣ ፡ ተቀምጣ ፡ እየቀጠፈችና ፡ እየዘነበጠች ፡ ትበላ ፡ ዠመር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የእኽሉ ፡ ባለቤት ፡ ሽመሉን ፡ መዞ ፡ ሲሮጥ ፡ መጥቶ ፡ ማን ፡ ፈቀደልሽና ፡ ነው ፡ ከዚህ ፡ የገባሽው ፡ በይ ፡ አሁን ፡ አትወጭም ፡ ሲል ፡ ጠየቃት ። እሷም ፡ የት ፡ ነው ፡ የምወጣው ፡ በልጆቼ ፡ አዝመራ ፡ ዐይንህ ፡ ይውጣና ፡ አትሄድም ፡ ስትል ፡ በልበ ፡ ሙሉነት ፡ ተሳድባ ፡ መለሰችለት ።

እሱም ፡ ያለርኅራኄ ፡ በያዘው ፡ ሽመል ፡ እየጨረገደ ፡ ከእኽሉ ፡ ውስጥ ፡ አስወጥቶ ፡ አባረራት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከልጆቿ ፡ ቀጣፊነት ፡ የተነሣ ፡ በመደብደቧ ፡ እጅግ ፡ አዝና ፡ ወደ ፡ ፈጣሪዋ ፡ አንጋጣ ፡ ጌታዬ ፡ መልክ ፡ ወይም ፡ ቁመት ፡ አልልህም ፤ በቁም ፡ ነገር ፡ ከነዚህ ፡ የተሻለ ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ የሚያኽል ፡ ብልኅ ፡ ልጅ ፡ ስጠኝ ፡ ስትል ፡ በቁመቷ ፡ ሙሉ ፡ እንባዋን ፡ እያወረደች ፡ ብዕፀት ፡ አደረገች ።

እግዚአብሔርም ፡ የለመነችን ፡ የማይነሣ ፡ የነገሩትን ፡ የማይረሳ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ምኞቷ ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ የሚያኽል ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ሰጣት ። ለልጁም ፡ በቁመቱ ፡ ማጠር ፡ ምክንያት «ስንዝሮ» የሚባል ፡ ስም ፡ ወጥቶለት ፡ በዚሁ ፡ እየተጠራ ፡ አድጎ ፡ እናቱን ፡ በሥራ ፡ ለማገልገል ፡ ደረሰ ። ቅን ፡ አገልጋይ ፡ በመሆኑና ፡ ወላጅቱን ፡ በማስደሰቱ ፡ እየተወደደ ፡ ስለ ፡ ኼደ ፡ ወንድሞቹ ፡ ቀንተው ፡ ለመግደል ፡ ይመክሩበት ገመር ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እነዚሁ ፡ ስድስቱ ፡ አጕራማ ፡ ወንድሞቹ ፡ ከብት ፡ እንስረቅ ፡ እንስረቅ ፡ ተባብለው ፡ ወደ አንዱ ፡ አገር ፡ ኼዱ ። ስንዝሮም ፡ እየተሸሸገ ፡ ሳያዩት ፡ እሥር ፡ እሥራቸው ፡ እያለ ፡ ተከተላቸው ። ለመስረቅ ፡ ካሰቡበትም ፡ ቦታ ፡ ቢደርሱ ፡ አጥሩ ፡ የጠበቀ ፡ መዝጊያው ፡ በተዋጋ ፡ የጠነከረ ፡ ኖሮ ፡ ለመግባት ፡ ባለመቻላቸው ፡ ዋይ ፡ ነዶ ፡ ዛሬ ፡ ስንዝሮ ፡ መጥቶ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ይጠቅመን ፡ ነበር ፡ ሲባባሉ ፡ ሰማ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አለሁ ፡ እኔ ፡ ወንድማችሁ ፡ ሲል ፡ ከሥራቸው ፡ ብቅ ፡ አለ ። እነሱም ፡ በመኖሩ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ በል ፡ ግባና ፡ ከብቶቹን ፡ አስወጥተህ ፡ አምጣ ፡ ሲሉ ፡ አዘዙት ። ትንሹም ፡ ሰው ፡ በወንዳ ፡ ወንዴው ፡ ሥር ፡ ሾልኮ ፡ ገባና ፡ እበረት ፡ ሲደርስ ፡ ወንድሞቹ ፡ ዳለቻውን ፡ ነው ፡ ሰመግማውን ፡ ወይስ ፡ ዶግማውን ፡ ማናቸውን ፡ በሬ ፡ ነው ፡ የማመጣው ፡ እያለ ፡ ይለፈልፍ ፡ ገመር ። ባለቤቱ ፡ ድምፅ ፡ ሰምቶ ፡ የራስጌውን ፡ ዱላ ፡ መዞ ፡ ሐኔውን ፡ አገንድሮ ፡ ቢወጣ ፡ ከበሬ ፡ ጥፍር ፡ ሥር ፡ ተሸሸገ ። እየተዘዋወረ ፡ ቢፈልግም ፡ ሰው ፡ ስላጣ ፡ ሰይጣን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ተመልሶ ፡ ገብቶ ፡ ከቄጡ ፡ ተኛ ። አሁንም ፡ ጥቂት ፡ ቈይቶ ፡ እንደ ፡ በፊቱ ፡ ወንድሞቼ ፡ የማስወጣው ፡ ጥቍሩን ፡ ነውን ፡ ነጩን ፡ ወይስ ፡ ወይንማውን ፡ ወይስ ፡ ደግሞ ፡ በለጭማውን ፡ እያለ ፡ በጕላ ፡ ድምፅ ፡ ሲጠይቅ ፡ ተሰማ ። ባለቤቱም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወጥቶ ፡ በሩን ፡ ቢመረምር ፡ እንደዚያው ፡ በተዋጋ ፡ ተጠርቅሞ ፡ እንደ ፡ ተዘጋ ፡ አገኘው ። ከበረትም ፡ ከብቶቹን ፡ ቢቈጥራቸው ፡ ሁሉም ፡ መኖራቸውን ፡ አረጋገጠ ።



ስለዚህም ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ሰይጣን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከቤቱ ፡ ገብቶ ፡ ተመልሶ ፡ ተኛ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ስንዝሮ ፡ ከበሬው ፡ እግር ፡ ሥር ፡ ወጥቶ ፡ እጕራውን ፡ ከፍቶ ፡ የሠባ ፡ የሠባውን ፡ በሬ ፡ መርጦ ፡ ነድቶ ፡ ለወንድሞቹ ፡ አስረከበ ። እነሱም ፡ አፍአዊ ምስጋና ፡ አደረጉለትና ፡ ቶሎ ፡ ብለው ፡ አንዱን ፡ በሬ ፡ አረዱት ። ብልትም ፡ ማውጣት ፡ እንደ ፡ ገመሩ ፡ በምን ፡ አዋዜና ፡ አፍርንጅ ፡ ሥጋውን ፡ እንብላው ፡ ይሆን ፡ እያሉ ፡ ሲጠያየቁ ፡ ሰምቶ ፡ አቶ ፡ ስንዝሮ ፡ አታስቡ ፡ እኔ ፡ አመጣላችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ ተመልሶ ፡ ከዚያው ፡ ከባለከብቱ ፡ ቤት ፡ በፉካ ፡ ሾልኮ ፡ ገባ ። ወዲያው ፡ እማደያ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ወንድሞቼ ፡ የቅቤውን ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ የድልኹን ፡ ቅል ፡ የማመጣው ፡ እያለ ፡ በመጣራት ፡ ሲለፈልፍ ፡ ተሰማ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባለቤቱ ፡ እረ ፡ ዛሬ ፡ ምን ፡ ጕድ ፡ መጣብን ፡ በማለት ፡ ሚስቱን ፡ ተነሽ ፡ እሳት ፡ አንድጂ ፡ ሲል ፡ አዘዛት ። እሷም ፡ የግዷን ፡ ስትጨነቅ ፡ ከቄጥ ፡ ወርዳ ፡ ማዘንቱ ፡ ላይ ፡ ተቀምጣ ፡ የተዳፈነውን ፡ እሳት ፡ ለማንደድ ፤ እፍ ፡ ስትል ፡ የስእለቱ ፡ ልጅ ፡ ረመጡን ፡ አፍሶ ፡ ባይኗ ፡ ድርግም ፡ አደረገባት ። ወዲያው ፡ ደንግጣ ፡ እረ ፡ በእሳት ፡ አቃጠለኝ ፡ እያለች ፡ እዚያው ፡ እማዘንቱ ፡ ላይ ፡ ወድቃ ፡ ትንፈራፈር ፡ ገመር ። ባልዮውም ፡ የማትረቢ ፡ እሳት ፡ እንኳ ፡ ማንደድ ፡ የማይሆንልሽ ፡ ፈዛዛ ፡ በማለት ፡ በቍጣ ፡ ከቄጡ ፡ ወርዶ ፡ ለማንደድ ፡ አጐንብሶ ፡ እፍ ፡ ሲል ፡ ሳለ ፡ ስንዝሮ ፡ አሁንም ፡ ተንጠራርቶ ፡ ረመጡን ፡ አፍሶ ፡ በዐይኑ ፡ ሞጀረበት ። እሱም ፡ ሰማይና ፡ ምድሩ ፡ ዞሮበት ፤ የሚይዘውንና ፤ የሚጨብጠውንም ፡ አጥቶ ፡ ሲደናበር ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ እማጀቱ ፡ ገብቶ ፡ እየተንገራደደ ፡ የሚፈልገውን ፡ ካገኘ ፡ በኋላ ፡ የቅቤና ፡ የድልኹ ፡ ቅሉን ፡ ተሸክሞ ፡ ወጣና ፡ ለወንድሞቹ ፡ ይኸው ፡ ይገር ፡ መጣሁ ፡ ብሎ ፡ ሰጣቸው ። እነሱ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ አገልግሎቱ ፡ አንዳች ፡ እንኳ ፡ ምስጋና ፡ ሳያደርጉለት ፡ ሥጋውን ፡ ለመብላት ፡ ቸኵለው ፡ ቅቤውንና ፡ ድልኹን ፡ ተቀብለው ፡ ና ፡ ሂድ ፡ ከፊታችን ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ውሻ ፡ አባረሩት ።

ስንዝሮም ፡ እያዘነና ፡ እየተከዘ ፡ እባካችሁ ፡ ወንድሞቼ ፡ ቈሽትና ፡ ወተት ፡ አንገቱን ፡ እንኳ ፡ ስጡኝ ፡ ብሎ ፡ አጥብቆ ፡ ለመናቸው ። ምኞቱ ፡ ይህ ፡ ከሆነ ፡ ይውሰድ ፡ በማለት ፡ ሁሉም ፡ ተስማሙ ። እሱ ፡ ግን ፡ እናቱን ፡ በጣም ፡ ይወዳት ፡ ነበርና ፡ ያገኘውን ፡ ምናምን ፡ ሳይቀንስለት ፡ ይዞ ፡ ወደሷ ፡ በረረ ። ወንድሞቹም ፡ የሚበቃቸውን ፡ ያኽል ፡ ከተመገቡ ፡ በኋላ ፡ የተረፈ

ውን ፣ ሥጋና ፣ ከብቶቹን ፣ መከፈል ፣ ያዙ ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ስንዝሮ ፣ አንዲት ፣ የከሳች ፣ ላም ፣ ነበረችና ፣ ይህችን ፣ እንኳ ፣ ስጡኝ ፣ ሲል ፣ ጠየቃቸው ። እነሱም ፣ ስለ ፣ ፈቀዱለት ፣ ወሰዳትና ፣ በሚገባ ፣ ይዞ ፣ ከሚበላው ፣ እያበላ ፣ በጣም ፣ አወፈራት ፣ መልኳም ፣ እጅግ ፣ አማረ ።

ስንዝሮ ፣ ይህቺ ፣ ላምህ ፣ በምን ፣ ወፈረችልህ ፣ ሲሉ ፣ ወንድሞቹ ፣ ጠየቁት ። እሱም ፣ በተንኰል ፣ አንድ ፣ በመሆኗ ፣ ነው ፣ ሲል ፣ መለሰላቸው ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ እነዚያ ፣ ቂሎች ፣ ለካ ፣ የኛም ፣ አንዳንድ ፣ ቢሆኑ ፣ ይወፍሩ ፣ ኖሯልና ፣ ብለው ፣ አንዳንድ ፣ ከብት ፣ እያስቀሩ ፣ ሌሎቹን ፣ በሙሉ ፣ ፈጁዋቸው ።

ይሁን ፣ እንጂ ፣ ምንም ፣ ቀጥራቸውን ፣ ቢቀንሱ ፣ ሳይወፍሩላቸው ፣ ቀሩ ። ስለዚህም ፣ በቀሩት ፣ መገደል ፣ ተጸጽተውና ፣ ተናደው ፣ የስንዝሮን ፣ ላም ፣ ቀምተው ፣ አርደው ፣ በሉበት ። ትንሹም ፣ ሰው ፣ በላሙ ፣ መታረድ ፣ እጅግ ፣ አለመጠን ፣ አዘነ ፣ ተከዘም ። በኋላም ፣ ሄደና ፣ እባካችሁ ፣ ወንድሞቼ ፣ ሌላው ፣ እንኳ ፣ ቢቀር ፣ ቈዳዋን ፣ ስጡኝ ፣ ብሎ ፣ ለመናቸው ። እነሱም ፣ እንዲወስድ ፣ ፈቀዱለት ። ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ቈዳውን ፣ አድርቆ ፣ ተሸክሞ ፣ በማለዳ ፣ እገበያ ፣ ሄደ ። ሕዝቡ ፣ ከሚገበያይበትም ፣ ቦታ ፣ ትልቅ ፣ ዛፍ ፣ ነበረና ፣ ከዚያ ፣ ላይ ፣ ወጥቶ ፣ ድምጡን ፣ አጥፍቶ ፣ ተቀመጠ ። ገበያውም ፣ በደራ ፣ ጊዜ ፣ ያንን ፣ ቈዳ ፣ በኀይል፡እየመታ፡ የተሰበሰበውን፡ሰው ፣ አሸበረው ። እንዲያውም ፣ በመንጠራራት ፣ እየደጋገመ ፣ በመደብደቡና ፣ መጣብን ፣ እያለ ፣ ነጋዴውና ፣ ገበያተኛው ፣ ሸቀጡንና ፣ ዕቃውን ፣ እየጣለ ፣ በያለበት፡ ተበታተነ። ጥቂት ፣ ቈይቶ ፣ ቀበሌው ፣ ምድረ ፣ በዳ ፣ሲሆን፡ አይቶ ፣ ስንዝሮ ፣ ሆዬ ፣ ከዛፉ ፣ ላይ ፣ ወረደና ፣ ሰዉ ፣ ጥሎ ፣ የሸሸውን ፣ እኽል ፣ ወርቅ ፣ ብርና፡ ማናቸውንም ፣ ሸቀጥ ፣ ሁሉ ፣ በገበያተኛው ፣ አህያና፣ አጋሰስ ፣ ጭኖ ፣ እየነዳ ፣ ሄዶ ፣ ማታ ፣ ከቤቱ ፣ ገብቶ ፣ ለናቱ ፣ አስረከባት ።

ወንድሞቹ ፣ ፈረሶችና ፣ በቅሎዎች ፣ ወርቅና ፣ ብር ፣ ማናቸውንም ፣ ለኑሮ ፣ ጠቃሚ ፣ የሚሆን ፣ ብዙ ፣ ሀብት ፣ ማግኘቱን ፣ አይተው ፣ ይህንን ፣ ሁሉ ፣ ከወዴት ፣ አመጣኸው ፣ ሲሉ ፣ ጠየቁት ። እሱም ፣ ወንድሞቼ ፣ ሆይ ፣



የዚያችን ፣ የላሜን ፣ ቈዳ ፣ በቀጭኑ ፣ እየተለተልኩ ፣ አድርቄ ፣ እገበያ ፣ ባወጣው ፣ ቈዳ ፣ ተወዶ ፣ ኖሮ ፣ ብዙ ፣ ገንዘብ ፣ ስላገኘሁበት ፣ ይህንን ፣ ሁሉ ፣ ሲሳይና ፣ ዕቃ ፣ ለመግዛት ፣ ቻልኩ ፣ ሲል ፣ መለሰላቸው ።



ነጋዴውና ፣ ገበያተኛው ፣ ሸቀጡንና ፣ ዕቃውን ፣ እየጣለ፣ በያለበት ፣ ተበታተነ ።

እነሱም ፣ ይህነን በመስማታቸው ፣ የተረፏቸውን ፣ ከብቶች ፣ አርደው ፣ ቈዳቸውን ፣ ሠንጥቀው ፣ ወደ ፣ ገበያ ፣ ይዘው ፣ ወጥተው ፣ እየተዘዋወሩ ፣ ቈዳ ፣ ግዙ ፣ ይሉ ፣ ጀመር ። በገበያ ፣ ያለውም ፣ ሕዝብ ፣ የምን፣ ቂሎች ፣ ናቸው ፣ የቈዳ ፣ ቋንጣ ፣ ይዘው ፣ የሚዞሩ ፣ እያለ ፣ መሣቂያ ፣ አድርጓቸው ፣ ዋለ ። ማታም ፣ ምንም ፣ ሳይሸጡለት ፣ እንደ ፣ ተሸከሙ ፣ ወደየሰፈራቸው ፣ ተመልሰው ፣ ገቡ ። በማግስቱም ፣ ጧት ፣ ከየቤታቸው ፣ ተጠራርተው ፣ ካንድ ፣ ስፍራ ፣ ላይ ፣ ተሰብስበው ፣ እየዶለቱ ፣ ሲማከሩ፣ ከስድስቱ ፣ አንዱ ፣ ወንድማቸው ፣ እረ ፣ ይህ ፣ ስንዝሮ ፣ ምንኛ ፣ ጠገበ፣ ሲያሞኘን ፣ ያንድ ፣ ላም ፣ ቈዳ ፣ ይህነን ፣ ሁሉ ፣ ገንዘብ ፣ አወጣልኝ ፣ ብሎ ፣ ከብቶቻችንን ፣ አሳርዶ ፣ የገበያ ፣ ሰው ፣ ሁሉ ፣ መሣቂያ ፣ አድርጎን ፣ ዋለ ። እንግዲህ ፣ ምን ፣ ይበጀናል ፣ ሲል ፣ ጥያቄ ፣ አቀረበ ። አንዱ ፣ ደግሞ ፣ እሱን ፣ ከነቤቱ ፣ እናቱን ፣ ጭምር ፣ አቃጥለን ፣ ካላጠፋነው ፣ ምንም፡ ጤና ፣ አናገኝም ፣ ሲል ፣ ሐሳቡን ፣ በመግለጡ ፣ ሁሉም ፣ በምክሩም ፣ ተስማሙ ።

ስንዝሮም ፡ ወንድሞቹ ፡ ሊገድሉት ፡ ማሰባቸውን ፡ ስላወቀ ፡ ሙቀጫውን ፡ ልብስ ፡ አልብሶ ፡ ከቄጥ ፡ ላይ ፡ አስተኝቶ ፡ እናቱን ፡ ይዞ ፡ ተሸሸገ ። ወንድሞቹም ፡ እንደ ፡ ተማከሩት ፡ በጭላንጭል ፡ ሰው ፡ መኖሩን ፡ ካረጋገጡ ፡ በኋላ ፡ በቤቱ ፡ እሳት ፡ ለቀቁበት ። ቆመውም ፡ ቃጠሎውን ፡ ሲመለከቱ ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ በፈነዳ ፡ ቍጥር ፡ እሰይ ፡ የዚያች ፡ የፈርሳም ፡ ልቧ ፡ ፈነዳ ፡ ዐይኗ ፡ ፈነዳ ፡ እያሉ ፡ በመደሰት ፡ ቈይተው ፡ እሳቱ ፡ ሲበርድ ፡ ወደየቤታቸው ፡ ተመለሱ ። በማግስቱ ፡ ስንዝሮ ፡ ከወንድሞቹ ፡ ዘንድ ፡ ሄዶ ፡ እባካችሁ ፡ የቤቴን ፡ አመዱን ፤ እንኳ ፡ ፍቀዱልኝና ፡ ልውሰድ ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ ከመቃጠል ፡ በመዳኑ ፡ እየተደነቁ ፡ ውሰደው ፡ እኛ ፡ ምን ፡ ቸገረን ፡ አመድ ፡ ምን ፡ ያደርግልናል ፡ ሲሉ ፡ መለሱለት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ስንዝሮ ፡ ከገበያ ፡ ባመጣቸው ፡ ኽብቶች ፡ በስልቻ ፡ አመዱን ፡ ጭኖ ፡ ወደ ፡ ማይታወቅበት ፡ አገር ፡ ሲጓዝ ፡ ውሎ ፡ ካንድ ፡ ሀብታም ፡ ግቢ ፡ ሲደርስ ፡ የመንግሥት ፡ እኽል ፡ ጭኛለሁና ፡ አሳድሩኝ ፡ ሲል ፡ ለመነ ። የመንግሥት ፡ እኽል ፡ የጫነ ፡ ክብር ፡ ነውና ፡ ያ ፡ ከበርቴ ፡ ቶሎ ፡ ተቀብሎ ፡ አሰፈረው ። ለከብቱም ፡ አስፈላጊውን ፡ ገፈራ ፡ ሰጥቶ ፡ ስንዝሮን ፡ በሚገባ ፡ አስተናግዶ ፡ ከድንክ ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ አስተኛው ። እኩለ ፡ ሌሊት ፡ ሲሆን ፡ ባለቤቱን ፡ እንቅልፍ ፡ ድብን ፡ አድርጎ ፡ ሲወስደው ፡ አይቶ ፡ ስንዝሮ ፡ ሆዬ ፡ ከተኛበት ፡ ተነሥቶ ፡ ጐተራ ፡ ቀዶ ፡ ነጩን ፡ ጤፍ ፡ አውጥቶ ፡ እሱ ፡ ስልቻ ፡ ድረስ ፡ ነስንሶ ፡ ተመልሶ ፡ ተኛ። ጧት ፡ ከመኝታው ፡ ተነሥቶ ፡ ወንድሞቼ ፡ አጫጭኑኝ ፡ መንገድ ፡ በማለዳ ፡ ነው ፡ አላቸውና ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ጭነቱ ፡ ሄደ ። ወዲያው ፡ እረ ፡ ይህ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ የፈሰሰው ፡ እያለ ፡ እንደ ፡ ተሰረቀ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይቅበጠበጥ ፡ ጀመር ። የቤቱም ፡ ጌታ ፡ ድምፁን ፡ ሰምቶ ፡ ምንድነው ፡ ወንድሜ ፡ ምን ፡ አገኘህ ፡ አለው ። በጭነቴ ፡ ዙሪያ ፡ ነጭ ፡ ጤፍ ፡ ፈሷል ፡ ይህም ፡ እኔ ፡ የያዝኩትን ፡ ይመስላል ፡ እረ ፡ ለመሆኑ ፡ እስቲ ፡ ሽልቻዬን ፡ ልየው ፡ ና ፡ ርዳኝ ፡ አለና ፡ ቢፈታው ፡ አመድ ፡ ሆኖ ፡ አገኙት።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አቶ ፡ ስንዝሮ ፡ የጨዋ ፡ ግቢ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ከቤታችሁ ፡ ባድር ፡ የመንግሥቱን ፡ ጤፍ ፡ እንጐተራችሁ ፡ ስትገለብጡ ፡ ታድሩ ፡ ትዘርፉኝ ፡ እንግዲህ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ አደርጋለሁ ፡ ወደ ፡ መንግሥት ፡ አደባባይ ፡ ሄጄ ፡ እጮኻለሁ ፡ እያለ ፡ ይጋበዝ ፡ ጀመር ። ወዲያው ፡ ከበርቴው ፡ እጫማው ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ እባክህ ፡ ወደ ፡ ዳኛ ፡ አትሂድ ፡ ሀብቴን ፡ አታስወርሰኝ ፡ የመንግሥቱን ፡



ነጭ ፡ ጤፍ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እኔ ፡ እከፍላለሁ ፡ ብሎ ፡ ካስታገሠው ፡ በኋላ ፡ አመዱን ፡ እየገለበጠ ፡ ጤፉን ፡ በስልቻው ፡ ሞልቶ ፡ አጫጭኖ ፡ ወደ ፡ ሀገሩ ፡ ሰደደው ።

ስንዝሮም ፡ ከብቶቹን ፡ እየነዳ ፡ እኽሉን ፡ ይዞ ፡ ሄዶ ፡ ለናቱ ፡ አስረከባት ። ወንድሞቹ ፡ ግን ፡ እንደልማዳቸው ፡ መጥተው ፡ ደግሞ ፡ ይህንን ፡ ሁሉ ፡ ጤፍ ፡ ከየት ፡ አመጣኸው ፡ ሲሉ ፡ ጠየቁት።እሱም ፡ እናንተ ፡ ቤቴን ፡ ብታቃጥሉት ፡ አመዱን ፡ ውድ ፡ ከሆነበት ፡ አገር ፡ ወስጄ ፡ በጤፍ ፡ ለወጥኩት ፡ አለና ፡ መለሰላቸው ።

እነሱም፡እንግዲያውማ፡አመድ፡እንደዚህ፡ያለ፡ጤፍ፡ከለወጠ፡እኛስ፡ቤታችንን፡አናቃጥለምን፡ብለው፡ስድስቱም፡ያላቸውን፡ቤት፡አጋይተው፡አመዱን፡ከያምባው፡በለመኑት፡በአጋሰስ፡ጭነው፡ወደ፡አንድ፡አገር፡ሄደው፡ አመድ ፡ በጤፍ ፡ ለውጡን ፡ እያሉ ፡ መንደር ፡ ለመንደር ፡ ይዞሩ ፡ ጀመር ። ያገሩም ፡ ሰዎች ፡ ይህ ፡ አነጋገር ፡ እንግዳ ፡ ስለ ፡ ሆነባቸው ፡ ከወዴት ፡ የመጣችሁ ፡ ቂሎች ፡ ናችሁ ፡ ለመሆኑ ፡ አመድ ፡ ያድርጋችሁና ፡ በማን ፡ አገር ፡ ነው ፡ አመድ ፡ በነጭ ፡ ጤፍ ፡ ይለወጣል ፡ ሲባል ፡ የሰማችሁት ፡ እያሉ ፡ መሣቂያና ፡ መሣለቂያ ፡ አደረጓቸው ።

እነሱም ፡ በመታለላቸው ፡ በጣም ፡ ተናደውና ፡ ተበሳጭተው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ተመልሰው ፡ እንደ ፡ ገቡ ፡ ስንዝሮን ፡ ገደል ፡ ለመጣል ፡ ምክር ፡ አደረጉ ። ወዲያውኑ ፡ ቀፎ ፡ ሠርተው ፡ ከዚያ ፡ ውስጥ ፡ ለማግባት ፡ ይዘውት ፡ ሳለ ፡ እባካችሁ ፡ ወንድሞቼ ፡ እንዳያቃገኝ ፡ ከራስጌዬ ፡ የማስቀምጠው ፡ ማጭድ ፡ ስጡኝ ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ ይሁን ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ሰጡት ። ቀፎውን ፡ ዘግተው ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ ተሸክመው ፡ ሲጓዙ ፡ በመንገዳቸው ፡ አጠገብ ፡ ዳስ ፡ አዩ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መቼም ፡ ለሆዳቸው ፡ የሞቱ ፡ ነበሩና ፡ ጥቂት ፡ በልተንና ፡ ጠጥተን ፡ እንመለስ ፡ ብለው ፡ የተሸከሙትን ፡ ካንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ አኑረው ፡ ወደ ፡ ድግሱ ፡ ቤት ፡ ሄዱ ። ገና ፡ እግራቸው ፡ እልፍ ፡ ሲል ፡ ስንዝሮ ፡ ሆዬ ፡ በሰጡት ፡ ማጭድ ፡ ቀፎውን ፡ ቀዶ ፡ ወጥቶ ፡ በራሱ ፡ ምትክ ፡ ድንጋይ ፡ ጨምሮ ፡ ቀዳዳውንም ፡ በደንብ ፡ ደፍኖ ፡ ተሸሸገባቸው ። ወንድሞቹም ፡ ሲጠጡ ፡ ውለው ፡ ስክር ፡ ስለ ፡ ተጫጫናቸው ፡ እንደ ፡ መጡ ፡ ቀፎውን ፡ ካኖሩበት ፡ አንሥተው ፡ ወደ ፡ ገደል ፡ ሰደው ፡ ገደልነው ፡ ብለው ፡ ወደየቤታቸው ፡ ተመለሱ ።

ስንዝሮ፡ ግን ፡ ከሞላ ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ ተቀምጦ ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበርና ፡ በማኸል ፡ አንድ ፡ ሴት ፡ ጃኖ ፡ ለብሳ ፡ አገልግል ፡ ተሸክማ ፡ ከሩቅ ፡ ስትመጣ ፡ ተመለከተ ። እንደ ፡ ደረሰችም ፡ ከወንዙ ፡ ዳር ፡ ሲንጎራደድ ፡ አይታ ፡ በመጣራት ፡ ጌታ ፡ እባክዎ ፡ ያሻግሩኝ ፡ ስትል ፡ ለመነችው ። ስንዝሮም ፡ እሺ ፡ ደኅና ፡ ነው ፡ በሴት ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ አይጨክንምና ፡ ያላንድ ፡ ኪሳራ ፡ አንችንም ፡ ስቃሽንም ፡ በደኅና ፡ አድርጌ ፡ አሻግራለሁ ፡ ብሎ ቃል ፡ ሰጣት ። ወዲያው ፡ ጃኖውንና ፡ አገልግሉን ፡ ብቻ ፡ ተሸክሞ ፡ በቁም ፡ ዋና ፡ ካሻገረ ፡ በኋላ ፡ ተመልሶ ፡ መጥቶ ፡ ሴቲቱን ፡ ይዞ ፡ ገባ ። ነገር ፡ ግን ፡ በልቡ ፡ ተንኰል ፡ አስቦ ፡ ኖሮ ፡ ከማኸል ፡ ሲደርስ ፡ ስለ ፡ ለቀቃት ፡ ፈረሰኛው ፡ እያዳፋ ፡ ይዟት ፡ ወረደ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ስንዝሮ ፡ የሚችቱን ፡ ልብስ ፡ ተከናንቦ ፡ ካንድ ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ ተቀምጦ ፡ አገልግሉን ፡ ከፍቶ ፡ ፍትፍቱን ፡ ይበላ ፡ ገ[illegible]መር ። ሊጠግብ ፡ ሲል ፡ አንድ ፡ ፈረሰኛ ፡ በመንገድ ፡ ሲያልፍ ፡ አየና ፡ ጠርቶ ፡ ወንድም ፡ እንደኔ ፡ እርቦህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንካ ፡ ብላ ፡ ብሎ ፡ አገልግሉን ፡ አቀረበለት ። ሰውዬውም ፡ መመገብ ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ይህ ፡ ፈረስህ ፡ ጮሌ ፡ ነውን ፡ እስቲ ፡ ጥቂት ፡ ልሞክረው ፡ አለው ። ስለ ፡ ፈቀደለትም ፡ ተቀምጦ ፡ እስቲሞቀው ፡ ድረስ ፡ በደንገላሳ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ይል ፡ ገ[illegible]መረ ። ወዲያ ፡ ስሄድ ፡ መጣ ፡ ወደዚህ ፡ ስመጣ ፡ ሂደ ፡ እያልክ ፡ ሳትቸኩል ፡ ቀስ ፡ እያልክ ፡ ብላ ፡ ብሎ ፡ አስጠንቅቆት ፡ ነበርና ፡ ወዲያ ፡ ሲሄድ ፡ መጣ ፡ ወዲህ ፡ ሲመጣ ፡ ሂደ ፡ በማለት ፡ ጥቂት ፡ ካላመደ ፡ በኋላ ፡ ልበ ፡ ሙሉው ፡ ስንዝሮ ፡ ኰርኵሮ ፡ ጋልቦ ፡ ጠፋ ።

ባለፈረሱ ፡ ግን ፡ በልማድ ፡ መጣ—መጣ ፡ ሲል ፡ ቈይቶ ፡ በመጨረሻው ፡ ዘወር ፡ ቢል ፡ ላይኑ ፡ እንኳ ፡ የሚያየው ፡ አጣ ።

ስንዝሮ ፡ ግን ፡ ጃኖውን ፡ ደርቦ ፡ በፈረስ ፡ ተቀምጦ ፡ እየተቈነነ ፡ ከቤት ፡ ገባ ። ወንድሞቹም ፡ እንደ ፡ ልማዳቸው ፡ ይህንን ፡ መሳይ ፡ ፈረስና ፡ ልብስ ፡ ከወዴት ፡ አመጣህ ፡ ብለው ፡ አጥብቀው ፡ ጠየቁት ።

እሱም ፡ ገደል ፡ ከገቡ ፡ በዝራው ፡ ድንጐላው ፡ ጃኖው ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ፡ ሞልቷል ፡ አላቸው ። እንግዲያውስ ፡ እባክህ ፡ እኛንም ፡ ስደደን ፡ ሲሉ ፡ ለመኑት ። እሱም ፡ ምን ፡ ከፋኝ ፡ እሺ ፡ እኔ ፡ እንደናንተ ፡ ምቀኛ ፡ አይደለሁም ፡ ሌላ ፡ ከሚጠቀምበት ፡ ወንድሞቼ ፡ ብትወስዱት ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ አለና ፡ ስድስቱንም ፡ ወስዶ ፡ በተርታ ፡ ከገደሉ ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ አቁሞ ፡ አንዳንድ ፡ ያውልህ ፡ ይታይሃል ፡ ብሎ ፡ ሲያጎነብስ ፡ በስውር ፡ ከቂጡ ፡ ገፋ ፡ በማድረጉ ፡ ከድንጋይ ፡ ላይ ፡ ተከስክሶ ፡ ደሙ ፡ ስለ ፡ ቀላ ፡ ዐጥንቱ ፡ ስለ ፡ ነጣ ፡ ለቀሩት ፡ ይኸውላችሁ ፡ ጃኖውን ፡ መዘዘው ፡ አላቸው ።

እንከላ—ቂል ፡ ወንድሞቹም ፡ በመመቀኛኘት ፡ ሳይጨርስና ፡ ሁሉንም ፡ ሳይወስደው ፡ ቶሎ ፡ እኔን ፡ ስደደኝ ፡ እኔን ፡ ስደደኝ ፡ በማለታቸው ፡ ሁሉንም ፡ እያከታተለ ፡ ገደል ፡ አገባቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እናቱን ፡ በመልካም ፡ አድርጎ ፡ አገልግሎና ፡ ጦሮ ፡ ስትሞትም ፡ በወግ ፡ በማዕርግ ፡ ቀበራት ።



ሳይጨርስና ፡ ሁሉንም ፡ ሳይ
ወስድ ፡ ቶሎ ፡ እኔን ፡ ስደደኝ ።

እሱም ፡ በደኅና ፡ ሲኖር ፡ ቈይቶ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የረጋ ፡ ወተት ፡ በጣባ ፡ ቀድቶ ፡ እያማገ ፡ እስቲጠግብ ፡ ምሳውን ፡ ከበላ ፡ በኋላ ፡ ትንሽ ፡ የርጎ ፡ ፍንጣቂ ፡ እሆዱ ፡ ላይ ፡ ጠብ ፡ ብላ ፡ በማየቱ ፡ እሷን ፡ ጐንበስ ፡ ብዬ ፡ እልሳለሁ ፡ ሲል ፡ እተቀመጠበት ፡ ፈንድቶ ፡ ሞተ ፡ ይባላል ።

፨ ሰው ፡ አጠረ ፡ ቀጠነ ፡ ተብሎ ፡ አይናቅም ። ለደግም ፡ ሆነ ፡ ለክፉ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ አእምሮው ፡ ስፋት ፡ ችሎታ ፡ ይኖረዋል ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ የኀይለኛውም ፡ የደካማውም ፡ የብልኁም ፡ የየዋሁም ፡ አሸናፊ ፡ ሞት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይኸን ፡ ዐውቆ ፡ ከተንኰል ፡ ርቆ ፡ ውለታ ፡ ቢስ ፡ ሳይሆኑ ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ እየሠሩ ፡ መኖር ፡ የተመረጠ ፡ መሆኑን ፡ ማወቅ ፡ ይገባናል ።

## ስለ ፡ አንዲት ፡ የቆቅ ፡ ልጅ ፡ በወጥመድ ፡ መያዝ ።

አንዲት ፡ የቆቅ ፡ ልጅ ፡ የስንዴ ፡ እሸት ፡ ትርክክ ፡ ብሎ ፡ በስሎ ፡ በሚገኝበት ፡ እርሻ ፡ አጠገብ ፡ ወጥመድ ፡ ተጠምዶ ፡ አይታ ፡ እናቷን ፡ እናቴ ፡ ሆይ ፡ እሸት ፡ አምሮኝ ፡ ነበር ፡ ከዚህ ፡ ማሳ ፡ ገብቼ ፡ እንዳልበላ ፡ ወጥመድ ፡ ተጠምዷል ፡ ምን ፡ ይሻለኛል ፡ አለቻት ።

እናቷም ፡ ተዪ ፡ ልጄ ፡ ይቅርብሽ ፡ ትያዣለሽ ፡ አይሆንም ፡ ብላ ፡ መከረቻት ።

ልጅቷ ፡ ግን ፡ ግድ ፡ የለሽም ፡ አይዘኝም ፡ ትንሽ ፡ ተክ ፡ ተክ ፡ አድርጌ ፡ ልውጣ ፡ አለችና ፡ ገብታ ፡ ስትበላ ፡ ያ ፡ ወጥመድ ፡ እናቷ ፡ እንደ ፡ ፈራችው ፡ እግሯን ፡ ጥርቅም ፡ አድርጎ ፡ ያዛት ።

መቼም ፡ መከራ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ መገርመሪያ ፡ የሚታሰቡት ፡ ወላጆች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ያች ፡ የናቷን ፡ ምክር ፡ አልሰማ ፡ ያለች ፡ ልጅ ፡ እናቴ ፡ እረ ፡ ተያዝኩልሽ ፡ አለቻት ። እሷም ፡ ምነው ፡ ልጄ ፡ አስቀድሚ ፡ ነግሬሽ ፡ አልነበረምን ፡ አሁን ፡ ታዲያ ፡ ምን ፡ ላደርግልሽ ፡ እችላለሁ ፡ ስትል ፡ መለሰችላት ።

—እማምዬ ፡ እባክሽን ፡ ፍቺልኝ ፡

—በምን ፡ እጄ ?

—ታዲያ ፡ እንዴት ፡ ልሁን ፡ ምን ፡ ይብጀኝ ? የኔ ፡ እናት ፡

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እናት ፡ ለልጅዋ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ምክር ፡ ዐዋቂ ፡ ናትና ፡ ዝም ፡ ብለሽ ፡ የሞትሽ ፡ መስለሽ ፡ ተኚ ፡ ባለወጥመዱ ፡ ሲመጣ ፡ ሞታለች ፡ ብሎ ፡ ፈትቶ ፡ ይለቅሻል ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ታመልጫለሽ ፡ አለቻት ።

ያ ፡ ባለወጥመድ ፡ ሰው ፡ ሰብሉን ፡ ጎብኝቶ ፡ መጣና ፡ ቢመለከት ፡ ዝልፍልፍ ፡ ብላ ፡ ተኝታ ፡ ዐይኗን ፡ አጨልማ ፡ አገኛት ።

እሱም ፡ የሞተች ፡ መሰለውና ፡ አዬ ፡ ጉድ ፡ ወጥመዴ ፡ ቆቅ ፡ ይዞልኝ ፡ ነበረ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በክታለች ፡ እያለ ፡ አዝኖ ።

ጓደኛው ፡ ከበላዩ ፡ ሰብል ፡ ይጠቅ ፡ ነበርና ፡ ወንድም ፡ ብሎ ፡ ተጣርቶ ፡ ወጥመዴ ፡ ቆቅ ፡ ይዞልኝ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በክታ ፡ አገኘኋት ፡ አለና ፡ ነገረው ። ባልንጀራውም ፡ እስቲ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አጉናት ፡ አለው ። እሱም ፡ እያት ፡ አለና ፡



ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወርወር ፡ ቢያደርጋት ፡ ቱር ፡ ብላ ፡ ከሜከዋ ፡ ቀልቅ ፡ አለች ፡ ይባላል ።



እያት ፡ አለና ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወርወር ፡ ቢያደርጋት ፡ ቱር ፡ ብላ ፡ ከሜከዋ ፡ ቀልቅ ፡ አለች ።

፨ ልጆች ፡ ሆይ ፡ ያባትና ፡ የናት ፡ ምክር ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ ተገንዝባችሁ ፡ ከምክር ፡ ከትእዛዝና ፡ ከፈቃድ ፡ አትውጡ ።

## ስለ ፡ አንድ ፡ አባት ፡ ኑዛዜ ።

ሦስት ፡ ወንድ ፡ ልጆች ፡ ያሉት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ ይባላል ። እሱም ፡ አርጅቶ ፡ ጊዜ ፡ ሞቱ ፡ ስለ ፡ ተቃረበ ፡ ሽማግሎችንና ፡ የንስሐ ፡ አባቱን ፡ አስጠርቶ ፡ ኑዛዜ ፡ አደረገ ። ይኸውም ፡ እንዲያው ፡ በደፈናው ፡ አንዱን ፡ ልጄን ፡ መርቄዋለሁና ፡ ርስቴንም ፡ ቤቴንም ፡ ከብቴንም ፡ ያለ ፡ ሀብቴንም ፡ ሁሉ ፡ በሙሉ ፡ ይውሰድ ፡ ምንም ፡ አይነካበት ፡ አለቃ ፡ አድርጌዋለሁ ፡ አንድም ፡ ከብት ፡ ያለፈቃዱ ፡ አይነካበት ። ሁለተኛው ፡ ልጄ ፡ ምንዝር ፡ ሆኖ ፡ ይብላ ፡ የወንድሙን ፡ ቃልና ፡ ትእዛዝ ፡ ሰምቶ ፡ ይደር ። ዳግም ፡ ሦስተኛውን ፡ ልጄን ፡ ረግሜዋለሁና ፡ ከርስቴም ፡ እንዳይበላ ፡ ከቤቴም ፡ እንዳይቀመጥ ፡ ከብትም ፡ እንዳይከፈል ፡ የሚል ፡ ነው ።

ነገር ፡ ግን ፡ የመረቀውንም ፡ ምንዝር ፡ ሆኖ ፡ ይብላ ፡ ያለውንም ፡ የረገመውንም ፡ ለይቶ ፡ ሳይናገር ፡ ቀረ ። ሽማግሎቹና ፡ የንስሓ ፡ አባቱም ፡ ይህንኑ ፡ ሳያጣሩ ፡ ኑዛዜውን ፡ ብቻ ፡ ሰምተው ፡ ተነሥተው ፡ ወደየቤታቸው ፡ ሄዱ ።

ይህም ፡ ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ ያኽል ፡ ሳይቈይ ፡ ጥቂት ፡ ሰንብቶ ፡ ወዲያው ፡ ሞተ ። እነዚያም ፡ ሦስቱ ፡ ልጆች ፡ በገመድ ፡ ታጥቀው ፡ ሲያለቅሱ ፡ ውለው ፡ አባታቸውን ፡ ቀብረው ፡ ማታ ፡ ሕዝቡን ፡ ወደየቤቱ ፡ አሰናበቱ ። አባታቸው ፡ ጥሩ ፡ ክርስቲያን ፡ ነበረና ፡ ልጆቹ ፡ ከሞተበት ፡ ቀን ፡ ዠምረው ፡ ሣልስቱን ፡ ሰባቱን ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ኻያውንና ፡ ሠላሳውን ፡ አስቈርበው ፡ አርባውን ፡ ደግሞ ፡ በመልካም ፡ ደግሰው ፡ አወጡ ። በማግስቱ ፡ ጧት ፡ ሦስቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ ዳሱ ፡ ሳይፈርስ ፡ ዋንጫው ፡ ሳይመለስ ፡ ያባታችንን ፡ ኑዛዜ ፡ ንገሩን ፡ ብለው ፡ የንስሓ ፡ አባትየውንና ፡ ያናዘዙትን ፡ ሽሚግሎች ፡ ጠየቋቸው ።



ያባታችንን ፡ ኑዛዜ ፡ ንገሩን ፡ ብለው ፡ የንስሓ ፡ አባትየውንና ፡ ያናዘዙትን ፡ ሽማግሎች ፡ ጠየቋቸው ።

እነሱም ፡ ብዙ ፡ ምስክሮች ፡ ባሉበት ፡ አባታችሁ ፡ አንደኛችሁን ፡ መርቆ ፡ ያለውን ፡ ሀብት ፡ ሁሉ ፡ ሰጥቶ ፡ አለቃ ፡ አድርጎታል ፤ ሁለተኛውን ፡ ምንዝር ፡ ሆኖ ፡ ለወንድሙ ፡ ታዥ ፡ ቃሉን ፡ ሰምቶ ፡ እንደ ፡ አባት ፡ አክብሮ ፡ እንዲያድር ፡ ሲያደርግ ፡ ሦስተኛውን ፡ ግን ፡ ረግሞ ፡ ክርስቴም ፡ አይብላ ፡ ከወንድሞቹም ፡ አይቀላቀል ፡ ከቤቱም ፡ አይቀመጥ ፡ ብሏል ፡ ሲሉ ፡ ኑዛዜውን ፡ አፈሰሱ ። ልጆቹም ፡ ተራቸውን ፡ የተመረቀውን ፡ ምንዝር ፡ ሆኖ ፡ ይብላ ፡ የተባለውን ፡ የተረገመውን ፡ በስም ፡ በስሙ ፡ ለይታችሁ ፡ ንገሩን ፡ ብለው ፡ ጠየቋቸው ። አናዛዦቹ ፡ ግን ፡ ይህንኑ ፡ ነገረን ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ የገለጸልን ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ስለዚህ ፡ ወደ ፡ ተማረ ፡ ዐዋቂ ፡ ሂዳችሁ ፡ ይለይላችሁ ፡ እንጂ ፡ እኛ ፡ ፍቺውን ፡ አላወቅነውም ፡ አሏቸው ።




ወንድማማቾቹም ፡ ስለ ፡ ተቸገሩ ፡ ተነሥተው ፡ ከንድ ፡ ስሙ ፡ ጥሩ ፡ ፈላስፋ ፡ ዘንድ ፡ ሄዱ ። እሱንም ፡ ምንም ፡ አርጅቶ ፡ ከተቀመጠበት ፡ መንሣት ፡ አቅቶት ፡ ከቤት ፡ ውሎ ፡ መናገር ፡ አውኮት ፡ ቢያገኙት ፡ ጌታችን ፡ ሆይ ፡ አባታችን ፡ ሲሞት ፡ አንደኛችንን ፡ መርቄዋለሁና ፡ ርስቴንም ፡ ከብቴንም ፡ በሙሉ ፡ ይውሰድ ፡ አንደኛችንን ፡ ምንዝር ፡ ሆኖ ፡ ይብላ ፡ ለወንድሙ ፡ ታዥ ፡ ቃሉን ፡ ሰምቶ ፡ እንደ ፡ አባት ፡ አድርጎ ፡ አክብሮ ፡ ይደር ፤ አንደኛችንን ፡ ደግሞ ፡ ረግሜዋለሁ ፡ ክርስቴም ፡ አይብላ ፡ ከቤቴም ፡ አይቀመጥ ፡ ከብቴንም ፡ አይንካ ፡ ከልጆቼም ፡ ዘንድ ፡ አይድረስ ፡ ብሎ ፡ ተናግሮ ፡ ሞተ ። ነገር ፡ ግን ፡ የተመረቀውን ፡ ምንዝር ፡ የሚሆነውን ፡ የተረገመውን ፡ በመለየት ፡ አልገለጸልንም ። አንተ ፡ ምስጢርን ፡ የምትመረምር ፡ ዐዋቂ ፡ መሆንክን ፡ ስለ ፡ ሰማን ፡ ይህንን ፡ ነገር ፡ ፈትህ ፡ ትነግረን ፡ ዘንድ ፡ ይኸው ፡ ወዳንተ ፡ መጥተናል ፡ አሉት ። ፈላስፋውም ፡ ዝርዝር ፡ ጉዳዩን ፡ ከዳመጠ ፡ በኋላ ፡ የዚህ ፡ ፍቺው ፡ በውነት ፡ ለኔ ፡ አልተገለጸልኝም ፤ ስለዚህ ፡ በጣም ፡ የተማረ ፡ ሰውነቱም ፡ ከኔ ፡ ልጅ ፡ የሆነ ፡ ታላቅ ፡ ወንድም ፡ አለኝና ፡ ከሱ ፡ ዘንድ ፡ ብትሄዱ ፡ ትርጕሙን ፡ ሊነግራችሁ ፡ ይችላል ፡ አላቸው ።

ወንድማማቾቹም ፡ ይኸ ፡ ትንሹ ፡ እንደዚህ ፡ ያረጀና ፡ የወደቀ ፡ ሲሆን ፡ ትልቁማ ፡ ምን ፡ መናገር ፡ ይችላል ፤ እንዲያው ፡ መንገድ ፡ መቶን ፡ እንመጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ብለው ፡ ሄዱ ። በደረሱም ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ታላቅ ፡ የተባለውን ፡ ወንድም ፡ ገና ፡ ያልቀና ፡ ወይፈን ፡ ሲገርፍ ፡ አገኙት ። እነሱም ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ የመጡበትን ፡ ጉዳይ ፡ ዘርዝረው ፡ ከስረዱ ፡ በኋላ ፡ ችግራቸውን ፡ የሚያስወግዱበትን ፡ ብልኀት ፡ እንዲነግራቸው ፡ ለመኑት ። ነገሩን ፡ ሰምቶ ፡ በልቡናው ፡ ገምቶ ፡ አውጥቶና ፡ አውርዶ ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ ምስጢሩ ፡ የረቀቀ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ለታላቅ ፡ ወንድሜ ፡ እንጂ ፡ ለኔ ፡ የሚገለጽልኝ ፡ አልሆነም ። ስለዚህ ፡ ፈልጋችሁ ፡ ንገሩት ፡ ስላላቸው ፡ ትንሹ ፡ በማርጀቱ ፡ ትልቁ ፡ ወይፈን ፡ እየገረፈ ፡ በማቅናቱ ፡ እየተደነቁና ፡ እየተገረሙ ፡ አንጋፋ ፡ ወደ ፡ ሆነው ፡ ዘንድ ፡ ሄዱ ።

ይኸም ፡ ግልገል ፡ በቅሎ ፡ በልጓም ፡ ይዞ ፡ ሲገራ ፡ አገኙት ። ለዚህ ፡ ለሦስተኛው ፡ ሊቅ ፡ ስለ ፡ ወንድማማቾቹ ፡ የተገላቢጦሽ ፡ እርጅና ፡ መደነቃቸውን ፡ ሳይጀምር ፡ ያመጣጣቸውን ፡ ሁኔታና ፡ ችግራቸውን ፡ ዘርዝረው ፡

ገለጹለት ። ጉዳዩን ፡ በሙሉ ፡ ካዳመጠ ፡ በኋላ ፡ አባታችሁ ፡ በጣም ፡ ብልኅ ፡
ሰው ፡ ኖሯል ፡ የተናዘዘው ፡ መልካም ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለ ።
ያ ፡ አርጅቶ ፡ ከመሬት ፡ መነሣት ፡ አቅቶት ፡ ያያችሁት ፡ ትንሹ ፡ ወንድሜ ፡



ግልገል፡በቅሎ፡በልጓም፡
ይዞ ፡ ሲገራ ፡ አገኙት ።

ነው ። ለቤት ፡ ለንብረት ፡ ከደረሰም ፡ ወዲህ ፡ ቢሠራ ፡ ጠብ ፡ አይልለትም፡
በሕፃንነቱ ፡ እናቱና ፡ አባቱ ፡ ሞተውበት ፡ በሰው ፡ ቤት ፡ ሲንገላታ ፡ የሰው፡
ፊት ፡ እንደሳት ፡ ሲጠብሰው ፡ ከንዱ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ቤት ፡ ሲል ፡ ያደገ ፡ ነው ።
ደግሞ ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ ልጆች ፡ ራስ ፡ በራስ ፡ ወልዷል ። እነዚህም ፡ የሚ
በሉት ፡ ምግብና ፡ የሚለብሱት ፡ ልብስ ፡ እየተቸገሩ ፡ ባለቀሱበት ፡ ቍጥር ፡
በዕድሉ ፡ ስለሚያዝንና ፡ ከልጆቹ ፡ ጋራ ፡ ስለሚሠቃይ ፡ እንባው ፡ ፊቱን ፡
ጣፊያ ፡ አስመስሎታል ። ጺትም ፡ ነጋ ፡ አልነጋም ፡ ብሎ ፡ ነጠላውን ፡ ለል
ጆቹ ፡ አልብሶ ፡ እሱ ፡ ትንሽ ፡ የበግ ፡ ሌጦ ፡ እትከሻው ፡ ላይ ፡ ጣል ፡ አድርጎ ፡ ማጭ
ዱን ፡ ይዞ ፡ ብርድ ፡ እየፈደፈደው ፡ ላንድ ፡ ባለጸጋ ፡ የሞያተኛ ፡ ለማጨድ ፡ ይሄ
ዳል ። እርሻውም ፡ ከደጋ ፡ ላይ ፡ በመሆኑ ፡ ያ ፡ የጥቅምት ፡ ውርጭ ፡ ከጢት ፡
እስከ ፡ ማታ ፡ ሲወርድበት ፡ ይውልና ፡ ቈፈን ፡ እንደ ፡ ያዘው ፡ አንድ ፡ አምስ
ትና ፡ ስድስት ፡ ነዶዎች ፡ ተሰጥቶት ፡ ይመጣል ። ማታም ፡ ይህንኑ ፡ ለልጆቹ ፡
ያቀምስና ፡ በዚሁ ፡ አድሮ ፡ ይውላል ። ስለዚህ ፡ በችግር ፡ ተቈራምዶ ፡ በመ
ኖሩ ፡ ይኸው ፡ እንዳያችሁት ፡ ከመሬት ፡ መነሣት ፡ አቅቶታል ። ወይፈን ፡ የሚ
ያቀናው ፡ የሱ ፡ ታላቅ ፡ ደግሞ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ለሰው ፡ የሚተርፍ ፡ ሀብት ፡
ባይኖረው ፡ ራሱን ፡ ችሎ ፡ ልጆቹን ፡ እንደ ፡ ልባቸው ፡ አብልቶና ፡ አልብሶ ፡ ያድ
ራል ። ነገር ፡ ግን ፡ ግልፍተኛና ፡ ብስጩ ፡ በመሆኑ ፡ ሸብቶ ፡ ይታያል ። እኔ ፡
ግን ፡ ክብርና ፡ ምስጋና ፡ ለፈጣሪዬ ፡ ይግባውና ፡ የናትና ፡ ያባቴ ፡ ትዳራቸው፡



በናጀለበት ፡ ጊዜ ፡ በመወለዴ ፡ ችግር ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሳላውቅ ፡ ወተ
ትና ፡ ጮማ ፡ ሳይለየኝ ፡ በመንቀባረር ፡ ትምህርቴንም ፡ እየተማርኩ ፡ ያደ
ግሁ ፡ ነኝ ። በቁማቸውም ፡ ደኅና ፡ የጨዋ ፡ ልጅ ፡ ድረው ፡ ሀብታቸውን ፡
ከፍለው ፡ ሰጥተውኝ ፡ እንደ ፡ ልቤ ፡ በጌትነት ፡ ስለምኖር እንደምታዩኝ ፡
የሁለቱም ፡ ታናሽ ፡ እንጂ ፡ ታላቅ ፡ መስዬ ፡ አልታይም ። ሰውን ፡ ያለጊዜው ፡
የሚያስረጅውና ፡ የሚያገሰቍለው ፡ ማጣት ፡ የሰው ፡ ፊት ፡ ማየት ፡ መበሳ
ጨት ፡ መቈጨትና ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ተቃዋሚዎች ፡ በገጠሙት ፡ ጊዜ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ የዕድሜ ፡ ብዛት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። አሁንም ፡ ስለ ፡ መጣችሁ
በት ፡ ጉዳይ ፡ እንዳስረዳችሁ ፡ ዘመዶቻችሁን ፡ ጎረቤቶቻችሁን ፡ ያባታች
ሁን ፡ የንስሓ ፡ አባትና ፡ ያናዘዙትንም ፡ ሽማግሎች ፡ ሁሉ ፡ ሰብስባችሁ ፡
ከወላጃችሁ ፡ መቃብር ፡ ዶማ ፡ ይዛችሁ ፡ ቈዩኝ ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ ምስ
ጋና ፡ አቅርበው ፡ ተሰናብተውት ፡ ሄዱ ።

እንደ ፡ ታዘዙትም ፡ ሁሉ ፡ ፈጽመው ፡ ሲጠባበቁ ፡ ፈላስፋው ፡ መጣና ፡
በሉ ፡ እንግዲህ ፡ ይህንን ፡ መቃብር ፡ ቈፍሩ ፡ አሁን ፡ አባታችሁ ፡ የኑዛዜ
ውን ፡ ትርጉም ፡ ይገልጽላችኋል ፡ አላቸው ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንደኛው ፡ ልጅ ፡ ርስቱም ፡ ቤቱም ፡ ከብቱም ፡ ማናቸ
ውም ፡ አዱኛው ፡ ይቅርብኝ ፡ እንጂ ፡ ያባቴን ፡ መቃብር ፡ አልቈፍርም ፡
የትም ፡ አገር ፡ ተሰድጄ ፡ እየለመንኩ ፡ እኖራለሁ ፡ አለና ፡ እንቢ ፡ አለው ።

ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ ዶማውን ፡ አንሣና ፡ ጥቂት ፡ እንደ ፡ ቈፈረ ፡ እኔ ፡
ሆዴ ፡ ቡጭ ፡ ቡጭ ፡ አለብኝ ፡ አለና ፡ ተወ ። ሦስተኛው ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ቈፍሬ፡
አስመሰክራለሁ ፡ እንጂ ፡ እንደዚሁ ፡ በከንቱ ፡ የተመረቀውን ፡ ምንዝር ፡



እኔ ፡ ቈፍሬ ፡ አስመሰክራለሁ፡
እንጂ ፡ እንደዚሁ ፡ በከንቱ ፡
የተመረቀውን ፡ ምንዝር ፡
ሆኖ ፡ ይብላ ፡ የተባለውንና ፡
የተረገመውን ፡ ሳላውቅ ፡ አል
ተውም ፡ . . . . . . . . .

ሆኖ ፡ ይብላ ፡ የተባለውንና ፡ የተረገመውን ፡ ሳላውቅ ፡ አልተውም ፡ ብሎ፡ ሰናፊሉን ፡ ባጭር ፡ ታጥቆ ፡ ሲቈፍር ፡ ድራሩን ፡ ነካው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የተማረው ፡ ምስጢር ፡ ዐዋቂው ፡ ፈላስፋ ፡ ዶማውን ፡ ተቀብሎ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ መካከል ፡ ቆሞ ፡ ንግግሩን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ዠመረ ። ሰማችሁ ፡ ወንድሞቼ ፤ ይህ ፡ የሞተ ፡ ሰው ፡ በጣም ፡ ዕውቀት ፡ የተመላው ፡ ኖሯል ። አንዱን ፡ ልጄን ፡ መርቄዋለሁ ፡ ያለው ፡ ይህ ፡ አሁን ፡ ያበቴ ፡ ርስቱ ፡ ቤቱና ፡ ከብቱም ፡ ማናቸውም ፡ አዱኛው ፡ ይቅርብኝ ፡ ተሰድጄ ፡ እኖራለሁ ፡ እንጂ ፡ መቃብሩን ፡ አልቈፍርም ፡ ያለው ፡ ነው ። ምንዝር ፡ የተባለው ፡ ልጁም ፤ ይህ ፡ ጥቂት ፡ ሞክሮ ፡ ሆዴ ፡ ተንበጫበጨብኝ፡ ብሎ ፡ መቈፈሩን ፡ የተወው ፡ ነው ። ቈፍሬ ፡ አስመሰክራለሁ ፡ እንጂ ፡ የተመረቀውንና ፡ ምንዝር ፡ ሆኖ ፡ ይብላ ፡ የተባለውን ፡ የተረገመውንም ፡ ሳላውቅ ፡ አልተውም ፡ ብሎ ፡ እስከ ፡ ድራሩ ፡ ድረስ ፡ የቈፈረው ፡ ግን ፡ የተረገመው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የኑዛዜውን ፡ ትርጕም ፡ በመዘርዘር ፡ አስረዳ ። የተሰበሰቡትም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በሆነው ፡ ነገር ፡ ተገርመውና ፡ ተደንቀው ፡ ፈላስፋውን ፡ ካመሰገኑ ፡ በኋላ ፡ ተበታትነው ፡ ተለያዩ ፡ ይባላል ።



ሰማችሁ ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ ይህ ፡ የሞተ ፡ ሰው ፡ በጣም ፡ ዕውቀት ፡ የተመላው ፡ ኖሯል ።

፨ ልጆች ፡ ሆይ ፤ በስውር ፡ ክፉ ፡ አድርጋችሁ ፡ በደባባይ ፡ ተፈርዶባችሁ፡ ውርደት ፡ ቅሌት ኀፍረት ፡ እንዳያገኛችሁ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ደግ ፡ ሥራችሁ ፡ እንዲፈረድላችሁ ፡ መሆን ፡ ይገባችኋል ። ደግሞ ፡ መማርና ፡ ዕውቀት ፡ ማግኘት ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ለሰው ፡ የተሰወረውን ፡ ምስጢር ፡ መርምሮ ፡



ለመረዳት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በትምህርታችሁ ፡ ለመትጋትና ፡ ለመጣጣር ፡ ከመሸቀዳደም ፡ አትበዝኑ ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ መልካም ፡ ኑሮ ፡ ጤና ፡ አስገኝቶ ፡ የሰውን ፡ ዕድሜ ፡ የሚቀጥል ፡ መሆኑንም ፡ ባለመዘንጋት ፡ ትጋትን ፡ ለማሻሻል ፡ መታገል ፡ እንደሚገባችሁ ፡ አስተውሉ ።

## አንድ መነኰሴና ነብር ።

አንድ ፡ ደካማ ፡ የሆኑ ፡ መነኰሴ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከዳገት ፡ ላይ ፡ ሲቈፍሩ ፡ አዳኞች ፡ የሚያባርሩት ፡ ነብር ፡ መጥቶ ፡ አባ ፡ እባክዎ ፡ አድኑኝ ፡ አላቸው ።

መነኰሲውም ፡ ከስልቻቸው ፡ ውስጥ ፡ አግብተው ፡ አጥፋቸውን ፡ አልብሰው ፡ እንደ ፡ ደበቁት ፡ አዳኞቹ ፡ መጥተው ፡ አባታችን ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዋሉ ፡ አንድ ፡ ነብር ፡ በዚህ ፡ ሲያልፍ ፡ አላዩምን ፡ አሏቸው ።



አዳኞች ፡ የሚያባርሩት ፡ ነብር ፡ መጥቶ ፡ አባ ፡ እባክዎ፡አድኑኝ ፡ አላቸው ።

መነኰሴውም ፡ ልጆቼ ፡ ከቍፋሮዬ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ቀና ፡ ስላላልኩ ፡ እረ ፡ አላየሁትም ፡ ሲሉ ፡ መለሱላቸው ። አዳኞቹ ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ የማታ ፡ ማታ ፡ መነኰሲው ፡ ነብሩን ፡ እንግዲህ ፡ የሚፈልጉህ ፡ የሉም ፡ ርቀዋልና ፡ ተነሥተህ ፡ ጥፋ ፡ እኔም ፡ መሸቶብኛልና ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ እገባለሁ ፡

ብለው ፡ ከስልቻቸው ፡ ሲያወጡት ፡ አስረው ፡ ጠሜን ፡ አውለው ፡ እንዲሁ ፡ ልሄድ ፡ ነውን ፤ እርስዎን ፡ እበላለሁ ፡ እንጂ ፡ አላቸው ።

ከሞት ፡ ባዳንኩህ ፡ ፈንታ ፡ ልትበላኝ ፡ ቢሉት ፡ አዎን ፡ አላቸው ። እንግዲያውስ ፡ አራዊት ፡ በሸንጎ ፡ ተሰብስበው ፡ ይፍረዱ ። ደግ ፡ መልካም ፡ ይፍረዱ ፡ ይፍረዱ ፡ ተባብለው ፡ አራዊት ፡ ከተሰበሰቡበት ፡ ሸንጎ ፡ ቀርበው ፡ ነገራቸውን ፡ አመለከቱ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዝንጀሮ ፡ ተነሣና ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ከስልቻ ፡ ውስጥ ፡ አስገብተው ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ብሎ ፡ የሚመገበውን ፡ እንዳይፈልግ ፡ አስረው ፡ አውለው ፡ አሁን ፡ ምን ፡ ይሁን ፡ ብለው ፡ ነው ፡ ሊበላዎ ፡ ይገባል ፡ በማለት ፡ ፈረደባቸው ።

ፍየል ፡ ደግሞ ፡ ጠሙን ፡ አውለው ፡ ምን ፡ ይብላ ብለው ፡ ነው ፡ ሊበላዎ ፡ ይገባል ፡ ብላ ፡ ፈረደች ።

ውሻ ፡ ኸርብ ፡ የቀሩትም ፡ ሁሉ ፡ በየተራቸው ፡ እየተነሡ ፡ ሊበላዎ ፡ ይገባዋል ፡ እያሉ ፡ ተቀመጡ ።

ጦጣ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀርታ ፡ ነበርና ፡ እንደ ፡ መጣች ፡ አየና ፡ ነብሩ ፡ ይኸውልሽ ፡ እንከዎ ፡ ጠጪት ፡ ጠሜን ፡ አውለው ፡ ማታ ፡ ሂድ ፡ አሉኝ ፤ ይኸንን ፡ ፍርድ ፡ እስቲ ፡ አንቺ ፡ እዩልኝ ፡ አላት ። ወንድሜ ፡ አያ ፡ ነብሮ ፡ እኔ ፡ ከዛፍ ፡ ላይ ፡ እንጂ ፡ ከምድር ፡ ተቀምጬ ፡ መፍረድ ፡ አላውቅም ፡ አለችው ። እሱም ፡ እንደ ፡ ፈቀድሽ ፡ የትም ፡ ሁኚ ፡ ግድ ፡ የለም ፤ ከዛፉም ፡ ከሆነ ፡ ነገሩ ፡ በዩ ፡ ውጪና ፡ ፍረጂ ፡ አላት ።

ከዛፉ ፡ ላይ ፡ ወጣችና ፡ አባ ፡ አያ ፡ ነብሮን ፡ ከዳኞች ፡ እኔ ፡ አዳንኩት ፡ እያሉ ፡ የሚፎክሩት ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ ነው ፡ እርስዎ ፡ ደካማ ፡ ነዎት ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሁሉን ፡ የሚያንቀጠቅጥና ፡ የሚያሸንፍ ፡ ጐበዝ ፡ ነው ፡ እረ ፡ ለነገሩ ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ አኳኋን ፡ ነው ፡ ያዳኑት ፤ እንጃ ፡ እውነት ፡ አይመስለኝም ፡ እስቲ ፡ ለመሆኑ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርገው ፡ እንደ ፡ ሸሸጉት ፡ ያሳዩኝ ፡ አለቻቸው ።

መነኮሴውም ፡ ይኸውልሽ ፡ እንከዩ ፡ ጠጪት ፡ እንደዚህ ፡ አድርጌ ፡ ነው ፡ ያዳንኩት ፡ አሉና ፡ ከስልቻቸው ፡ ውስጥ ፡ አግብተው ፡ አጥፋቸውን ፡ አልብሰው ፡ ቢያሳዩዋት ፡ አባ ፡ እንግዲህ ፡ አባ ፡ እንግዲህ ፡ አለቻቸው ።



ቀና ፡ ብለው ፡ አየት ፡ ቢያደርጓት ፡ የስልቻውን ፡ አፍ ፡ አስረው ፡ ይደብድቡት ፡ በማለት ፡ አመለከተቻቸው ። እሳቸውም ፡ እንዳሳየቻቸው ፡ አቁማዳውን ፡ አስረው ፡ ኀይለኛውን ፡ ባለጋራ ፡ በቈመጥ ፡ ነርተው ፡ ገደሉት ፡ ይባላል ።



እስቲ ፡ ለመሆኑ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርገው ፡ እንደ ፡ ሸሸጉት ፡ ያሳዩኝ ።

፨ በፍርድ ፡ ላይ ፡ መፍራትና ፡ ማድላት ፡ አይገባም ። ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ለተንኰለኛ ፡ ሰው ፡ ደግ ፡ ቢሠሩለት ፡ ሸሩን ፡ አይተውም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ፍርድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነውና ፡ ተንኰሉ ፡ ያጠፋዋል ።

## ስለ ፡ አንዲት ፡ ገበያተኛ ፡ ሴት ።

አንዲት ፡ ሴትኛ ፡ አዳሪ ፡ ገበያ ፡ ወጥታ ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ ስትመለስ ፡ ከመንገድ ፡ ዳር ፡ አንድ ፡ ማሽላ ፡ ጠባቂ ፡ አገኘችና ፡ ሰላምታ ፡ ሰጠችው ። እሱም ፡ እኅቴ ፡ ሆዬ ፡ ዛሬ ፡ አንቺ ፡ ዘንድ ፡ መጥቼ ፡ ነውና ፡ እራቴን ፡ የምበላው ፡ ተዘጋጅተሽ ፡ እንድትቈዩኝ ፡ አላት ። እሷም ፡ እሺ ፡ ወንድሜ ፡ እንዳልክ ፡ ፈቃድህን ፡ እፈጽማለሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የማሽላ ፡ እሸት ፡ አምሮኛልና ፡ አንድ ፡ ሸክም ፡ ይዘህልኝ ፡ ና ፡ አለችውና ፡ መንገዷን ፡ ቀጠለች ። ሁለተኛ ፡ ደግሞ ፡

አንድ ፡ የፍየል ፡ እረኛ ፡ አገኘችና ፡ እሱም ፡ እንደዚያው ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ ሰውዬ ፡ ዛሬ ፡ አዳሬ ፡ ካንቺ ፡ ዘንድ ፡ ነውና ፡ እንድትጠብቂኝ ፡ አላት ። አሁንም ፡ እሺ ፡ ወንድሜ ፡ እንደ ፡ ፈቃድህ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሥጋ ፡ አምሮኛልና ፡ ከነዚህ ፡ ከፍየሎችህ ፡ አንድ ፡ ደኅና ፡ ጠቦት ፡ ይዘህልኝ ፡ እንድትመጣ ፡ አለችው ።

ከሱም ፡ አጠገብ ፡ ገና ፡ ምንም ፡ ያኽል ፡ ሳትርቅ ፡ አንድ ፡ የላሞች ፡ እረኛ ፡ አገኘች ። ለዚህም ፡ ሰላምታ ፡ ሰጥታው ፡ አለፍ ፡ ስትል ፡ አንቺ ፡ ሴት ፡ እስቲ ፡ እባክሽ ፡ ቈዪኝ ፡ አንድ ፡ የምነግርሽ ፡ ጕዳይ ፡ አለኝ ፡ አላት ። እሷም ፡ ወደርሱ ፡ መለስ ፡ ብላ ፡ ወንድሜ ፡ ምነው ፡ በደኅና ፡ ነውን ፡ ቈዪኝ ፡ የምትለኝ ፡ ስትል ፡ ጠየቀችው ። ጕዳዩስ ፡ ቀላል ፡ ነው ፡ እኅቴ ፡ ሆይ ፡ ዛሬ ፡ እራቴን ፡ ካንቺ ፡ ቤት ፡ ለመብላት ፡ አስቢያለሁና ፡ ፈቃድ ፡ ታደርጊልኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መለሰላት ። ምን ፡ ቸገረኝ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ወተት ፡ ስላማረኝ ፡ አንተ ፡ ይኸው ፡ እንዳየሁህ ፡ ባለብዙ ፡ ላሞች ፡ ነህና ፡ አንድ ፡ ቅል ፡ ርጎ ፡ ይዘህልኝ ፡ እንድትመጣ ፤ እኔም ፡ ተደራጅቼ ፡ እጠብቅሃለሁ ፡ በማለት ፡ ሸንግላው ፡ ሄደች ።

አራተኛ ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ዱግ ፡ ሠጋር ፡ በሆነች ፡ በቅሎ ፡ ተቀምጦ ፡ አሽከሩን ፡ ነፍጥ ፡ አሲዞ ፡ ሲያሠግር ፡ ደረሰባት ። ከወዴት ፡ ትመጫለሽ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃት ። እሷም ፡ ከገበያ ፡ ነው ፡ ጌታዬ ፡ ብላ ፡ መልሳለት ፡ እየተጨዋወቱ ፡ ጥቂት ፡ መንገድ ፡ እንደ ፡ ተጓዙ ፡ ሎሌውን ፡ ከበቅሎ ፡ ላይ ፡ አውጣት ፡ አለውና ፡ አፈናጧት ፡ እስከ ፡ ቤቷ ፡ ድረስ ፡ ይዟት ፡ ሄደ ። እንግዳህ ፡ ማታ ፡ መጥቼ ፡ ከዚሁ ፡ ቤት ፡ እራት ፡ እበላለሁና ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ እንዳትነጋገሪ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ደርሼ ፡ ልምጣ ፡ አላት ። ጥቂት ፡ ቈይቶም ፡ ጊዜው ፡ መምሸት ፡ ስለ ፡ ጀመረ ፡ ያ ፡ ከገበያ ፡ ስትመጣ ፡ የቀጠረችው ፡ እኽል ፡ ጠባቂ ፡ እንዳዘዘችው ፡ አንድ ፡ ሸክም ፡ የማሽላ ፡ እሸት ፡ ተሸክሞ ፡ መጣ ። እሷም ፡ የያዘውን ፡ ከተቀበለች ፡ በኋላ ፡ ሰውየውን ፡ ከማጀት ፡ ገብቶ ፡ እንዲቀመጥ ፡ አደረገችው ። ከሱ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ያ ፡ የፍየል ፡ እረኛ ፡ መልከም ፡ ሰናፊል ፡ አጥልቆ ፡ ረኸም ፡ ጥብቆ ፡ ለብሶ ፡ ድጉን ፡ ታጥቆ ፡ ኩታውን ፡ አጣፍቶ ፡ ፍየል ፡ እየሳበ ፡ መጣ ። እሱንም ፡ ከብቱን ፡ ተረከበችና ፡ ከድብኝት ፡ ውስጥ ፡ ደበቀችው ። ሦስተኛው ፡ ባለላሙ ፡ ርጎውን ፡ ይዞላት ፡ ደረሰ ፤ የወተቱንም ፡ ቅል ፡ ተቀብላ ፡ ከማዘንቱ ፡ በላይ ፡ ከውሲያኑ ፡ ላይ ፡ ከሰቀለች ፡ በኋላ ፡ ሰውየውን ፡ ከልጋ ፡ ሥር ፡ አስገብታ ፡ ሸሸገችው ።



በመጨረሻው ፡ በበቅሎ ፡ ይዟት ፡ የመጣው ፡ መኰንን ፡ አሽከሩን ፡ አስከትሎ ፡ ነፍጡን ፡ አሲዞ ፡ ከተፍ ፡ አለ ። እሷም ፡ ቤቷን ፡ አንጥፋ ፡ ተዘጋጅታ ፡ ትጠብቀው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ርጎ ፡ የያዘው ፡ ጮጮ ፡ ከተሰቀለበት ፡ በታች ፡ ማዘንቱ ፡ ላይ ፡ አስቀመጠችው ።

ጥቂት ፡ ጭውውት ፡ እንደ ፡ ያዙም ፡ ያ ፡ ማሽላ ፡ ጠባቂ ፡ አረኽ ፡ ላረኽ ፡ ከጠጣና ፡ ከዝንጀሮ ፡ ጋራ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ሲሮጥ ፡ በመዋሉ ፡ ደክሞት ፡ እንቅልፍ ፡ ይዞት ፡ ኖሮ ፡ ከማጀት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሲቃዥ ፡ ተው ፡ በር ፡ በሩን ፡ ቅደመው ፡ አለ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዱጉ ፡ ተነሥቶ ፡ እሸሻለሁ ፡ ሲል ፡ የተሰቀ



ርጎው ፡ በጭንቅላቱ ፡ ላይ ፡ ተከለበሰበት ።

ለውን ፡ የወተት ፡ ቅል ፡ በራሱ ፡ ስለ ፡ መታው ፡ ርጎው ፡ በጭንቅላቱ ፡ ላይ ፡ ተከለበሰበት ። ተደናግጦም ፡ ነፍጡን ፡ እንኳ ፡ ሳይዝ ፡ ከነሎሌው ፡ ፈረጠጠ ። ባለፍየሉም ፡ ድብኝቱን ፡ በታትኖ ፡ ኩታውን ፡ ጥሎ ፡ አውጭኝ ፡ እግሬ ፡ አለ ። ባለወተቱም ፡ ከተሸሸገበት ፡ ብድግ ፡ እላለሁ ፡ ሲል ፡ አልጋውን ፡ አንሥቶ ፡ በውኃ ፡ እንስራውና ፡ በቡሖ ፡ ዕቃው ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ጣለው ፡ ሸክላው ፡ እንክትክት ፡ ስብርብር ፡ ብሎ ፡ ገል ፡ ዐፈር ፡ ሆነ ። መውጫውም ፡ ጠፍቶበት ፡ ሲደናበር ፡ መዝጊያውን ፡ ከሥር ፡ ሰቅስቆ ፡ ወንዴውን ፡ ነቅሎ ፡ እልም ፡ ብሎ ፡ ጠፋ ።

ያ ፡ ወተት ፡ የተደፋበት ፡ ሹም ፡ ነፍጡን ፡ ጥሎ ፡ ነፍሱን ፡ አጥቶ ፡ እየተክነፈነፈ ፡ ከሮጠ ፡ በኋላ ፡ ከመንገድ ፡ አሽከሩን ፡ አንተ ፡ ራሴን ፡ ተመትቻለሁና ፡ እስቲ ፡ እባክህ ፡ ጕድቶኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቆም ፡ ብለህ ፡ አይተህ ፡ ንገረኝ ፡ አለው ። ሎሌውም ፡ ጭንቅላቱ ፡ ነጭ ፡ ነገር ፡ ለብሶ ፡ አየና ፡ እረ ፡

ጌታዬ ፡ ምንም ፡ አልተረፋ ፡ ደምዎ ፡ አልቆ ፡ አንጐልዎ ፡ ወጥቷል ፡ እንዲያውም ፡ የሚድኑ ፡ አይመስልም ፡ አሁን ፡ ግን ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ ከምንገባ፡ እናምልጥ ፡ ብሎ ፡ ሸሽታቸውን ፡ ቀጠሉ ።

ባለፍየሉም ፡ ባለወተቱም ፡ እንዲሁ ፡ እየተከታተሉ ፡ ሄዱና ፡ ያው ፡ በሬት ፡ ያገኛት ፡ ባለማሽላው ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ቀረ ። እሱም ፡ ይህንን ፡ ፍጅትና ፡ ሽብር ፡ ሳይሰማ ፡ ቈይቶ ፡ በመጨረሻው ፡ ከእንቅልፉ ፡ ከነቃ ፡ በኋላ ፡ ከዚያች ፡ ሴት ፡ ቤት ፡ አድሮ ፡ በማግስቱ ፡ ጧት ፡ አፋን ፡ አሟሽቶ ፡ ወደ ፡ ማሽላ ፡ ጥበቃው ፡ ተነሥቶ ፡ ሄደ ፡ ይባላል ፡



ባለፍየሉም ፡ ባለወተቱም ፡ እንዲሁም ፡ እየተከታተሉ ፡ ሄዱና ፡ ያው ፡ በሬት ፡ ያገኛት ፡ ባለማሽላው ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ቀረ ።

፨ ማናቸውም ፡ ቢሆን ፡ ለሮጠም ፡ ለተሽቀዳደመም ፡ ለቸኰለም ፡ ሳይሆን ፡ ዕድሉ ፡ ለፈቀደለት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚሆነው ።

# የሰው ፡ ገንዘብ ፡ የወሰዱና ፡ ሰው ፡ በግፍ ፡ የገደሉ ፡ ወንበዴዎች ።

በየጊዜው ፡ የግፍ ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያስቀይመው ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። ከነዚህም ፡ አንደኛው ፡ ደገኛ ፡ የሆነውን ፡ ንጹሕ ፡ ሰው ፡ ባልሠራው ፡ ሥራ በግፍ ፡ ገድሎ ፡ ደሙም ፡ በከንቱ ፡ በጉማ፡



ተረሳስቶ ፡ እንዲቀር ፡ ያደረገ ፡ ሲሆን ፡ ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ የሰው ፡ ገንዘብ ፡ አጭበርብሮ ፡ ሰውሮ ፡ የበላ ፡ ነበር ።

ሁለቱም ፡ ግፈኞች ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ ተለዩ ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀንም ፡ የዚያ ፡ የሰውን ፡ ገንዘብ ፡ ሰውሮ ፡ የበላ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ በስልቻ ፡ ቋጥሮ ፡ ተሸክሞ ፡ ወደ ፡ ንግድ ፡ ሄደ ። ብዙ ፡ ቀንም ፡ ሲጓዝ ፡ ከቈየ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻው ፡ ከንዲት ፡ ምንጭ ፡ አጠገብ ፡ ምሳውን ፡ በላና ፡ ሲነሣ ፡ ያንን ፡ ብር ፡ ረስቶት ፡ ሄደ ። ገንዘቡንም ፡ ተላላፊ ፡ መንገደኛ ፡ አንሥቶ ፡ ወሰደው ። ጥቂት ፡ እንደ ፡ ቈየም ፡ ባለገንዘቡ ፡ ዕቃ ፡ መርሳቱ ፡ ትዝ ፡ ብሎት ፡ እየሮጠ ፡ ቢመለስ ፡ የዚያ ፡ በግፍ ፡ ነፍስ ፡ ገድሎ ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ ሲሄድ ፡ ከዚያው ፡ ከምንጭ ፡ አጠገብ ፡ ዐርፎ ፡ ምሳውን ፡ ሲበላ ፡ አገኘው ። እንደ ፡ ደረሰም ፡ አንተ ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ ቦታ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ረስቼ ፡ ሄጄ ፡ ነበረ ፡ እኔ ፡ ታለፍኩ ፡ ወዲህ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ባዚህ ፡ መንገድ ፡ ከቶ ፡ አልተከተለኝም ፡ ወይም ፡ አልፎኝ ፡ አልሄደም ፡ ያንሣኸው ፡ አንተ ፡ ሳትሆን ፡ አትቀርምና ፡ መልስልኝ ፡ አለው ። እሱም ፡ ደንግጦ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠርቶ ፡ አልወሰድኩም ፡ አለው ። ባለገንዘቡ ፡ ግን ፡ ዕውቀቱ ፡ የጸጋ ፡ በመሆኑ ፡ መሐላውን ፡ ሳይቀበለው ፡ ቀርቶ ፡ በጦር ፡ ወግቶ ፡ አሠቃይቶ ፡ ገደለው ።



መሐላውን ፡ ሳይቀበለው ፡ ቀርቶ ፡ በጦር ፡ ወግቶ ፡ አሠቃይቶ ፡ ገደለው ።

ይህም ፡ ስፍራ ፡ ጫካነት ፡ ያለው ፡ የግሑማን ፡ ቦታ ፡ ኖሮ ፡ ሐሩረ ፡ መዓልትን ፡ ቊረ ፡ ሌሊትን ፡ ግርማ ፡ ጽልመትን ፡ ድምፀ ፡ አራዊትን ፡ ታግሦ ፡ ለርዕዮተ ፡ ዐይንም ፡ ተሰውሮ ፡ የሚኖር ፡ አንድ ፡ ባሕታዊ ፡ የተደረገውን ፡

ተመለከተ ። መናኒውም ፡ ይህንን ፡ ሁሉ ፡ የግፍ ፡ ሥራ ፡ አየና ፡ እኔ ፡ ለሁሉም ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ዋጋውን ፡ የምትከፍል ፡ አምላክ ፡ ነህ ፡ ብዬ ፡ ከወገኖቼ ፡ ተለይቼ ፡ እንደዚህ፡ ስደክምና ፡ ስንገላታ ፡ ለከስ ፡ ሰው ፡ ባልሠራው ፡ ሥራ ፡ እንዲሞት ፡ ታደርጋለህ ፤ ባላየው ፡ ባላደረገው ፡ የምታጠፋማ ፡ ከሆንክ ፡ አንተን ፡ ለማገልገል ፡ ምን ፡ ያታክተኛል ፡ ብሎ ፡ በአቱን፡ ለቆ ፡ ለመሄድ ፡ ሲሞክር ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠርቶ ፡ አንተ ፡ ደካማ ፡ ፍጡር፡



አንተ ፡ ደካማ ፡ ፍጡር ፡ እግዚአብሔር ፡ በባሕርይ ፡ ዕውቀቱ ፡ የፈጸመውን ፡ ፍርድ ፡ ትቃወማለህን ፤

እግዚአብሔር ፡ በባሕርይ ፡ ዕውቀቱ ፡ የፈጸመውን ፡ ፍርድ ፡ ትቃወማለህን ፤ ፍጡር ፡ ሆይ ፡ አስተውል ፡ የዚህ ፡ የሚች ፡ ሰው ፡ አባት ፡ ሰው ፡ በግፍ ፡ አስጨንቆና ፡ አሠቃይቶ ፡ ገድሎ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የፍርዱ ፡ ባለቤት ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍዳውን ፡ በልጁ ፡ መክፈሉ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ የዚህ፡ ገንዘብ፡ የጠፋበት ፡ ሰው ፡ አባት ፡ የሰው ፡ ገንዘብ ፡ ሰውሮ ፡ በልቶ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የሱን ፡ ብድር ፡ በልጁ ፡ መፈጸሙ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ አንተ ፡ በማታውቀው ፡ ምዕጢር ፡ የአምላክን ፡ ፍርድ ፡ መቃወም ፡ የለብህምና ፡ ወደ ፡ ቀድሞ ፡ አገልግሎትህ ፡ ተመለስ ፡ ብሎ ፡ ምስጢሩን ፡ አስረድቶ ፡ ወደ ፡ በአቱ ፡ መለሰው ፡ ይባላል ።

ብድር ፡ አይቀር ፡ በምድር ፡ የተባለው ፡ እውነተኛ ፡ መሆኑን ፡ ከተ ገንዘብን ፡ በኋላ ፡ በንጹሓን ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ለሚደረገው ፡ ግፍ ፡ ተበቃዩ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሆኑን ፡ ማመን ፡ ይገባናል ።



# ያንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ምርቃት ።

ባንድ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ግብረ ፡ ገብ ፡ የሆኑ ፡ ብዙ ፡ ልጆች ፡ ያሏቸው ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ነበሩ ።

ሰው ፡ ሆኖ ፡ ዞሮ ፡ ዞሮ ፡ ከቤት ፡ ኑሮ፡ኑሮ ከመሬት ፡ የማይቀር ፡ ስለሆነ፡ በእርጅናቸው ፡ ምክንያት ፡ ጊዜ ፡ ሞታቸው ፡ መቃረቡን ፡ ስለ ፡ ተረዱት ፡ ልጆቻቸውን ፡ ጠርተው ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ የመሰናበቻ ፡ ንግግር ፡ አደረጉ።

ቃሉም ፤ ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ በምፈጽምበት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ትዳሬ ፡ ሳይጐድል ፡ እናንተን ፡ በማግኘቴና ፡ ለቁም ፡ ነገርም ፡ በማብቃቴ ፡ የሚሰማኝ ፡ ደስታ ፡ ወሰን ፡ የለውም ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ እናንተም ፡ ከደረሳችሁልኝ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ በግብረ ፡ ግብነት ፡ ያደረጋችሁልኝ ፡ ርዳታ ፡ ቀላል ፡ ባለመሆኑ ፡ አስተዳደራችንን ፡ በጣም ፡ ደግፎታል ። ስለዚህም ፡ ሞት ፡ ሌባ ፡ ነውና ፡ የሚመጣበት ፡ ሰዓት ፡ ስለማይታወቅ ፡ አስቀድሜ ፡ ተሰናብቻችሁ ፡ እንድቄይ ፡ በማለት ፡ ነው ፡ የጠራኋችሁ ፡ የሚል ፡ ነበር ። ሁሉም ፡ በተርታ ፡ ከፊታቸው ፡ እንደ ፡ ቆሙ ፡ ንግግራቸውን ፡ በመቀጠል ፡ ልጆቼን ፡ በሙሉ ፡ ስለምወዳችሁ ፡ በረከቴ፡ በሁላችሁም ፡ ላይ ፡ ይደር ፡ ፍቅር ፡ ለናንተ ፡ ይሁን ፤ ያለኝንም ፡ ሀብቴንና ፡ ንብረቴን ፡ ሁሉ ፡ እኩል ፡ አድርጋችሁ ፡ ተካፈሉ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ አንዱ ፡ ጣት ፡ ከንዲቱ ፡ እንደምትበልጥ ፡ ለዚህ ፡ ለታላቁ ፡ ወንድማችሁ፡ በተለይ ፡ አገልግሎት ፡ ስላለው ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ምርቃት ፡ እሰጠዋለሁ ። ልጄ ፡ ሆይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለቀደሙ ፡ አባታችንና ፡ እናታችን ፡ ለአዳምና ፡ ሔዋን ፡ ብዝኁ ፡ ወተባዝኁ ፡ ወምልእዋ ፡ ለምድር ፡ ብሎ ፡ የሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ስፈጽም ፡ መዠመሪያ ፡ አንተን ፡ በማግኘቴ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ የተሰማኝ፡ ደስታ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ መቃብር ፡ አይዘነጋኝም ። ከልጆቼ ፡ ቀደም ፡ ብለህ ፡ አእምሮ ፡ ከደረስክበት ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ ያደረግክልኝ ፡ አገልግሎት ፤ ፍጹም ፡ ቅንነት ፡ የተመላበትና ፡ እጅግ ፡ አስደሳች ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ አንደኛ ፡ ብልኀትና ፡ ምክንያት ፡ የሴትን ፡ ሁለተኛ ፡ ጉልበት ፡ የጉንዳንን ፡ ሦስተኛ፡ መብል ፡ የአንበጣን ፡ ይስጥህ ። ከገንዘቤም ፡ የእልቅናህን ፡ የምቀመጥበትን ፡ ግርንቡድ ፡ ውሰድ ፡ ብለው ፡ መረቁት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንግግራቸውን ፡ አቁመው ፡ ሁሉንም ፡ አሰናበቷቸው ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ያ ፡ የበኸር ፡ ልጅ ፡ አባቱ ፡ ጉልበት ፡ የጐን ዳንን ፡ ብልኀትና ፡ ምክንያት ፡ የሴትን ፡ መብል ፡ የአንበጣን ፡ ይስጥህ ፡ ከገ ንዘቤም ፡ የእልቅናህን ፡ የምቀመጥበትን ፡ ግርንቡድ ፡ ውሰድ ፡ ሰጥቼሃለሁ ፡ ያለኝ ፡ ከጐንዳንስ ፡ ያነሰ ፡ ምን ፡ ዐቅም ፡ ኖሮ ፡ ነው ፡ ከሴት ፡ አእምሮ ፡



ብልኀትና ፡ ምክንያት ፡ የሴትን ፡ ጉልበት ፡ የጐ ንዳንን ፡ መብል ፡ የአንበጣን ፡ ከገንዘቤም ፡ የል ቅናህን ፡ የምቀመጥበትን ፡ ግርንቡድ ፡ ውሰድ ፡

የደከመስ ፡ ምን ፡ ተገኝቶ ፡ ነው ፡ መብልስ ፡ የአንበጣን ፡ ያለኝ ፡ ከአንበጣ ፡ ያነሰ ፡ ሆድ ፡ ምን ፡ አለና ፡ ነው ፡ ስለ ፡ እልቅናውስ ፡ ግርንቡድ ፡ ሰጠሁህ ፡ ያለኝ ፡ ደግሞ ፡ ከሱ ፡ ያነሰ ፡ ምን ፡ ዕቃ ፡ ኖሮ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ አዝኖና ፡ ተክዞ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ ወደ ፡ ስደት ፡ ሲሄድ ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡ የተማሩ ፡ አረጋዊ ፡ ቄስ ፡ በመንገድ ፡ አገኘ ። እኒህም ፡ ሽማግሌ ፡ እንዴት ፡ አደርክ ፡ ወንድሜ ፡ ወዴትስ ፡ ትሄዳለህ ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ። እሱም ፡ አባቱን ፡ በቅን ነት ፡ ሳገለግል ፡ ኖሬ ፡ በመጨረሻው ፡ ጉልበት ፡ የጐንዳንን ፡ ብልኀትና ፡ ምክንያት ፡ የሴትን ፡ መብል ፡ የአንበጣን ፡ ይስጥህ ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ረገመኝ ፡ ደግሞ ፡ ከገንዘቤ ፡ ስለ ፡ እልቅናህ ፡ የምቀመጥበትን ፡ ግርንቡድ ፡ ሰጥቼሃለሁ ፡ ስላለኝ ፡ ከሀገር ፡ ተሰድጄ ፡ መሄዴ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ። ቄሱም ፡ ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ አባትህ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ መረቁህ ፡ እንጂ ፡ አልረገሙህም ፡ ስለዚህም ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ እሰጥሃለሁና ፡ ተመለስ ፡ ብለው ፡



ጣደ ፡ ቤታቸው ፡ ይዘውት ፡ ሲጓዙ ፡ ጐንዳን ፡ በለበት ፡ ቀበሌ ፡ ደረሱ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንዱ ፡ ያንዱን ፡ ጐንዳን ፡ ሬሳ ፡ ብቻ ፡ ለብቻ ፡ ተሸክሞ ፡ ሲሮጥ ፡ አይተው ፡ ይኸውልህ ፡ ይህች ፡ ጐንዳን ፡ የጓደኛዋን ፡ ሬሳ ፡ ይዛ ፡ ስትሮጥ ፡ ትመለከታለህን ፡ እስቲ ፡ ትችል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እኔን ፡ ከመሬት ፡ አንሥተህ ፡ ትከሻህ ፡ ላይ ፡ አድርገኝ ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ሬሳ ፡ ዝርግት ፡ ብለው ፡ ተኙ። ለመሸከም ፡ ቢሞክር ፡ ማንሣት ፡ ተሣነው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቄሱ ፡ ያባትህን ፡ ምርቃት ፡ ብትቀበለውና ፡ ቢደርስህ ፡ ኖሮ ፡ አንሥተኸኝ ፡ ትሮጥ ፡ ነበር ፤ ደግሞ ፡ ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ማስረጃ ፡ ልሰጥህ ፡ እችላለሁ ፡ ብለው ፡ ይዘውት ፡ ጣደ ፡ ቤታቸው ፡ ሄዱና ፡ ለሚስታቸው ፡ ይኸውልሽ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ እን ግዳ ፡ ይገፎልሽ ፡ መጣሁ ፡ አሏት ። እሷም ፡ ይህንን ፡ ከመስማቷ ፡ ወዲያው ፡ ምግብ ፡ አሰናድታ ፡ አቀረበችላቸው ። ቀጥሎም ፡ ባበሬ ፡ መጠጥ ፡ ብታ መጣላቸው ፡ ከነገቱ ፡ ካልቀረበ ፡ አይበቃንም ፡ ስላሏት ፡ ወደ ፡ ማጀት ፡ ገባች ። እንግዳው ፡ ሰውዬ ፡ በል ፡ ተከትለህ ፡ ወደ ፡ ጓዳ ፡ ግባና ፡ ጋን ፡ ስታነሣ ፡ ርዳት ፡ ደግሞ ፡ ጐንበስ ፡ ስትል ፡ አይተህ ፡ ድብን ፡ አድርገህ ፡ ቈንጥጣት ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የምታመጣውን ፡ ምክንያት ፡ ታያለህ ፡ ብለው ፡ ከህኑ ፡ በምስጢር ፡ መከሩት ።

እሱም ፡ ተከትሎ ፡ ገባና ፡ የጠላውን ፡ ዕቃ ፡ ለማንሣት ፡ ስታጐነብስ ፡ ድብን ፡ አድርጎ ፡ ቈነጠጣት ፡ ሴቲቱም ፡ ደንግጣ ፡ ቃሏን ፡ አሰምታ ፡ ውይ ፡ ብላ ፡ ጮኸች ። ቄሱ ፡ ምን ፡ ሆንሽ ፡ ብለው ፡ ቢጠይቋት ፡ የማርያምን ፡ ገቾ ፡ አነሣለሁ ፡ ብሎ ፡ ያበን ፡ ጋን ፡ አነሣዋ ፡ ብላ ፡ መለሰችላቸው ። የተፈለገ ውና ፡ የተጠየቀው ፡ ሁሉ ፡ ቀርበ ፡ ግብገሮው ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ እንግዳ ውን ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ሲሸኙት ፡ አየኸተ ፡ ወንድሜ ፡ ይህቺ ፡ ሴት ፡ ድንገት ፡ የመለሰችውን ፡ መልስ ፡ አንተም ፡ ያባትህ ፡ ምርቃት ፡ ቢደርስህ ፡ እንደ ዚሁ ፡ ድንገት ፡ ስትጠየቅ ፡ በቂ ፡ መልስ ፡ ለማግኘት ፡ በቻልክ ። መብል ፡ የአንበጣን ፡ ይስጥህ ፡ ያሉህ ፡ አንበጣ ፡ እፊቱ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ በልቶ ፡ ጤና ፡ ይሆንዋል ፡ አይቈርጠውም ፡ አይፈልጠውም ፤ አንተም ፡ ያባትህ ፡ ምርቃት ፡ ቢደርስህ ፡ የተገኘውን ፡ ጥሬውንም ፡ ብስሉንም ፡ በልተህ ፡ ሙሉ ፡ ጤና ፡ ታገኝ ፡ ነበር ። ስለ ፡ እልቅናህም ፡ መቀመጫዬን ፡ ግርንቡድ ፡ ውሰድ ፡ ሰጥቼሃለሁ ፡ ያሉህ ፤ በውስጡ ፡ ጠቃሚ ፡ ነገር ፡ አኑረውበት ፡ ይሆናል ። ስለ ዚህ ፡ አባትህ ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ አልቀው ፡ መርቀውሃልና ፡ ወደ ፡ ቤትህ ፡ ግባ ፡ ብለው ፡ አስረድተውት ፡ በደስታ ፡ ወዳገሩ ፡ ተመለሰ ። ሄዶም ፡ ያንን ፡ ያባቱን ፡

ግርንቡድ ፡ ቢፈልጠው ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ ስላገኘበት ፡ ቄሱን ፡ አመስግኖ ፡ ያባቱን ፡ ዐፅም ፡ እየመረቀ ፡ በደኅና ፡ ቤቱንና ፡ ንብረቱን ፡ አዘጋጅቶ ፡ ኖረ ፡ ይባላል ።

፨ ልጆች ፡ ሆይ ፡ በውል ፡ መርምሮ ፡ ሳያውቁ ፡ ያባትን ፡ ስጦታና ፡ ምርቃት ፡ ማቃለልና ፡ መንቀፍ ፡ ታላቅ ፡ ኀጢአት ፡ ነው ፤ ደግሞ ፡ ባልተረዱትና ፡ ባልተገነዘቡት ፡ ነገር ፡ በከንቱ ፡ ማማረር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስሕተት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሁሉ ፡ መጠንቀቅ ፡ ይገባል ።

# ያንድ ፡ ኸርብ ፡ ሞት ።

አንድ ፡ አሮጌ ፡ ኸርብና ፡ ልጆቹ ፡ ማንሾለላና ፡ መዝሩጥ ፡ አብረው ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ሲሄዱ ፤ አንድ ፡ ወደል ፡ አህያ ፡ አግኝተው ፡ ተረዳድተው ፡ ዘርጥጠው ፡ ጣሉት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አባትዮው ፡ ልጆቹን ፡ አባሮ ፡ ለብቻው ፡ ይበላ ፡ ዠመር ። በልቶም ፡ ጠገብ ፡ ሲል ፡ ለማንሾለላ ፡ አንድ ፡ ዡሮ ፡ ሰጠው ። ለመዝሩጥ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ሳይሰጠው ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ሲበላ ፡ አባታችን ፡ እረ ፡ ነጋ ፡ አሉት ።



አባትዮው ፡ ልጆቹን ፡ አባሮ ፡ ለብቻው ፡ ይበላ ፡ ዠመር ።



ተዉ ፡ ቄዩ ፡ ግድ ፡ የለም ፡ የጨረቃን ፡ ንጋትና ፡ ያህያን ፡ ሥባት ፡ የማውቅ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ እናንተ ፡ አታውቁም ፡ እያለ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ሲበላ ፡ ነጋ ። ከነጋም ፡ በኋላ ፡ ያህያው ፡ ባለቤት ፡ መጣና ፡ ሲያሳድዳቸው ፡ ልጆቹ ፡ አባታቸውን ፡ ጥለውት ፡ ቀድመው ፡ ሸሹ ።



አባትዮው ፡ ግን ፡ መሮጥ ፡ አቅቶት ፡ ሲንቀረደድ ፡ ያህያው ፡ ባለቤት ፡ ደርሶ ፡ በጦር ፡ ወግቶ ፡ ገደለው ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ኸርብ ፡ ሆዱ ፡ ሞልቶ ፡ መሮጥ ፡ አቅቶት ፡ ዘርገፍ ፡ ዘርገፍ ፡ እያለ ፡ አድነኝ ፡ ልጄ ፡ ማንሾለላ ፡ ቢለው ፡ ምን ፡ ሰጥተኸኝ ፡ ኖሯል ፡ ካንድ ፡ ዡሮ ፡ ሌላ ፡ ብሎት ፡ ሸሽቱን ፡ ቀጠለ ። ሁለተኛውን ፡ ደግሞ ፡ አድነኝ ፡ ልጄ ፡ መዝሩጥ ፡ ቢለው ፡ ምን ፡ ሰጥተኸኛል ፡ አባቴ ፡ እንደ ፡ በላህ ፡ ሩጥ ፡ አለውና ፡ ሁለቱም ፡ ልጆቹ ፡ በባዶ ፡ አንገታቸው ፡ ቀልጥፈው ፡ አመለጡ ። አባትዮው ፡ ግን ፡ መሮጥ ፡ አቅቶት ፡ ሲንቀረደድ ፡ ያህያው ፡ ባለቤት ፡ ደርሶ ፡ በጦር ፡ ወግቶ ፡ ገደለው ፡ ይባላል ።

ብቻውን ፡ የበላ ፡ ብቻውን ፡ ይሞታል ፡ የተባለው ፡ እንዳይደርስባችሁ ፡ ያገኛችሁትን ፡ ከወገናችሁና ፡ ከዘመዶቻችሁ ፡ ጋራ ፡ ተካፈሉት ፤ እሱም ፡ ለናንተ ፡ ሕይወቱን ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣል ።

# ወታደርና ፡ ተማሪ ።

አንድ ፡ ወታደር ፡ ሠንጋ ፡ ፈረስ ፡ ጭኖ ፡ ጠመንዣውን ፡ አንግቶ ፡ በገዳና ፡ ሲገሰግስ ፡ አንድ ፡ ተማሪ ፡ ደበሎውን ፡ ለብሶ ፡ ልብሱን ፡ ባኩፋዳው ፡ ቋጥሮ ፡ ሲሄድ ፡ ደረሰበት ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ወታደሩ ፡ ተማሪውን ፡ ተሜ ፡ ምን ፡ ይዘሃል ፡ ወዴትስ ፡ ትሄዳለህ ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ ጥጥ ፡ መሳይ ፡ መዝኜ ፡ ለናቴ ፡ መውሰዴ ፡ ነው ፡ አለው ። ወታደሩ ፡ በሠንጋ ፡ ፈረሱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሲፈስ ፡ ተማሪው ፡ ብቻውን ፡ እንዳይሆን ፡ እየተከታተለው ፡ ሲሄድ ፡ ውሎ ፡ መሸባቸውና ፡ ወታደሩ ፡ እዚህም ፡ እባካችሁ ፡ አሳድሩኝ ፡ እዚያም ፡ እባካችሁ ፡ አሳድሩኝ ፡ እያለ ፡ በየቤቱ ፡ ሲለምን ፡ እሺ ፡ የሚለው ፡ አጣ ። ተማሪው ፡ ግን ፡ የክት ፡ ልብሱን ፡ ከአኩፋዳው ፡ አውጥቶ ፡ ለብሶ ፡ ጥምጥሙን ፡ ጠመጠመና ፡ በእንተ ፡ ስሟ ፡ ለማርያም ፡ ስለ ፡ ቸሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ የመሸብኝ ፡ መንገደኛ ፡ አሳድሩኝ ፡ ብሎ ፡ ለመናቸው ። እነዚያም ፡ ሰዎች ፡ ወዲያው ፡ አባቴ ፡ ይምጡ ፡ ብለው ፡ አስገቡና ፡ ጐዝጕዘው ፡ የሠንጋ ፡ ቍርበት ፡ በልጋው ፡ ላይ ፡ አንጥፈው ፡ ጠላውን ፡ ከማጀት ፡ ቀድተው ፡ እንጀራውን ፡ ከሌማት ፡ በገበታ ፡ አድርገው ፡ ግብር ፡ ሠሩና ፡ ማዕድ ፡ ይባርኩልን ፡ ብለው ፡ አስባርከው ፡ እራታቸውን ፡ በመልካም ፡ አድርገው ፡ ተጋበዙ ። ያ ፡ ወታደር ፡ ግን ፡ ፈረሱን ፡ ይዞ ፡ ከደጅ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበርና ፡ ተማሪው ፡ ባለቤቶቹን ፡ አሽከሬ ፡ እደጅ ፡ ከብት ፡ ይዞ ፡ ተቀምጧልና ፡ አስገቡልኝ ፡ አላቸው ። ባለቤቱም ፡ ተነሥቶ ፡ ወጥቶ ፡ ፈረሱን ፡ ተቀብሎ ፡ አስገብቶ ፡ ለሰውየው ፡ የተማሪውን ፡ ትርፍራፊ ፡ እንዲበላ ፡ ሰጠው ። ከራትም ፡ በኋላ ፡ ተማሪውን ፡ በመልካም ፡



የዚያን ፡ የተማሪ ፡ ልብስ ፡ በእሳት ፡ እዚያም ፡ እዚያም ፡ እየለኰሰ ፡ ብስትስት ፡ አድርጎ ፡ ተመልሶ ፡ ተኛ ።



ከተነጠፈ ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ አስተኙት ። ወታደሩ ፡ ግን ፡ በአሽከር ፡ ደንብ ፡ ተማሪው ፡ ከተኛበት ፡ ቤት ፡ ከማደያው ፡ ላይ ፡ ትንሽ ፡ ደላን ፡ ተሰጠውና ፡ ያችን ፡ አንጥፎ ፡ ከዚያ ፡ ከደረቀ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ተኛ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንቅልፍ ፡ ሲወስደው ፡ ወታደሩ ፡ ሌሊት ፡ ከተኛበት ፡ ተነሣና ፡ እሱ ፡ እንደዚህ ፡ የተከበረው ፡ በዚህ ፡ በልብሱ ፡ አይደለምን ፡ ብሎ ፡ ከምድጃ ፡ የግራር ፡ ጕልጥምት ፡ ተዳፍኖ ፡ ነበርና ፡ የዚያን ፡



ለካ ፡ ያንተ ፡ ፈረስ ፡ የሚስቀው ፡ የኔን ፡ ልብስ ፡ መቃጠል ፡ እያየ ፡ ኖሯል ፡

የተማሪ ፡ ልብስ ፡ በዚያ ፡ በእሳት ፡ እዚያም ፡ እዚያም ፡ እየለኰሰ ፡ ብስትስት ፡ አድርጎ ፡ ተመልሶ ፡ ተኛ ። ተማሪው ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሲሠራ ፡ ተከናንቦ ፡ ያይ ፡ ነበርና ፡ ወታደሩ ፡ እንቅልፍ ፡ ሲወስደው ፡ ጠብቆ ፡ የሠንጋ ፡ ፈረሱን ፡ ለንጨጭ ፡ በጩቤ ፡ ሙልጭ ፡ አድርጎ ፡ ቈረጠና ፡ ተመልሶ ፡ ተኛ ። ማለዳ ፡ ሲነጋጋም ፡ ቀድም ፡ ብሎ ፡ ተነሥቶ ፡ ያንን ፡ በእሳት ፡ የተቃጠለ ፡ ልብሱን ፡ ለብሶ ፡ በዚያ ፡ በወታደር ፡ ፈረስ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ቆሞ ፡ ዳዊት ፡ ይደግም ፡ ዠመር ። ያም ፡ ወታደር ፡ ከንቅልፉ ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡ መጣና ፡ የፈረሱን ፡ ለንጨጭ ፡ መቀልፈፍ ፡ ሳየይ ፡ ደብተራ ፡ ልብስህን ፡ ምን ፡ እንደዚህ ፡ አቃጠለብህ ፡ አለው ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ተማሪው ፡ እንዳላየ ፡ ሰው ፡ ውይ ፡ ውይ ፡ ለካ ፡ ያንተ ፡ ፈረስ ፡ የሚሥቀው ፡ የኔን ፡ ልብስ ፡ መቃጠል ፡ እያየ ፡ ኖሯል ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ፡ ወታደሩም ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ቢያይ ፡ ፈረሱን ፡ ጥርሱን ፡ አግጦ ፡ ስላገኘው ፡ ራሱን ፡ ይዞ ፡ ጮኸ ፡ ይባላል ።

እግዚአብሔር ፡ በሰጠው ፡ ዕድል ፡ ምቀኛ ፡ መሆን ፡ አይገባም ፡ ቅንነት ፡ እንጂ ፡ ተንኰለኛነት ፡ አይጠቅምም ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ሠሪውን ፡ ከመጕዳት ፡ አይመለስም ።

# ባልና ፡ ሚስትን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንዳታለላቸው ።

ባልና ፡ ሚስት ፡ ሆነው ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሞቱ ፡ ይባላል ። የወለዱትም ፡ ልጅ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ብቻ ፡ ስትሆን ፡ እሷውም ፡ በጣም ፡ ቂልነትን ፡ የምታበዛ ፡ ነበረች ። ትዳር ፡ መያዝም ፡ ስለማይቀር ፡ ባል ፡ አግብታ ፡ ስትኖር ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እናትና ፡ አባቷ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቈይቶ ፡ ባሏ ፡ ወደ ፡ መንገድ ፡ ሲሄድ ፡ አንድ ፡ አታላይ ፡ ሰው ፡ ተጠበብቆ ፡ መጣና ፡ ቤቶች ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዋላችሁ ፡ አለ ። ሴቲቱም ፡ ብቅ ፡ አለችና ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ብላ ፡ ሰላምታ ፡ ከሰጠችው ፡ በኋላ ፡ ወንድሜ ፡ ከወዴት ፡ መጥተሃል ፡ አለችው ። ሰውዮውም ፡ እናትሽና ፡ አባትሽ ፡ ልከውኝ ፡ ነው ፡ አላት ። ምን ፡ ብለው ፡ ላኩህ ፡ ለጤናቸውስ ፡ ደኅና ፡ ናቸውን ፡ ብላ ፡ ብትጠይቀው ፡ ደኅንነቱንስ ፡ ደኅና ፡ ናቸው ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ተራቆቱ ፡ ከልጃችን ፡ ዘንድ ፡ ልብስ ፡ አምጣልን ፡ ብለው ፡ ነው ፡ የላኩኝ ፡ አላት ።

ይህንንም ፡ እንደ ፡ ነገራት ፡ አዬ ፡ ጉድ ፡ ተራቍተውብኛላ ፡ በል ፡ ና ፡ ብላ ፡ ከቤት ፡ አስገብታ ፡ ምሳውን ፡ አብልታ ፡ መጠጥ ፡ አጠጥታ ፡ የባሏን ፡ ሰናፌል ፡ እጀ ፡ ጠባብ ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ የሚለብሰውን ፡ ኩታውን ፡ ጃኖውንና ፡



አዬ ፡ ጉድ ፡ ተራቍተውብኛላ ፡ በል ፡ ና ፡ ብላ ፡ ከቤት ፡ አስገብታ ፡ በስልቻ ፡ ከታ ፡ ሰጠችው ።

ድጉን ፡ ከተቀመጠበት ፡ ማጀት ፡ ከጋን ፡ ውስጥ ፡ አውጥታ ፡ ይኸንን ፡ ላባቱ ፡ ስጥልኝ ፤ ደግሞ ፡ የርሷን ፡ ቀሚስና ፡ ኩታ ፡ መቀነትና ፡ የራስ ፡ ማሰሪያ ፡



ለናቴ ፡ ስጥልኝ ፤ ሰላምታም ፡ እናንተ ፡ እንደምንድናችሁ ፡ እኔ ፡ ጤናዬን ፡ ደኅና ፡ ነኝ ፡ ብለህ ፡ ንገርልኝ ፤ ልብሱንም ፡ አሁን ፡ ቶሎ ፡ ብለህ ፡ አድርስ



እረ ፡ ለነገሩ ፡ ማነው ፡ ስምህ ፡ ስትል ፡ ጠየቀችው ።

ላቸው ፡ ብላ ፡ በስልቻ ፡ ከታ ፡ ሰጠችው ። ወዲያው ፡ እረ ፡ ለነገሩ ፡ ማነው ፡ ስምህ ፡ ስትል ፡ ጠየቀችው ። እሱም ፡ ስሜ ፡ አታለለኝ ፡ ነው ፡ ብሏት ፡ ዕቃውን ፡ ይዞ ፡ ሄደ ። ጥቂት ፡ ቈይቶ ፡ እንዳጋጣሚ ፡ ባሏ ፡ ከሄደበት ፡ መንገድ ፡ መጣ ፤ ወዲያው ፡ ገና ፡ ሳያርፍ ፡ አንቱዬ ፡ ዛሬ ፡ እናቴና ፡ አባቴ ፡ ልብስ ፡ አልቆብናል ፡ ላኪልን ፡ ብለው ፡ መልክተኛ ፡ ስለ ፡ ላኩ ፡ የርስዎን ፡ የክት ፡ ልብስ ፡ ሰናፌልዎንና ፡ ድግዎን ፡ እጀ ፡ ጠባብዎንና ፡ ኩታዎን ፡ እንዲሁም ፡ ጃኖዎን ፡ ላባቴ ፡ የኔን ፡ ቀሚስና ፡ ኩታ ፡ መቀነትና ፡ የራስ ፡ ማሰሪያ ፡ ለናቴ ፡ ሰደድኩላቸው ። ሰላምታም ፡ እናንተ ፡ እንዴት ፡ ናችሁ ፡ እኛ ፡ ደኅና ፡ ነን ፡ ብለው ፡ ልከው ፡ ነበር ፡ አለችው ።

እሱም ፡ ተናደደና ፡ አዬ ፡ ጉድ ፡ ከመቼ ፡ ወዲህ ፡ ነው ፡ የሞተ ፡ ሰው ፡ ልብስ ፡ የሚፈልገው ፡ እንዲያው ፡ ሲያታልልሽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለመሆኑ ፡ በየት ፡ በኩል ፡ ነው ፡ የሄደው ፡ አሳዩኝ ፡ አላት ። እርስዋም ፡ ያውልዎ ፡ በዚያ ፡ በኩል ፡ ነው ፡ አለችው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሡንጋ ፡ ፈረሱን ፡ ጭኖ ፡ ሲጋልብ ፡ አታላዩ ፡ ሰው ፡ እንደሚከተለው ፡ ጠርጥሮ ፡ ኖሮ ፡ ያንን ፡ ልብስ ፡ ከነስልቻው ፡ እቍጥቋጦ ፡ ሥር ፡ ደብቆ ፡ ከዛፍ ፡ ሥር ፡ ቍጭ ፡ ብሎ ፡ ቈየው ።

ፈረሰኛውም ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ወንድሜ ፡ በዚህ ፡ መንገድ ፡ የተቋጠረ ፡ ስልቻ ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ሲሄድ ፡ አላየህምን ፡ አለው ። እሱም ፡ በዚህ ፡ ሽለቆ ፡ ወደ ፡

ታች፡ወረደልህ፡መንገዱ፡ግን፡ለከብት፡አይመችም፡ሲል፡መለሰለት። የቱናደደውም፡ሰው፡እውነት፡መስሎት፡እንግዲያውስ፡በድፍረቱ፡ይቅርታ፡አድርግልኝና፡ደርሼ፡እስክመለስ፡ይህንን፡ፈረስ፡ያዝና፡ቈየኝ፡ብሎ፡ለመነው። እሱም፡ብቻ፡ቶሎ፡ናልኝ፡እንጂ፡ለመያዙ፡ግድ፡የለም፡እሺ፡ስጠኝ፡አለና፡ፈረሱን፡ተቀበለው። ከመለያየታቸውም፡በፊት፡ወንድም፡ምናልባት፡አገኘውና፡ስንጨቃጨቅ፡ትንሽ፡ያቈየሁህ፡እንደ፡ሆነ፡ማን፡ብዬ፡ልጥራህ፡ብሎ፡ጠየቀው። አታላዩም፡ስሜ፡"ያሁኑ፡ይባስ"፡ነው፡ያሁኑ፡ይባስ፡ያሁኑ፡ይባስ፡ብለህ፡ጥራኝ፡አለው።



እሱም፡በዚህ፡ሸለቆ፡ወደ፡ታች፡ወረደልህ፡ሲል፡መለሰለት።

ከዚያ፡በኋላ፡በዚያ፡ሥርጥ፡ሲወርድለት፡ያንን፡ልብስ፡ከደበቀበት፡ቍጥቋጦ፡ውስጥ፡አውጥቶ፡ከፈረሱ፡ላይ፡ተቀምጦ፡እየኰረኰረ፡ሽምጦ፡ሄደ። የልብሱም፡ባለቤት፡በሥርጡ፡ቢወርድ፡የተባለውን፡ሰው፡ሳያገኘው፡ቀረ። ተመልሶ፡ቢመጣም፡ባላደረው፡ፈረሱን፡ይዞበት፡ጠፋ። እረ፡ያሁኑ፡ይባስ፡እረ፡ያሁኑ፡ይባስ፡እያለ፡ቢጣራም፡ከወዴት፡ያግኘው! ከልብሱ፡ጥፋት፡ይልቅ፡ፈረሱንም፡አስወስዶ፡አተርፍ፡ባይ፡አጕዳይ፡ሆኖ፡ሁሉንም፡አጥቶ፡በዶ፡እጁን፡ተመልሶ፡እቤቱ፡ገባ፡ይባላል።

ምንም፡ሲትዮዋ፡እጅግ፡ከልክ፡ያለፈ፡የዋህ፡ብትሆን፡ወንድየውም፡ተሞኝቷል። አያድርስ፡ነው፡እንጂ፡ከቶ፡ሰው፡ሆኖ፡መታለል፡አይቀርም።



# የዥብ፡ልጅ፡ሞት።

ዥብ፡ልጁ፡ሞተበትና፡ለነእንኰዬ፡አህዮት፡ልጄ፡ሞቷልና፡አላቅሱኝ፡ሲል፡መርዶ፡ነጋሪ፡ላከ።

ተረጅዎቹም፡እንግዲህ፡ሰምተን፡ብንቀር፡ይጣላናል፡ብንሄድም፡ይበላናል፤ እንዴት፡ብናደርግ፡ይሻላል፡በማለት፡ምክር፡ዠመሩ። ነገር፡ግን፡ቀርተን፡ከሚጣላን፡ሄደን፡ቢበላን፡ይሻላል፡ብለው፡ተነሥተው፡ልብሳቸውን፡አሸራርጠው፡ሄዱ።

ከለቅሶውም፡ቦታ፡እንደ፡ደረሱ፡አንደኛዋ፡ብድግ፡ኣለችና፡
ምን፡ዐጥንት፡ቢሆን፡ይሰብራል፡ጥርስዎ፤
ምን፡ጨለማ፡ቢሆን፡እሾኽ፡አይወጋዎ፤
ምን፡ጥቍር፡ቢበሉ፡ነጭ፡ነው፡ኵስዎ፤
ያንን፡ጐሬ፡ዞሮ፡ይሰማል፡ድምጥዎ፤
አሁን፡የርስዎን፡ልጅ፡ምን፡አገኘብዎ፤
እያለች፡ሙሾ፡ታወርድ፡ዠመር።

እሱ፡ደግሞ፡ቀበል፡አለና፤ አንችስ፡ደግ፡ብለሻል፤
መልከም፡አልቅሰሻል፤
ይህ፡ሁሉ፡አዘንተኛ፡ምን፡ይብላ፡ብለሻል፡
ሲል፡መለሰ።

እንዳልማራቸው፡በወቂ፡ጊዜ፡እንግዲህ፡አለቀቀንም፡ምን፡ማድረግ፡ይሻለናል፡ብለው፡እነእንኰዬ፡አህዮት፡ምክር፡ዠመሩ። አንዲት፡እናቷ፡የሞተችበት፡ውርንጭላ፡ከነርሱ፡ጋር፡ነበረችና፡ይህችን፡እንስጥና፡እንገላገል፡ብለው፡ሲነጋገሩ፡ግልገሏ፡አህያ፡ሰምታ፡ምነው፡እኔ፡ውርንጫ፡ማ—ይዞኝ፡በሩጫ፡ብላ፡ተነሥታ፡እልም፡አለች።

ከዚህ፡በኋላ፡ጭንቅ፡ያዛቸውና፡መቼስ፡ምን፡ይደረግ፡ለንበጫችንን፡ሰጥተነው፡እንሂድ፡ብለው፡ተማከሩ። ወዲያው፡በል፡እንግዲህ፡የላይ፡የላይ፡ለንበጫችንን፡ውሰድ፡አሉት። እሱም፡እንዳመለከቱት፡ለንጨጭ፡ለንጨጫቸውን፡ገንጣጠለና፡ለቀቃቸው።

በሦስተኛው፡ቀን፡ደግሞ፡እስቲ፡ዛሬ፡ማልስቱ፡ነውና፡እመቃብሩ፡ላይ፡ደርሰን፡አያ፡ዥቦን፡ጠይቀን፡እንምጣ፡ብለው፡ቢሄዱ፡አያ፡ዥቦ፡ቀድሞ፡ከመቃብሩ፡ላይ፡ሲያለቅስ፡ደረሱ።

አያ ፡ ኽቦም ፡ ድዳቸውን ፡ ገልፍጠው ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ ለክ ፡ የኔ ፡ ሐዘን ፡ ለናንተ ፡ ሰርግና ፡ ምላሽ ፡ ሆኖላችኋልና ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ ትላንትና ፡ ሞቶ ፡



በል ፡ እንግዲህ ፡ የላይ ፡ የላይ ፡ ለንበጫችንን ፡ ውሰድ ፡ አሉት ።

ዛሬ ፡ እናንተ ፡ እየተሳሳቃችሁ ፡ የመጣችሁት ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ተቈጣና ፡ ለወገኖቹ ፡ እረ ፡ በሉ ፡ አንድ ፡ አንድዋን ፡ እየዘረጠጣችሁ ፡ ጣሉልኝ ፡ አላቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የኽብ ፡ ወገን ፡ ያህያን ፡ ልጅ ፡ እየገነጣጠለ ፡ ጣለ ፡ ይባላል ።



የኔ ፡ ልጅ ፡ ትላንትና ፡ ሞቶ ፡ ዛሬ ፡ እናንተ ፡ እየተሳሳቃችሁ ፡ የመጣችሁት ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡

፨ ባላጋራን ፡ ቆቅ ፡ ሆኖ ፡ ካልቈዩት ፡ ምንም ፡ ቢለማመጡት ፡ ማጥቃቱን ፡ አይተውም ። አያ ፡ ኽቦ ፡ ሳታመኻኝ ፡ ብላኝ ፡ የተባለውም ፡ ይህ ፡ ነው ።



# ሚስቱ ፡ የጕሽ ፡ ወተት ፡ አምጣ ፡ ስላለችው ፡ ሰው ።

ሥራው ፡ ግብርና ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሚስቱ ፡ ከወዳጅዋ ፡ ጋራ ፡ ቀጠሮ ፡ አድርጋ ፡ ኖሮ ፡ ባሏን ፡ ዐይኔን ፡ በብርቱ ፡ አሞኛልና ፡ መድኀኒቱ ፡ የጕሽ ፡ ወተት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ስለ ፡ ነገሩኝ ፡ ይህንኑ ፡ ፈልገህ ፡ አምጣልኝ ፡ ብላ ፡ አስጨንቃ ፡ ያዘችው ።

የዋሁ ፡ ገበሬም ፡ የታመመች ፡ መስሎት ፡ ተነሥቶ ፡ ሊፈልግ ፡ ሲሄድ ፡ አንድ ፡ መነኰሴ ፡ እመንገድ ፡ አገኙትና ፡ ወዴት ፡ ትሄዳለህ ፡ ልጄ ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ። እሱም ፡ ሚስቴ ፡ በድንገት ፡ ዐይኔን ፡ በጠና ፡ ታምሚያለሁና ፡ የጕሽ ፡ ወተት ፡ መድኀኒት ፡ ነው ፡ ስላሉኝ ፡ ከምትገባበት ፡ ገብተህ ፡ አምጣልኝ ፡ ብላኝ ፡ ልፈልግ ፡ እሄዳለሁ ፡ ሲል ፡ መለሰላቸው ። መነኰሴው ፡ ነገሩ ፡ የተንኰል ፡ መሆኑን ፡ በመንፈስ ፡ ስለ ፡ ተረዱት ፡ ይህ ፡ ከሆነማ ፡ ዕዳው ፡ ቀላል ፡ ነው ፤ ወደ ፡ ቤትህ ፡ እንመለስ ፡ መድኀኒቱንም ፡ እኔ ፡ አሳይሃለሁ ፡ አሉት ። እሺ ፡ ብሎ ፡ ከሰፈሩ ፡ ሲደርስ ፡ በሩቅ ፡ ቤቴ ፡ ያ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ነገራቸው ። እንግዲያውስ ፡ ቈይ ፡ ብለው ፡ እሱን ፡ በስልቻ ፡ ከተው ፡ በትከሻቸው ፡ ተሸክመው ፡ ከቤት ፡ ደረሱና ፡ እባካችሁ ፡ አሳድሩኝ ፡ ብለው ፡ ለመኑ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የተሸከሙት ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ ብቅ ፡ አለችና ፡ አባቴ ፡ ደኅና ፡ ውለዋል ፡ ምን ፡ ተሸክመዋል ፡ አለቻቸው ። መነኰሴውም ፡ የታቦት ፡ ዕቃ ፡ ዳውላ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መለሱላት ። ከቤት ፡ አገባቻቸውና ፡ መብራት ፡ ላብራልዎ ፡ ብትላቸው ፡ አይሆንም ፡ የታቦት ፡ ዕቃዩ ፡ ይታይብኛና ፡ ሌባ ፡ መጥቶ ፡ ይሰርቀኛል ፤ ከጨለማ ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ ይገር ፡ የምቀመጠው ፡ አሏት ። እንግዲያውስ ፡ ያውልዎ ፡ ብላ ፡ ከጓዳ ፡ ቦታ ፡ ሰጠቻቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ለወዳጅዋ ፡ የታረደ ፡ ሙክትና ፡ የተጠመቀ ፡ ጠላ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤ ከጠላውም ፡ ከሥጋውም ፡ አድርጋ ፡ እዚያው ፡ እተቀመጡበት ፡ ጨለማ ፡ ውስጥ ፡ እራታቸውን ፡ ሰጠቻቸው ። መነኰሴውም ፡ ስልቻውን ፡ ፈተው ፡ ያንን ፡ ሥጋና ፡ ጠላ ፡ ከጓደኛቸው ፡ ጋራ ፡ ከበሉና ፡ ከጠጡ ፡ በኋላ ፡ አባቴ ፡ እስቲ ፡ ዘፈን ፡ ያምጡ ፡ እንጫወት ፡ አለቻቸው ።

እሳቸውም ፡ ልጄ ፡ እስቲ ፡ ካንቺ ፡ ይጀመር ፡ ሲሉ ፡ መለሱላት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እጕሽ ፡ የሄደው ፡ ወዲያው ፡ በቀረው ፡ እጕሽ ፡ የሄደው ፡ ወዲያው ፡ በቀረው ፡ እያለች ፡ ትዘፍን ፡ ጀመር ።

መነኮሴውም ፡ ቀበል ፡ አሉና ፡ ይኸንን ፡ ጉባኤ ፡ ስማ ፡ ዳውላዬ ፡ ይኸንን ፡ ጉባኤ ፡ ስማ ፡ ዳውላዬ ፡ እያሉ ፡ እያወረዱ ፡ ሲጫወቱ ፡ አመሹ ።

በመኝታ ፡ ሰዓት ፡ እርሷ ፡ ወጻጅዋን ፡ ይዛ ፡ ከልጋዋ ፡ ላይ ፡ ተኛች ። ሌሊት ፡ እንቅልፍ ፡ ይዟቸው ፡ ሳለ ፡ ያ ፡ ባሏ ፡ ተነሥቶ ፡ የሚስቱን ፡ ወጻጅ ፡ አንገቱን ፡ በክራ ፡ ቈርጦ ፡ ጭንቅላቱን ፡ እድፍድፍ ፡ ውስጥ ፡ ጨምሮ ፡ ሄደ።



አባቱ ፡ እስቲ ፡ ዘፈን ፡ ያምጡ ፡ እንጫወት ፡ አለቻቸው ።

ሴቲቱ ፡ ከእንቅልፏ ፡ ስትነቃ ፡ ወጻጅዋን ፡ ብትዳብሰው ፡ ራሱን ፡ አጣችው ። እኛን ፡ መነኮሴ ፡ አባ፡ አባ ፡ ብላ ፡ ጠርታ ፡ ወይ ፡ ቢሏት ፡ እረ ፡ ይኸ ፡ ማታ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ የተኛው ፡ ሰው ፡ አንገት ፡ የለውም ፡ ኖሯል ፡ ወይ ፡ ብላ ፡ ጠየቀቻቸው ። እርሳቸውም ፡ ልጄ ፡ ካንገትም ፡ አንገት ፡ መቃ ፡ የመሰለ ፡ አሏት ። እንግዲያውስ ፡ ሰው ፡ ሳያይ ፡ ሳይሰማ ፡ ከዚህ ፡ ላጥፋ ፡ ብላ ፡ ያንን ፡ ሬሳ ፡ ጐትታ ፡ ወስዳ ፡ እጉድፍ ፡ ቀበረችው። መነኮሴውም ፡ ጧት ፡ ተነሥተው ፡ ዳውላቸውን ፡ ቢያዩ ፡ ባዶ ፡ ሆነባቸው ፡ እንደ ፡ ፈራሁት ፡ የታበት ፡ ዕቃዬን ፡ አሰረቅሽብኝ ፡ አ ፡ አ ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ ቢሏት ፡ እባክዎ ፡ አይጩኹ ፡ እኔ ፡ እከፍላለሁ ፡ ብላ ፡ ከቤቷ ፡ በድብኝት ፡ ያላትን ፡ ሸማ ፡ ሁሉ ፡ በስልቻቸው ፡ ከታላቸው ፡ ይዘው ፡ ሄዱ ።

ባሏም ፡ በማግስቱ ፡ መጣና ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ውለሽ ፡ አደርሽ ፡ በጎ ፡ ሆንሽን ፡ ብሎ ፡ ጠየቃት ። እሷም ፡ ያላወቀባት ፡ መስሏት ፡ ደግ ፡ ነኝ ፡ ዛሬ ፡ ቀለል ፡ ብሎኛል ፡ አለችው ።



ጥቂት ፡ ቈይቶ ፡ ሴቲቱ ፡ ከምድጃ ፡ ምንቸት ፡ ጥዳ ፡ ነበርና ፡ ያ ፡ ምንቸት ፡ ሲር ፡ ሲር ፡ ሲል ፡ ሰምቶ ፡ አንቺ ፡ እረ ፡ ይኸ ፡ የጣድሽው ፡ ማሰሮ ፡ ምነው ፡ አንገት ፡ እድፍድፍ ፡ ሬሳ ፡ እጉድፍ ፡ ይላልሳ ፡ እስቲ ፡ የድፍድፉን ፡ ጋን ፡ እዪው ፡ አላት ። ቶሎ ፡ ተነሣችና ፡ ያንን ፡ የድፍድፍ ፡ ጋን ፡ ከፍታ ፡ እጅዋን ፡ ብታገባ ፡ ጭንቅላት ፡ ከውስጡ ፡ አገኘችና ፡ ገሮውን ፡ ይዛ ፡ ብቅ ፡ አደረገችው ። ደግሞ ፡ ሬሳ ፡ እጉድፍ ፡ ይላል ፡ እስቲ ፡ እደጅ ፡ ወጥተሽ ፡ ከጥራጊ ፡ ማፍሰሻ ፡ ያለውን ፡ ጉድፍ ፡ ተመልከቺ ፡ ቢላት ፡ ባስቀመጠችበት ፡ ሄዳ ፡ የቀበረችውን ፡ ሬሳ ፡ አወጣች። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እሱ ፡ ይህንን ፡ ነገር ፡ ሰው ፡ የሰማብን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዳንወረስ ፡ መጫኛ ፡ አምጪና ፡ ገደል ፡ ጥለነው ፡ እንምጣ ፡ ብሎ ፡ ያንን ፡ ሬሳና ፡ አንገት ፡ ባቀረበችለት ፡ መጫኛ ፡ ጥፍር ፡ አድርጎ ፡ አስሮ ፡ እዠርባዋ ፡ ላይ ፡ አሳዝሎ ፡ ሄደው ፡ ከገደል ፡ አፋፍ ፡ ሲደርሱ ፡ የወደድሽው ፡ ነው ፡ አትለዪው ፡ ብሎ ፡ ባንድነት ፡ ገደል ፡ ሰዷቸው ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመለሰ ፡ ይባላል ።



ከገደል ፡ አፋፍ ፡ ሲደርሱ ፡ የወደድሽው ፡ ነው ፡ አትለዪው ፡ ብሎ ፡ ባንድነት ፡ ገደል ፡ ሰዷቸው ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመለሰ ።

፨ ሚስት ፡ ለባሏ ፡ ባልም ፡ ለሚስቱ ፡ ታማኝ ፡ ሆነው ፡ መገኘት ፡ ይገባቸዋል ። በየዋሁ ፡ ባልደረባችሁ ፡ ተንኰል ፡ ብታስቡ ፡ ትጠፋላችሁና ፡ ክፋትን ፡ ከላያችሁ ፡ አርቃችሁ ፡ አስወግዱት ።

# ሁለት ፡ ሌቦች ።

ጓደኛ ፡ ሆነው ፡ አብረው ፡ ሲሰርቁ ፡ የሚኖሩ ፡ ሁለት ፡ ሌቦች ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከመንገድ ፡ ዳር ፡ ተቀምጠው ፡ ሲጨዋወቱ ፡ አንድ ፡ ባላገር ፡ ለግብር ፡ ቃዘ ፡ ማር ፡ በገንቦ ፡ ተሸክሞ ፡ ሙክት ፡ እየሳበ ፡ ሲመጣ ፡ አዩት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ለመንጠቅ ፡ ተማከሩ ፡ አንዱ ፡ ሌባ ፡ ተነሥቶ ፡ እጫካ ፡ ገባ ። ሁለተኛው ፡ ግን ፡ እዚያው ፡ እመንገድ ፡ ዳር ፡ ዐይነ ፡ ስውር ፡ መስሎ ፡ ጥቅልል ፡ አለና ፡ ተኛ ።

ያ ፡ ባላገር ፡ ሙክቱን ፡ እየሳበ ፡ ማሩን ፡ በዕቃ ፡ ተሸክሞ ፡ አጠገቡ ፡ ሲደርስ ፡ ሌባው ፡ አየና ፡ ስለ ፡ ቸሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡ አትለፈኝ ፡ የቀን ፡ ጨለማ ፡ የወረሰኝ ፡ ነኝና ፡ እየመራኸኝ ፡ ሂድ ፡ ብሎ ፡ ለመነው ። እሱም ፡ እኔ ፡ ለግብር ፡ ቶሎ ፡ አድርስ ፡ ተብዬ ፡ ቃዝገሬ ፡ ሙክት ፡ እስባለሁ ፡ ማር ፡ ተሸክሚያለሁ ፡



አጠገቡ ፡ ሲደርስ ፡ ስለ ቸሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡ አትለፈኝ ፡ የቀን ፡ ጨለማ ፡ የወረሰኝ ፡ ነኝና ፡ እየመራኸኝ ፡ ሂድ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ።



አንተን ፡ እንዴት ፡ አድርጌ ፡ ነው ፡ የምይዝህ ፡ ቢለው ፡ አንተ ፡ እኔን ፡ ከያዝከኝ ፡ የሙክቱን ፡ መሳቢያ ፡ ገመድ ፡ ሰጥተኸኝ ፡ እኔ ፡ እስበዋለሁ ፡ አለ።

ሰውዬውም ፡ የዋህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ነበርና ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ የመሳቢያውን ፡ ገመድ ፡ ለዐይነ ፡ ስዉሩ ፡ አስጨብጦ ፡ እርሱ ፡ ደግሞ ፡ የሌባውን ፡ እጅ ፡ ይዞ ፡ ጕዞ ፡ ዠመሩ ። ጥቂት ፡ እንደ ፡ ሄዱና ፡ ከጫካ ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ ጓደኛው ፡ በኋላ ፡ ደርሶ ፡ መሳቢያውን ፡ ገመድ ፡ ፈትቶ ፡ ሙክቱን ፡ ወሰደው ። ሲሄዱ ፡ ሲሄዱ ፡ ቈይተው ፡ ሳለ ፡ ዓይነ ፡ ስውሩ ፡ ወንድሜ ፡ ምነው ፡ ገመዱ ፡ ቀለለብኝ ፡ እስቲ ፡ ሙክቱን ፡ እይልኝ ፡ አለው ።



ጥቂት ፡ እንደ ፡ ሄዱና ፡ ከጫካ ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ ጓደኛው ፡ በኋላ ፡ ደርሶ ፡ መሳቢያውን ፡ ገመድ ፡ ፈትቶ ፡ ሙክቱን ፡ ወሰደው ፡

ይኸም ፡ የዋህ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ዞወር ፡ ብሎ ፡ ቢያይ ፡ ሙክቱ ፡ የለም ። ማሩን ፡ ከትከሻው ፡ አውርዶ ፡ እንካ ፡ በጅህ ፡ ይዘህ ፡ ጠብቅልኝ ፡ እኔ ፡ ተመልሼ ፡ ሙክቱን ፡ ልፈልግ ፡ አለውና ፡ ሄደ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ሌባ ፡ ደግሞ ፡ ማሩን ፡ ተሸክሞ ፡ እልም ፡ አለ ። ያንን ፡ የዋህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ተንኰል ፡ እነዚህ ፡ ሁለት ፡ አታላዮች ፡ ሁሉንም ፡ ቀምተው ፡ ሰደዱት ።

፨ ውስጡን ፡ ሳትመረምርና ፡ ጠባዩን ፡ ሳታውቅ ፡ እምነትህን ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ አትጣል ።

# አንድ ፡ በሬ ፡ ስለ ፡ ነበራቸው ፡ ቂሎች ፡ ባልና ፡ ሚስት ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ኑሯቸውን ፡ ሲወያዩ ፡ ሴትዮዋ ፡ ለባሏ ፡ ችግርና ፡ ረኃብ ፡ ጸናብን ፡ ይኸንን ፡ በሬያችንን ፡ አርደን ፡ እንብላው ፡ ብላ ፡ አሳሰበችው ። ባሏም ፡ እውነትሽ ፡ ነው ፡ እንረደው ፡ አላት ። ሁለቱም ፡ በሐሳቡ ፡ ስለ ፡ ተስማሙ ፡ በሬውን ፡ ከዛፍ ፡ ሥር ፡ አርደው ፡ ብልት ፡ ሲያወጡ ፡ አሞራ ፡ እየመጣ ፡ አንዳንዱን ፡ ሙዳ ፡ እየያዘው ፡ ይሄድ ፡ ጀመረ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እሱ ፡ የወሰድከው ፡ ሥጋ ፡ የብር ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ያዙ ። ደግሞ ፡ ጭልፊቶች ፡ ሥጋው ፡ ስለ ፡ ጣማቸው ፡ እየተመላለሱ ፡ በጥፊ ፡ እያነጎዱ ፡ ቅንጥብጣቢ ፡ ሲነጥቁ ፡ እኛ ፡ ነግረናል ፡ አሁን ፡ የወሰዳችሁት ፡ የብር ፡ ነው ፡ ዐውቃችሁ ፡ ግቡበት ፡ ይምሩናል ፡ ብላችሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አታስቡ ፡ በማለት ፡ ሲወተውቱ ፡ ከቈዩ ፡ በኋላ ፡ ቈዳውን ፡ ገፈው ፡ ሲያበቁ ፡ የተረፈውን ፡ ሥጋ ፡ በጋን ፡ ቀቅለው ፡ በመግላሊት ፡ ከድነው ፡ እንግዲህ ፡ ስንበላ ፡ እጥርሳችን ፡ የሚገባውን ፡ ለመጐርጐሪያ ፡ ስንደዶ ፡ አጭደን ፡ እናምጣ ፡ ብለው ፡ የቤታቸውን ፡ ጭራሮ ፡ መዝጊያ ፡ መለስ ፡ አድርገው ፡ ማጭድና ፡ መጫኛ ፡ ይዘው ፡ ሁለቱም ፡ ተያይዘው ፡ ከቤት ፡ ወጡ ። ወዲያው ፡ በዚያው ፡ መንገድ ፡ ባጠገባቸው ፡ ብዙ ፡ ወታደሮች ፡ ተፍ ፡ ተፍ ፡ እያሉ ፡ መጡ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እናንተ ፡ ጎበዞች ፡ ሰማችሁ ፡ በዚህ ፡ በምትሄዱበት ፡ መንገድ ፡ አጠገብ ፡ በጭራሮ ፡ መዝጊያ ፡ የተዘጋ ፡ ቤት ፡ አለና ፡ እኛ ፡ በሬያችንን ፡ አርደን ፡ ሥጋውን ፡ በጋን ፡ ቀቅለን ፡ በመግላሊት ፡ ከድነን ፡ ከወፍጮም ፡ ላይ ፡ ዳቦ ፡ በሌማት ፡ አስቀምጠን ፡ ለጥርሳችን ፡ መጐርጐሪያ ፡ ስንደዶ ፡ ለማጨድ ፡ መጥተናል ፡ በዚያ ፡ ስታልፉ ፡ እንዳትነኩብን ፡ ብለው ፡ ነገሯቸው ። መንገደኞቹም ፡ ይህንን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ገሥግሠው ፡ ሄደው ያንን ፡ የጭራሮ ፡ መዝጊያ ፡ ከፍተው ፡ ሥጋውን ፡ እደቅ ፡ ላይ ፡ እያወጡ ፡ በልተው ፡ ከጠገቡ ፡ በኋላ ፡ ዐጥንቱን ፡ መልሰው ፡ እጋኑ ፡ ውስጥ ፡ ጨምረው ፡ መግላሊቱን ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ከደኑት ። በሌማት ፡ የነበረውንም ፡ ዳቦ ፡ እየተከፋፈሉ ፡ በጭብጦ ፡ መያዣቸው ፡ ከቋጠሩ ፡ በኋላ ፡ ጭራሮ ፡ መዝ



ጊያውን ፡ መለስ ፡ አድርገው ፡ ተነሥተው ፡ መንገዳቸውን ፡ ቀጠሉ ።

ወታደሮቹም ፡ በዝብዘው ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ ባልና ፡ ሚስቱ ፡ ስንደዶቸውን ፡ ተሸክመው ፡ መጡና ፡ ቤታቸውን ፡ ከፍተው ፡ ቢገቡ ፡ መግላሊቱ ፡ ተንከርፍፎ ፡ ዝንቡ ፡ እቤት ፡ ባለው ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ በጋኑም ፡ በዋዲያቱም ፡ በአፍላሉም ፡ በበገፈጁም ፡ ዳቦ ፡ በነበረበት ፡ ሌማትም ፡ እቤት ፡ ባለው ፡ ደጃፍ ፡ በመለሰውና ፡ ማጀት ፡ በጐረሠው ፡ በማናቸውም ፡ ላይ ፡ ሰፍሮበት ፡ አዩ ። መግላሊቱን ፡ ከጋኑ ፡ ቢያነሡት ፡ ዝንቡ ፡ እው ፡ እያለ ፡ ከውስጡ ፡ ይወጣ ፡ ጀመር ። እጃቸውንም ፡ አግብተው ፡ ቢዳብሱት ፡ አጥንቱ ፡ ብቻ ፡ ቃጥሮ ፡ ሥጋው ፡ ተበልቶ ፡ አገኙት ። ሥጋችንን ፡ የበላብን ፡ ይኸ ፡ ዝንብ ፡ አይደለምን ፡ እንክሰሰው ፡ ብለው ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ዳኛ ፡ ሄደው ፡ አቤት ፡ አቤት ፡ እያሉ ፡ ጮኹ ። ዳኛውም ፡ ምነው ፡ ምን ፡ ሆናችሁ ፡ ምንስ ፡ ተበድላችሁ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ጠየቃቸው ። እነሱም ፡ ጌታችን ፡ ሆይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሳይዎ ፡ መልአኩ ፡ ይንገርዎ ፡ በሬያችንን ፡ አርደን ፡ ሥጋውን ፡ በጋን ፡ ቀቅለን ፡ በመግላሊት ፡ ከድነን ፡ ዳቢችንንም ፡ በሌማት ፡ አኑረን ፡ ቤታችንን ፡ ዘግተን ፡ ለጥርሳችን ፡ መጐርጐሪያ ፡ ስንደዶ ፡ ለማጨድ ፡ ሄደን ፡ ተመልሰን ፡ ብንመጣ ፡ ዝንብ ፡ ዐጥንቱ ፡ ብቻ ፡ እስኪቀር ፡ ሥጋውን ፡ በልቶ ፡ ዳቢችንን ፡ ጨርሶ ፡ አገኘነው ። የንቀቱ ፡ ንቀት ፡ የድፍረቱ ፡ ድፍረት ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጥፋት ፡ በኋላ ፡ ከቤታችን ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ ሰፍሮ ፡ ቈየን ። እኛንም ፡ አይቶ ፡ ትንሽ ፡ እንኳ ፡ ደንገጥ ፡ አላለም ። ዝም ፡ ብሎ ፡ የተረፈውን ፡ ይበላል ፡ አሉት ። ዳኛውም ፡ የዚህ ፡ ፍርድ ፡ አስቸጋሪ ፡ አይደለም ፡ ሄዳችሁ ፡ ያለውን ፡ ዝንብ ፡ ሁሉ ፡ ፍጁት ፡ በገዛ ፡ ቤታችሁና ፡ በገዛ ፡ ሥጋችሁ ፡ ዝም ፡ በሉ ፡ አልልም ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ ይህንን ፡ ፍርድ ፡ ተቀብለው ፡ እጅ ፡ ነሥተው ፡ ተመለሱ ።

ከቤታቸውም ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ ባለቤቱ ፡ ፈጥኖ ፡ ቈመጡን ፡ አንሥቶ ፡ ዝንብ ፡ ለመግደል ፡ ሲሰነዝር ፡ ጋኑን ፡ ከነመግላሊቱ ፡ ብትንትን ፡ አደረገው ። ደግሞ ፡ ከዋዲያቱ ፡ ላይ ፡ ያረፈውን ፡ ሊገድል ፡ ሽመሉን ፡ ቢያውዘገዝገው ፡ ዋዲያቱን ፡ ጣባውን ፡ ጕልቻውንም ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ እንክትክት ፡ አደረገው ።

እማጀትም ፡ ገብቶ ፡ መኽረጃንም ፡ አፍላሉንም ፡ ዶሙውንም ፡ ቻቹ
ንም ፡ አደቀቀው ፡ ዳግመኛ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ መለስ ፡ ቢል ፡ ከበገሬጁ ፡ ላይ ፡
አንድ ፡ ዝንብ ፡ አርፋ ፡ አየ ። ዝግ ፡ ብሎና ፡ አድብቶ ፡ ቈመጡን ፡ ቢያው
ዘገዝገው ፡ ይኸነንም ፡ እንኩትኩት ፡ አድርጎ ፡ ጣለው ። ዝንቡ ፡ ግን ፡ አም
ልጦ ፡ እሞግዱ ፡ ላይ ፡ አርፎ ፡ ነበር ፡ ተከታትሎ ፡ ወዲያው ፡ ሞግዱንም ፡
ከነምጣዱ ፡ ሰባበረው ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ የተሰቀሉትን ፡ ያደስ ፡ የድልህና
የሽሮ ፡ ቅሎችን ፡ ኩስኩስቱን ፡ ደቂንም ፡ በቤት ፡ ያለውን ፡ ማናቸውንም
ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ ሰብሮ ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ዝንብ ፡ ከሚስቱ ፡ ግንባር
ላይ ፡ አረፈች ። እሷም ፡ ጩራሮ ፡ አንሥታ ፡ እመታለሁ ፡ ስትል ፡ ብር ፡ ብላ
አመለጠቻት ። በዚህም ፡ ተናዳ ፡ ሳለች ፡ ሌላዋ ፡ ዝንብ ፡ መጥታ ፡ አፍ
ጫዋ ፡ ላይ ፡ አረፈች ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አኛን ፡ አሞጥሙጣ ፡ በፉጨት ፡ ባሏን
ጠርታ ፡ በጣቷ ፡ አመለከተችው ። ወዲያው ፡ ቈዩ ፡ እበክሽ ፡ ዝም ፡ በዩ
እኔስ ፡ እንዳንቺ ፡ አላዋዛትም ፡ ብሎ ፡ የሙቀጫ ፡ ግልገል ፡ አንሥቶ ፡ ባለው
ኀይል ፡ ሁሉ ፡ ሠርኗን ፡ አደቀቀው ። ነፍሷም ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ጥርሷ ፡ ገጠ
በማየቱ ፡ አረ ፡ ተነሺ ፡ ታጠቂ ፡ ያለዛሬም ፡ ስቀሽ ፡ አታውቂ ፡ አላት ፡ ይባላል



ቈዩ ፡ እበክሽ ፡ ዝም ፡ በዩ
እኔስ ፡ እንዳንቺ ፡ አላዋዛ
ም ፡ ብሎ ፡ የሙቀጫ ፡ ግ
ገል ፡ አንሥቶ ፡ ባለው ፡ ኀይ
ሁሉ ፡ ሠርኗን ፡ አደቀቀው

ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ ቂልነት ፡ ያደርሳል ፡ ክሞት ።



## አንድ ፡ ሚስቱ ፡ የተጫወተችበት ፡ ሰው ።

አንድ ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ አግብቶ ፡ ይኖር ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እሷ ፡ ዘወትር ፡ ሳያማት ፡ አሞኛል እያለች ፡ ዝም ፡ ብላ ፡ በመተኛት ፡ ጊዜዋን ፡ ስለምታሳልፍ ፡ እርሱ ፡ ውሃውን ፡ ቀድቶ ፡ ወፍጮውን ፡ ፈጭቶ ፡ ከበረት ፡ የከብት ፡ እበት ፡ አውጥቶ ፡ ጠፍጥፎ ፡ በወንዶቹም ፡ ሞያ ፡ ረገድ ፡ እርሻውን ፡ አርሶና ፡ ቈፍሮ ፡ አጭዶ ፡ ከሥራውም ፡ ሲመለስ ፡ ምጣድ ፡ ጥዶ ፡ እየጋገረ ፡ ወጥም ፡ እየሠራ ፡ ይኖር ፡ ነበር ።


ከቶ ፡ በዕድሜው ፡ ልክ ፡ ምሳ ፡ የሚባል ፡ ነገር ፡ አያውቅም ፤ ማታ ፡ ከሥራውም ፡ ሲገባ ፡ መክሰሱንም ፡ ሆነ ፡ ራቱን ፡ እሱው ፡ ራሱ ፡ አሰናድቶ ፡ ይበላል ። ሚስቱ ፡ ግን ፡ ከሰው ፡ ቈጥራ ፡ ደክሞታል ፡ ብላ ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ቢሆን ፡ አሰናድታለት ፡ አታውቅም ።

እንደዚሁ ፡ ስትጫወትበት ፡ ኖራ ፡ ሞት ፡ አይቀርምና ፡ ብትሞት ፡ ያለመጠን ፡ አድርጎ ፡ ፊቱን ፡ በዝተት ፡ ነጭቶ ፡ በገመድ ፡ ታጥቆ ፡ ደረቱን ፡ በድንጋይ ፡ እየደበደበ ፡ ከማ ፡ እለምዳለሁ ፡ እንግዲህ ፡ በባሕሪዬ ፡ ማን ፡ ያውቅልኛል ፡ እንዳንቺ ፡ ማነው ፡ የሚያሽሞነሙነኝ ፡ እንግዲህ ፡ በማነው ፡ የምንቀባረረው ፡ ኩራቴ ፡ በማነው ፡ እንግዲህ ፡ ንብረቴ ፡ ተፈታ ፡ እያለ ፡ ያለቅስ ፡ ዠመር ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንዱ ፡ ባልንጀራው ፡ ምነው ፡ ወንድሜ ፡ ጓዴ ፡ ከሞት ፡ የሚቀር ፡ የለም ፡ ሁሉም ፡ እንደምታየው ፡ ሟች ፡ ነው ። እኛስ ፡ ብንሆን ፡ ፈንገ ፡ ይሁን ፡ ተነገ ፡ ወዲያ ፡ መሞታችንን ፡ መቼ ፡ እናውቀዋለን ፡ ለምን ፡ እንደዚህ ፡ አድርገህ ፡ አጥብቀህ ፡ ታዝናለህ ፡ ሐዘኑን ፡ ተወት ፡ አድርገው ፡ እንጂ ፡ በሐዘን ፡ መቼ ፡ ይገፋል ፡ ብለህ ፡ ነው ፡ ትርፉ ፡ ዐይንን ፡ ማጥፋት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቢመክረው ፡ እንደርሷ ፡ ያለ ፡ አይገኝም ፡ እንጂ ፡ ሲትማ ፡ ሞልቶ ፡ የለምን ፡ እንደ ፡ እሷ ፡ ያለ ፡ ማንን ፡ አገኛለሁ ፡ አላገኝም ፡ አላገኝም ፡ ሲል ፡ መለሰለት ።

ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ መዋዕለ ፡ ሐዘኑን ፡ ሲጨርስ ፡ ያ ፡ ጓደኛው ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ያለሴት ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ለመቀመጥ ፡ ይችላል ፡ በማለት ፡ አስበ፡ የጨዋ ፡ ልጅ ፡ ትዳር ፡ የምታውቅ ፡ ፈልጎ ፡ አመጣለት ። በጢት ፡ ገና ፡ ሴት ዮዋ ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ ሆና ፡ ሳለች ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ እንስራውን ፡ አንሥቶ ፡ ውሃ ፡ ለመቅዳት ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ ለመውረድ ፡ ተነሣ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያች ፡ ሴት ፡ ጌታዬ ፡ ወዴት ፡ ሊሄዱ ፡ ነው ፡ ገና ፡ ሳይነጋ፡ ጕድጕድ ፡ የሚሉት ፡ ብትለው ፡ የትም ፡ አልሄድ ፡ ከወንዝ ፡ ውሃ ፡ ለመቅ ዳት ፡ ነው ፡ አሁን ፡ እመጣለሁ ፡ ዝም ፡ ብለሽ ፡ ተኚ ፡ አላት ። እንዴት ፡ እርስዎ ፡ ውሃ ፡ ከቀዱማ ፡ ታዲያ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ላደርግልዎ ፡ መጣሁ ፡ እረ ፡ በሉ ፡ አምጡ ፡ ብላ ፡ ሽርጢን ፡ ታጥቃ ፡ በነገት ፡ ልብሷ ፡ አንገቷን ፡ ጠምጥማ ፡ እን ስራውን ፡ ከባሏ ፡ ተቀብላ ፡ ስትንደረደር ፡ እወንዝ ፡ ወርዳ ፡ ውሃዋን ፡ ቀድታ፡



እንዴት ፡ እርስዎ ፡ ውሃ ፡ ከቀዱማ ፡ ታዲያ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ላደርግልዎ ፡ መጣሁ ፡ እረ ፡ በሉ ፡ አምጡ ፤


ተመለሰች ። ወዲያው ፡ ቶሎ ፡ ብላ ፡ ድስት ፡ ጥዳ ፡ ለጅ ፡ መታጠቢያ ፡ ውሃ፡ በሾስሾስት ፡ ወዝታ ፡ ማታ ፡ ከባት ፡ ከናቷ ፡ ቤት ፡ ይዛው ፡ የመጣች፡ ውን ፡ የቅቤውን ፡ የድልኹን ፡ የሽሮውንም ፡ ቅል ፡ አቅርባ ፡ ማማሰያዋን ፡ አበጅታ ፡ ወጢን ፡ አሳምራ ፡ ከሠራች ፡ በኋላ ፡ እጁን ፡ በሙቅ ፡ ውሃ ፡ አስታ ጥባ ፡ ምሳውን ፡ በደንብ ፡ አብልታ ፡ በሉ ፡ እንግዲህ ፡ ወደ ፡ እርሻዎ ፡ ይሂዱ ፡ አለችው ። እሱም ፡ የማያውቀውን ፡ ምሳ ፡ በማግኘቱ ፡ ሰውነቱ ፡ በደስታ ፡ ተመልቶ ፡ ከብቶቹን ነድቶ ፡ ወደ ፡ ግብርና ፡ ሥራው ፡ ሄደ ።



እርሻውም ፡ ወደ ፡ ደጋ ፡ ነበርና ፡ አፋፉን ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ቢያስታውስ፡ ምራኑን ፡ ትቶታል ። ስለዚህ ፡ ከፋፉ ፡ ላይ ፡ ብቅ ፡ አለና ፡ ሚስቱ ፡ እን ግዳ ፡ በመሆኗ ፡ በስሟ ፡ ለመጥራት ፡ ስለ ፡ ፈራ ፡ እረ ፡ አንቺ ፡ ሴትዮ ፡ ብሎ ፡ ተጣራ ። እሷም ፡ ወዲህ ፡ ነው ፡ ወይ ፡ የምትጣሩት ፡ አለችው ። አዎን ፡ ቢላት ፡ ምነው ፡ ምን ፡ ሆነዋል ፡ ስትል ፡ ጠየቀችው ፤ እረ ፡ ምራኑን ፡ ረስቼዋለሁና ፡ አቀብዪኝ ፡ አላት ።

ያንን ፡ ምራን ፡ እውሻው ፡ አንገት ፡ ላይ ፡ አሰረችና ፡ እንግዲህ ፡ ውሻ ውን ፡ ይጥሩት ፡ አለችው ።

እሱም ፡ እረ ፡ እኔ ፡ ውሻው ፡ ምን ፡ ያደርግልኛል ፡ አንቺ ፡ ምራኑን ፡ ይዘሽልኝ ፡ ነዪ ፡ አላት ። ይጥሩት ፡ አልኩዎ ፡ አለችና ፡ በቍጣ ፡ ቃል ፡ ተናገ ረችው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ና ፡ ቡቺ ፡ ና ፡ ና ፡ ና ፡ ብሎ ፡ ቢጣራ ፡ ውሻው ፡ ያንን ፡ ምራን ፡ በንገቱ ፡ ይዞለት ፡ ከተፍ ፡ አለ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ልቡ ፡ በደስታ ፡ ተነክና ፡ እዚያው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተጣርቶ ፡ ከቶ ፡ ለመሆኑ ፡ አንቺም ፡ ትሞቺ ፡ ይሆን ፡ ብሎ ፡ ተናግሮ ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ ሄደ ፡ ይባላል ።



ያንን ፡ ምራን ፡ እውሻው ፡ አንገት ፡ ላይ ፡ አሰረችና ፡ እን ግዲህ ፡ ውሻውን ፡ ይጥሩት ፡ አለችው ።

፨ በቅን ፡ ልቡ ፡ ለትዳሩ ፡ የደከመ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሳያልፍለ ትና ፡ ሳይደሰት ፡ እንደዚሁ ፡ እንደማይቀር ፡ ልናምን ፡ ይገባል ።

መልከም ፡ ሚስት ፡ ለባሏ ፡ ዘውድ ፡ ናት ፡ የተባለውም ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

# የባልና ፡ ሚስት ፡ በተስቦ ፡ መታመም ።

ባልና ፡ ሚስት ፡ የነበሩ ፡ ሁለት ፡ ጓዶች ፡ አያሌ ፡ ዘመን ፡ አብረው ፡ ሲኖሩ ፡ ቈይተው ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሁለቱንም ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ተስቦ ፡ ያዛቸው ፤ የወለዷት ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡ ነበረቻቸውም ፡ እሷ ፡ ጠንክራ ፡ ሳትሰለች ፡ ታስታምማቸው ፡ ጀመር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ ቅርስ ፡ የሌላቸው ፡ በመሆኑ ፡ ድኽነት ፡ እየተጫናቸው ፡ ሄደና ፡ የሚበሉት ፡ እንኳን ፡ እኽል ፡ አጡ ። በመጨረሻውም ፡ በቤታቸው ፡ ውስጥ ፡ ላዋይ ፡ ያስቀመጡት ፡ አንድ ፡ አሞሌ ፡ ነበራቸውና ፡ ልጅቷን ፡ አንቺ ፡ በዚህ ፡ አሞሌ ፡ እኽል ፡ ሸምተሽ ፡ አምጪልን ፡ ብለው ፡ ሰደዷት ።

ያችም ፡ ልጅ ፡ እገበያ ፡ ወጥታ ፡ በዚያች ፡ ጨው ፡ ለጆሮዋ ፡ ጉትቻ ፡ ገዝታ ፡ አጊጣ ፡ መጣች ። እቤትም ፡ በገባች ፡ ጊዜ ፡ እነዚያ ፡ የታመሙ ፡ ሰዎች ፡ እኽል ፡ በጣም ፡ ናፍቋቸው ፡ ነበርና ፡ ገና ፡ ከመመለሷ ፡ የሸመትሽው ፡ እኽል ፡ የታለ ፡ ብለው ፡ ጠየቋት ።

እርሷም ፡ እሱ ፡ ለበሳው ፡ ጕሮሮ ፡ እሱው ፡ ያስብለት ፡ ብዬ ፡ እኔ ፡ ለበሳሁት ፡ ጆሮዬ ፡ ጉትቻ ፡ ገዝቼበት ፡ መጣሁ ፡ በማለት ፡ ሳታፍርና ፡ ሳትፈራ ፡ በቀጥታ ፡ ነገረቻቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሽተኞቹ ፡ በንዴት ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ሳለ ፡ ማታውን ፡ ነጋዴዎች ፡ ብዙ ፡ እኽል ፡ በወቀሬና ፡ በአጋሰስ ፡ ጭነው ፡ መጥተው ፡ በሽተኞቹ ፡ ከሉበት ፡ ቤት ፡ አሳድሩን ፡ ብለው ፡ ለመኑ ።

ልጅቷም ፡ ርኅርኅት ፡ በመሆኗ ፡ ተቀብላ ፡ አሳደረቻቸው ። ጧት ፡ በማለዳ ፡ ወፍ ፡ ያልቀመሰው ፡ ውሃ ፡ ቀድታ ፡ ወላጆቿን ፡ ስታጠምቃቸው ፡ መሻዳሪዎቹ ፡ አይተው ፡ ምን ፡ ሆነዋል ፡ ብለው ፡ ጠየቋት ። እርሷም ፡ በተስቦ ፡ ታመዋል ፡ ስትል ፡ መለሰችላቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እነዚያ ፡ ነጋዴዎች ፡ ደንግጠው ፡ ከተስቦ ፡ ቤት ፡ ያራገፍነውን ፡ እኽል ፡ ጭነን ፡ ሄደን ፡ ልጆቻ





እሱ ፡ ለበሳው ፡ ጕሮሮ ፡ እሱው ፡ ያስብለት ፡ ብዬ ፡ እኔ ፡ ለበሳሁት ፡ ጆሮዬ ፡ ጉትቻ ፡ ገዝቼበት ፡ መጣሁ ፡



ወላጆቿን ፡ ስትጠምቃቸው ፡ መሻዳሪዎቹ ፡ አይተው ፡ ምን ፡ ሆነዋል ፡ ብለው ፡ ጠየቋት ።

ችንንና ፡ ዘመዶቻችንን ፡ በበሽታ ፡ ልናስፈጅ ፡ ነውን ፡ አይሆንም ፡ ይቅርብን ፡ ብለው ፡ እኽላቸውን ፡ ከነጭልጊው ፡ ጥለውላት ፡ ሄዱ ።

ልጅቷም ፡ ስለ ፡ ሰጣቸው ፡ ሲሳይ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግና ፡ በነጋዴዎቹ ፡ እኽል ፡ እናትና ፡ አባቷን ፡ አስታማ ፡ አዳነች ፡ ይባላል ።

※ እርሷ ፡ እንዳለችውም ፡ ሁሉ ፡ ለበሳቸው ፡ ጆሮዋ ፡ ጕትቻ ፡ ገዝታ ፡ ብታጌጥ ፡ እሱም ፡ (እግዚአብሔር) ፡ ደግሞ ፡ ለከፈተው ፡ ጕረሮ ፡ አስቦ ፡ እኽል ፡ አዘጋጀለት ።

ስለዚህም ፡ በእውነት ፡ በፈጣሪው ፡ ያመነ ፡ ሁሉ ፡ የፈለገውን ፡ ለማግኘት ፡ እንደሚችል ፡ እንወቅ ። የናትና ፡ ያባትን ፡ ትእዛዝ ፡ መጣስ ፡ የማይገባ ፡ መሆኑንም ፡ እንርሳ ።

# ያንድ ፡ ድኻ ፡ ሰው ፡ ኑዛዜ ።

ሁለት ፡ ወንድ ፡ ልጆች ፡ የወለደ ፡ አንድ ፡ ድኻ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ጊዜ ፡ ሞቱ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ያለው ፡ ሀብት ፡ አንድ ፡ ወደል ፡ አህያ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ይህንኑ ፡ ልጆቹ ፡ እንዲካፈሉት ፡ ተናዘዘ ፤ ወዲያው ፡ እሱም ፡ እጅግ ፡ ሳይሰነብት ፡ ለሞት ፡ በቃ ።

አንደኛው ፡ ልጅ ፡ በጣም ፡ ባለጸጋ ፡ ሲሆን ፡ ሁለተኛው ፡ ግን ፡ የዕለት ፡ ራት ፡ የሌለው ፡ ችግረኛ ፡ ነበር ። ከድኽነቱም ፡ ብዛት ፡ የተነጣ ፡ ገና ፡ አባቱ ፡ ከመሞቱ ፡ የሚበላው ፡ ቸገረው ። ስለዚህም ፡ ከበርቴ ፡ ወንድሙን ፡ እባክህ ፡ ወንድሜ ፡ ይኸንን ፡ አህያችንን ፡ ሸጠን ፡ እንካፈል ፡ አለና ፡ ለመነው ። ያም ፡ ባለጸጋ ፡ በሀብቱና ፡ በገንዘቡ ፡ ብዛት ፡ ተመክቶ ፡ ለችግረኛው ፡ ወንድሙ ፡ እኔ ፡ አርጂ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሸጬ ፡ አልካፈልም ፡ ሲል ፡ በመቃወም ፡ መለሰለት ።

በዚሁ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ተጣሉ ፡ በሀገሩ ፡ ከሚገኘው ፡ ዳኛ ፡ ዘንድ ፡ ሄዱ ። ባለጉዳዮቹም ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የመጡበትን ፡ በየተራቸው ፡ ዘርዝረው ፡ አመለከቱት ። ዳኛውም ፡ በሁለቱም ፡ በኩል ፡ የቀረበለትን ፡ መግለጫ ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ አርዳችሁ ፡ ተካፈሉት ፡ ብሎ ፡ ፈረደ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሀብታሙ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አለው ፤ ችግረኛው ፡ ግን ፡ አዝኖ ፡ አምሮ ፡ አስቀሰ ። ሆኖም ፡ ከዳኛ ፡ የተሰጠ ፡ ትእዛዝ ፡ መከበርና ፡ መፈጸም ፡ ስላለበት ፡ ወደል ፡ አህያው ፡ ታረደና ፡ ሥጋው ፡ እሁለት ፡ ላይ ፡ ተመደበ ። ባለጸጋው ፡ ድርሻውን ፡ ለውሾቹ ፡ ሰጣቸው ። ድኻው ፡ ግን ፡ እንኳን ፡ ውሻ ፡ ዶሮ ፡ የሌለው ፡ ነበርና ፡ ፈንታውን ፡ ከታረደበት ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ጥሎት ፡ ሄደ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እያዘነና ፡ እየተከዘ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ በድንገት ፡ ቤቴን ፡ በእሳት ፡ አቃጥዬ ፡ እሄዳለሁ ፡ ብሎ ፡ ተነሣ ፤ የሚኖርበት ፡ ጐዣና ፡ የባለጸጋውም ፡ ትልልቅ ፡ አዳራሾች ፡ባንድ ፡ አጥር ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ይገኙ ፡ ነበር ።



በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባለጸጋው ፡ ከብቱና ፡ ገንዘቡ ፡ አሳዝኖት ፡ ግምቱን ፡ ልስጥህ ፡ እንጂ ፡ ለምን ፡ ታቃጥላለህ ፡ ያለዚያ ፡ የኔም ፡ ቤት ፡ አብሮ ፡ ሊነድ ፡ አይደለምን ፡ አለው ። እሱም ፡ እንቢ ፡ እኔ ፡ ገንዘብ ፡ አያሻኝም ፡ ቤቴን ፡ አቃጥዬ ፡ ነው ፡ የምሄደው ፡ ሲል ፡ አጥብቆ ፡ መለሰለት ።

እንግዲያውስ ፡ ዳኛ ፡ ሳይፈርድ ፡ እንዲሁ ፡ ተነሥተህ ፡ አታቃጥልም ፡ በማለት ፡ ጠብ ፡ አብቅለው ፡ ሳለ ፡ ገላጋይ ፡ ስለ ፡ ገባቸው ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለማመልከት ፡ ተያይዘው ፡ ሄዱ ። ዳኛውም ፡ የሚያውቁት ፡ ያው ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የፈረደባቸው ፡ ነበር ። እሱም ፡ ሁለቱም ፡ ባላጋራዎች ፡ ያመለከቱትን ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ ቤቱን ፡ አቃጥሎ ፡ ይሂድ ፡ እንጂ ፡ ለማን ፡ ብሎ ፡ የደከመበትን ፡ ጥሎ ፡ ይሄዳል ፡ ሲል ፡ ፍርድ ፡ ሰጠ ።



ወደል ፡ አህያው ፡ ታረደና ፡ ሥጋው ፡ ከሁለት ፡ ላይ ፡ ተመደበ ።

ባለጐዣውም ፡ ዳኛው ፡ እንደ ፡ ፈረደለት ፡ ቤቱን ፡ በእሳት ፡ ለኰሰው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የዚያንም ፡ የባለጸጋ ፡ ወንድሙን ፡ አዳራሽ ፡ ነፋስ ፡ ተነሥቶ ፡ ነበርና ፡ እሳቱ ፡ ተምዘግዝጎና ፡ ተወርውሮ ፡ ተያያዘው ። ምንም ፡ ቢፈራጭና ፡ ቢደክምም ፡ ለማዳን ፡ ስላልቻለ ፡ እልፍኙ ፡ ማድቤቱ ፡ ጐተራውም ፡ ሳይቀሩ ፡ በሙሉ ፡ ተቃጠሉበት ።

አደጋው ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ባለጸጋው ፡ ቤቶቹ ፡ በተቃጠሉበት ፡ በታ ፡ ላይ ፡ የመኖሪያ ፡ ቤቱን ፡ ቀልሶ ፡ ሲቀመጥ ፡ ድኻው ፡ ደግሞ ፡ ጎጆው ፡ የነበረበትን ፡ ድርሻ ፡ በታውን ፡ ቈፍሮ ፡ ባቄላ ፡ ዘራው ። በሸ



እሳቱ ተያምዘግዝጎ ፡ የባለጸ ጋውን ፡ አዳራሽ ፡ ተያያ ዘው ።

ቱም ፡ ወራት ፡ የባለጸጋው ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ከባቄላው ፡ ውስጥ ፡ ገብታ ፡ እሸት ፡ ስትበላ ፡ ያዛትና ፡ ወዲያው ፡ ገላጋይም ፡ ቢገባ ፡ አሸንፎ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይዟት ፡ ሄደ ። ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሳይዎ ፡ የድኻ ፡ ባቄላዬን ፡ ስትበላ ፡ ያገኟት ፤ ሆዷን ፡ ሰንጥቄ ፡ ባቄላዬን ፡ እን ድወስድ ፡ ፍርድ ፡ ይስጡኝ ፡ ሲል ፡ አቤቱታውን ፡ ለዳኛው ፡ አቀረበ ።

የልጅቱ ፡ አባትም ፡ በበኩሉ ፡ ባቄላ ፡ ባቄላ ፡ ነው ፡ ይልቁንም ፡ ድልቡን ፡ በገተራ ፡ ያለውን ፡ በሙሉ ፡ ይውሰድ ፡ እንጂ ፡ እንዴት ፡ ልጄን ፡




በሸቱም ፡ ወራት ፡ የባለጸ ጋው ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ከባቄላ ፡ ውስጥ ፡ ገብታ ፡ እሸት ፡ ስት በላ ፡ ያዛት ።



ሆዷን ፡ ይሰነጥቃል ፡ ሲል ፡ ለዳኛው ፡ ቢያመለክት ፡ ድኻው ፡ እሆዷ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ የራሴን ፡ ባቄላ ፡ እንጂ ፡ ያንተን ፡ የገተራ ፡ እኽል ፡ አልፈልግም ፡ ብሎ ፡ መለሰ ።

ዳኛውም ፡ መቼም ፡ ፍርደ ፡ ገምድል ፡ ነውና ፡ ልጅቱን ፡ ሆዷን ፡ ሠንጥቆ ፡ የራሱን ፡ ባቄላ ፡ አውጥቶ ፡ ይውሰድ ፡ ሲል ፡ ፈረደ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ድኻ ፡ ተደስቶ ፡ ሲፈነጥዝ ፡ ባለጸጋው ፡ ያለኝን ፡ ሀብት ፡ ው ሰድ ፡ እንጂ ፡ እንዴት ፡ አድርገህ ፡ ልጄን ፡ ታርዳለህ ፡ ሲል ፡ ጠየቀው ። እሱም ፡ አንተ ፡ በማን ፡ ሀገር ፡ ኖሯል ፡ አህያ ፡ ሲታረድ ፡ ያየኸው ፡ አለው ።



ዳኛውም ፡ ልጅቱን ፡ ሆዷን ፡ ሠንጥቆ ፡ የራሱን ፡ ባቄላ ፡ አው ጥቶ ፡ ይውሰድ ፡ ሲል ፡ ፈረደ ።

በዚህም ፡ መካከል ፡ የሀገር ፡ ሽማግሎች ፡ በግልግል ፡ ገብተዋቸው ፡ እንዲታረቁ ቢለምኑት ፡ አህያ ፡ አርዶብኝ ! አላቸው ። ይቅር ፡ ለእግዚአ ብሔር ፡ ነውና ፡ እባክህ ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ባለጸጋው ፡ ፍላጎት ፡ ሀብቱን ፡ እኩል ፡ ለኩል ፡ አካፍለው ፡ እርቅ ፡ እንዲሆን ፡ ስላደረጉ ፡ ልጅቱ ፡ ከመቀ ደድ ፡ ድና ፡ ድኻውም ፡ ከችግሩ ፡ ወጥቶ ፡ ኑሮውን ፡ በደስታ ፡ ለማሳለፍ ፡ ቻለ ፡ ይባላል ።

፨ ልበናቸው ፡ የዋህ ፡ ለሆነ ፡ ሰዎች ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅርባቸው ፡ ነው ። ምንም ፡ ቢውል ፡ ቢያድር ፡ በሰፈሩት ፡ ቍና ፡ መሰፈር ፡ የማይቀር ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ ከእንደዚህ ፡ ያለው ፡ የተንኰልና ፡ የጭካኔ ፡ መንፈስ ፡ መራቅ ፡ ይገባል ።

# ሦስት ፡ ቂል ፡ ወንድማማቾች ።

ሦስት ፡ ቂል ፡ ወንድማማቾች ፡ ባንድነት ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አብረው ፡ ሲሄዱ ፡ እልም ፡ ካለ ፡ ገደል ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ለሞፈር ፡ የሚሆን ፡ ዛፍ ፡ አገኙና ፡ መቍረጥ ፡ ዠመሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ መግሪያው ፡ ያልሰላ ፡ ሆኖ ፡ ቢሉት ፡ ቢሠሩት ፡ የማይወድቅላቸው ፡ ቢሆን ፡ በዚህ ፡ ተበሳጩና ፡ አንደኛው ፡ ሁለቱን ፡ ወንድሞቹን ፡ እጫፍ ፡ ላይ ፡ ወጥታችሁ ፡ ክበዱት ፡ እኔ ፡ ከሥር ፡ ልቍረጥ ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ እሺ ፡ መልካም ፡ ሐሳብ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ፈጥነው ፡ እናቱ ፡ ላይ ፡ ፊጥ ፡ ፊጥ ፡ አሉና ፡ እንዲወድቅ ፡ ያወዛውዙት ፡ ዠመር ። ያም ፡ ዛፍ ፡ ክርክሩ ፡ ጉድቶት ፡ ኖሮ ፡ ወዲያው ፡ ይዟቸው ፡ ወደ ፡ ገደሉ ፡ ገባ ። ቈራጩ ፡ ተናዶ ፡ እረ ፡ ጉድ ፡ ሞፈሩን ፡ ይዘውት ፡ ጠፉ ፡ ብሎ ፡ በዚያው ፡ በገቡበት ፡ ተከትሎ ፡ ቍል ቍል ፡ ዘሎ ፡ ወረደ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ አንደኛውም ፡ እንኳ ፡ ሳይተርፍ ፡ ሦስቱም ፡ አለቁ ፡ ይባላል ።



ቈራጩ ፡ ተናደ ፡ እረ ፡ ጉድ ! ሞፈሩን ፡ ይዘጡት ፡ ጠፉ ፡ ብሎ ፡ በዚያው ፡ በገቡበት ፡ ተከታትሎ ፡ ቍልቍል ፡ ዘሎ ፡ ወረደ ።

፨ እምብዛም ፡ ቂልነት ፡ ያደርሳል ፡ ከሞት ። በሬ ፡ ሆይ ፡ ሣሩን ፡ አየህና ፡ ገደሉን ፡ ሳታይ ፡ እየተባለ ፡ የሚተረተው ፡ ይህነን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ እንዳይደርስ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ መሆኑን ፡ እንገንዘብ ።



# የእሳትና ፡ ውሃ ፡ በሬ ፡ መግዛት ።

እሳትና ፡ ውሃ ፡ አብረው ፡ አንድ ፡ በሬ ፡ ገዝተው ፡ ነበር ፡ ይባላል ፤ ያንንም ፡ በሬያቸውን ፡ ሌባ ፡ ሠርቆ ፡ አረደባቸው ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አቶ ፡ እሳት ፡ ጌታዬ ፡ አቶ ፡ ውሃ ፡ ካንተ ፡ በቀር ፡ እኔ ፡ ሁሉን ፡ አሸንፋለሁ ፡ የሚችለኝ ፡ የለም ፤ ገንዘቡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሁለታችንም ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ተነሥቼ ፡ ደኑንም ፡ ሣሩንም ፡ ቤቱንም ፡ አቃጥዬ ፡ የበሬያችንን ፡ ሌባ ፡ ልፈልገው ፡ አለው ። ውሃውም ፡ ወንድሜ ፡ አቶ ፡ እሳት ፡ ምነው ፡ እንደዚህ ፡ ማለትህ ፡ የሠረቀውንም ፡ ደኅናውንም ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ ማቃጠል ፡ የሚገባ ፡ነውን ፤ ሌባችንን ፡ ለመያዝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚቸግረን ፡ ነገር ፡ የለም ፤ አሁን ፡ እናገኘዋለን ።

እጠብስ ፡ ያለ ፡ ካንተ ፡ አጥብ ፡ ያለ ፡ ከኔ ፡ የሚቀር ፡ አለን ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ልንይዘው ፡ ይቻላል ፡ ሲል ፡ መለሰለት ። ወዲያው ፡ ይኸንን ፡ ተነጋግረው ፡ ጥቂት ፡ ሳይቈዩ ፡ አንዱ ፡ ቅልጥም ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ መጣ ፤ አንደኛው ፡ ደግሞ ፡ ጨንራ ፡ ሊያጥብ ፡ ከውሃ ፡ ዘንድ ፡ ሄደ ። በዚህ ጊዜም ፡ ሌቦቹ ፡ ስለ ፡ ታወቁ ፡ ተያዙና ፡ ታሰሩ ፡ ይባላል ።

፨ መተባበርን ፡ ገንዘብ ፡ ያደረገ ፡ ጠላቱን ፡ ያሸንፋል ።

# የገንጆሮ፡ ገደል፡ መግባት ።

ገንጆሮ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በአንቅልፍ ፡ ምክንያት ፡ ገደል ፡ ገብቶ ፡ ጎኑ ፡ ደቀቀ ፡ እጁ ፡ ተሰበረ ፡ እግሩ ፡ ተቈላመመ ፡ ሕመሙም ፡ እየጠናበት ፡ ሄዶ ፡ እንዲያውም ፡ ሞት ፡ የሚያሠጋው ፡ ሆነ ። ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ለሚስ ቱና ፡ ለልጆቹ ፡ ለዘመዶቹም ፡ እንግዲህ ፡ እኔ ፡ እንደምታዩኝ ፡ ሕመሜ ፡ እየጠና ፡ ከመሔዱ ፡ በስተቀር ፡ ምንም ፡ የመዳን ፡ ተስፋ ፡ የለኝም ። አሁን ፡ በቁሜ ፡ ሕይወቴ ፡ ሳለ ፡ ዐይኔ ፡ እያየ ፡ ልጆቼ ፡ ሚስቴ ፡ ዘመዶቼም ፡ ሁና ችሁ ፡ ልቅሶዬን ፡ በቁሜ ፡ አልቅሱልኝ ፡ አላቸው ።



እንግዲህ ፡ እኔ ፡ እንደምታዩኝ ፡ ሕመሜ ፡ እየጠና ፡ ከመሔዱ ፡ በስተቀር ፡ ምንም ፡ የመዳን ፡ ተስፋ ፡ የለኝም ፡ አሁን ፡ በቁሜ ፡ ሕይወቴ ፡ ሳለ ፡ ዐይኔ ፡ እያየ ፡ ልጆቼ ፡ ሚስቴ ፡ ዘመዶቼም ፡ ሁናችሁ ፡ ልቅሶዬን ፡ በቁሜ ፡ አልቅሱልኝ ፡ አላቸው ።

ይህንንም ፡ ቃሉን ፡ ስለ ፡ ነገራቸው ፡ ሚስቱና ፡ ልጆቹ ፡ ዘመድ ፡ አዝ ማዶቻቸውን ፡ ጠርተው ፡ በሰሌ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ተሰብስበው ፡ ለቅሷቸውን ፡ ጀመሩ ።



ለቅሶውም ፡ በተፋፋመ ፡ ሰዓት ፡ ‹ወንገረዝ› ፡ የሚባለው ፡ ወንድ ፡ ልጁ ፡ ተነሥቶ ፡ አባቴ ፡ አሟዴ ፡ አባቴ ፡ አሟዴ ፡ አሟዴ ፡ ዘገር ፡ ነቅናቂው ፡ ጋሻ ፡ መከቼ ፡ ገዳዩ ፡ ፈረሰኛው ፡ አሟዴ ፡ አባ ፡ መንትፍ ፡ ያለው ፡ ባሕር ፡ ቀጋ ፡ ከቍልጭ ፡ ተነሥቶ ፡ እምቡስ ፡ የሚዋጋ ፡ እያለ ፡ ሲያለቅስ ፡ ተው ፡ ተው ፡ ያለሥራዩ ፤ ልጄ ፡ ይህ ፡ መቼ ፡ የኔ ፡ ሞያ ፡ ነው ፡ እለና ፡ በቍጣ ፡ ቃል ፡ ተናገረው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሴት ፡ ልጁን ፡ «ትውረስን» ፡ እስቲ ፡ አንቺ ፡ ተነሽ ፡ ልጄ ፡ አላት ። እሷም ፡ ተነሣችና ፡ አባቴ ፡ አሟዴ ፡ አባቴ ፡ አሟዴ ፡ ወደል ፡ ውሻ ፡ ገልማጭ ፡ በገደል ፡ ላይ ፡ ሯጭ ፡ የሰው ፡ ነዶ ፡ ዘርጣጭ ፡ አሟዴን ፡ ገደሉት ፡ አገኙተው ፡ በግላጭ ፡ ብላ ፡ በገጠመች ፡ ጊዜ ፡ እሱ ፡ ነዋ ፡ ልጄ ፡ እሱ ፡ ነዋ ፡ አለ ። ደግሞ ፡ የእንጀራ ፡ ልጁ ፡ ተነሣችና ፡

እንኳን ፡ መሞትና ፡ ይፍላበት ፡ በረዶ ፡
ሳያቀምሰኝ ፡ ቀርቷል ፡ ከሰረቀው ነዶ ፤ ባለች ፡ ጊዜ ፡ ልጁ ፡ ደግሞ ፡
መለስ ፡ አድርጋ ፡

ምነው ፡ የናቴ ፡ ልጅ ፡ ምነው ፡ የምዬ ፡ ልጅ ፡ ይሙት ፡ ትያለሽ ፡ ያድነን ፡ ነበረ ፡ ካምሳ ፡ ወደል ፡ ውሻ ፡ ብላ ፡ ገጠመች ። በዚህም ፡ ልብ ፡ በሚነካ ፡ ግጥሟ ፡ ከዚያ ፡ የተሰበሰበውን ፡ ዘመድ ፡ አዝማድ ፡ ትንሽ ፡ ትልቁን ፡ በእንባ ፡ አራጨችው ፡ ይባላል ።

፨ እንኳን ፡ ያሳደገን ፡ አባትና ፡ ማንንም ፡ በዕድሜ ፡ የሸመገለውን ፡ ሁሉ ፡ ማክበር ፡ ይገባል ።

ያለሟያው ፡ የሚደረገው ፡ ምስጋና ፡ ሁሉ ፡ ባስተዋዮች ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ስድብ ፡ ይቈጠራል ፤ ስለዚህ ፡ ልጆቼ ፡ ይኸን ፡ የመሳሰለውን ፡ አርአያ ፡ ከመከተል ፡ ጥንቃቄ ፡ አድርጉ ።

# ድ'ኻ ፡ ጥጃ ።

እናቴ ፡ የሞተችበት ፡ ድ'ኻ ፡ ጥጃ ፡ ነበረ ፡ ይባላል ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሣር ፡ ወደ ፡ ለመለመበት ፡ ውሃ ፡ ወደ ፡ ፈለቀበት ፡ ተሰዶ ፡ ሲሄድ ፡ ፍየል ፡ አገኘችውና ፡ አያ ፡ ድ'ኻ ፡ ጥጃ ፡ ወዴት ፡ ትሄዳለህ ፡ በማለት ፡ ጠየቀችው ። እሱም ፡ ሣር ፡ እለመለመበትና ፡ ውሃ ፡ እፈለቀ በት ፡ አላት ። እንግዲያውስ ፡ እባክህ ፡ እኔንም ፡ አስከትለኝ ፡ አለችው ።

—አንቺ ፡ አፍሽ ፡ አያርፍ ፡ ስትለፈልፊ ፡ ታስበሊኛለሽ ፡

—እረ ፡ እኔ ፡ አላስበላህም ።

—እንግዲያውስ ፡ ነዪ ፡ ተነሽ ፡ እንሂድ ፡ ብሎ ፡ አስከትሏት ፡ ሄደ ።

ደግሞ ፡ ሦስተኛ ፡ አቶ ፡ ዶሮ ፡ አገኛቸው ። አያ ፡ ድ'ኻ ፡ ጥጃ ፡ ወዴት ፡ ትሄዳለህ ፡ ሲል ፡ ጠየቀው ። ሣር ፡ እለመለመበት ፡ ውሃ ፡ እፈለቀ በት ፡ በማለት ፡ መለሰለት ። እባክህ ፡ እኔንም ፡ አስከትለኝ ፡ ቢለው ፡ ኳክ ፡ ኳክ ፡ ስትል ፡ ታስበላኛለህ ፡ አላደርገውም ፡ አለው ፤ ስለዚህ ፡ ጥጃው ፡ ፈቀደለትና ፡ ጉዟቸውን ፡ ቀጠሉ ።

ወይዘሮ ፡ ጦጢትም ፡ እንደዚሁ ፡ አያ ፡ ድ'ኻ ፡ ጥጃ ፡ ወዴት ፡ ትሄዳ ለህ ፡ አለችው ፤ እሱም ፡ ሣር ፡ እለመለመበት ፡ ውሃ ፡ እፈለቀበት ፡ ነዋ ፡ አላት ። እባክህ ፡ እኔንም ፡ አስከትለኝ ፡ ስላለችው ፡ ታስበሊኛለሽ ፡ አላት ። እረ ፡ እንዴት ፡ አድርጌ ፡ አላስበላህም ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ብለህ ፡ አስከት ለኝ ፡ አለችው ።



ምን ፡ ቸገረኝ ፡ ከሆነልሽ ፡ በዪ ፡ እንሂድ ፡



ምን ፡ ቸገረኝ ፡ ከሆነልሽ ፡ በዪ ፡ እንሂድ ፡ ብሏት ፡ አብረው ፡ ሲሄዱ ፡ ውሃው ፡ እፈለቀበት ፡ ሣሩ ፡ እለመለመበት ፡ ቦታ ፡ ደርሰው ፡ ከዚያ ፡ ሆነው ፡ ሲበ ሉና ፡ ሲጠጡ ፡ ስለ ፡ ሰነበቱ ፡ ጥጋብና ፡ እብሪት ፡ ተሰማቸው ።

ፍየል ፤ አያ ፡ ድ'ኻ ፡ ጥጃ ፡ ነፋኝ ፡ ቀበተተኝ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እባክህ ፡ ሚያ ፡ ልበልና ፡ ይውጣልኝ ፡ አለችው ። ድ'ኻ ፡ ጥጃም ፡ ተዪ ፡ አይሆንም ፡ ነብር ፡ ይሰማና ፡ መጥቶ ፡ ይበላሻል ፡ አላት ። ግድ ፡ የለህም ፡ አይበላኝም ፡ በማለት ፡ መልስ ፡ ሰጠችው ። እሱም ፡ በዪ ፡ እንግዲያው ፡ ይውጣልሽ ፡ ሚያ ፡ በዪ ፡ አላት ። ሚያ ፡ ስትል ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ ነብር ፡ መጥቶ ፡ ወደ ፡ ጫካ ፡ ይዟት ፡ ገባ ።

ዶሮ ፡ ደግሞ ፡ አያ ፡ ድ'ኻ ፡ ጥጃ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ኳክ ፡ ልበልና ፡ ይውጣ ልኝ ፡ እባክህ ፡ አለው ። ተው ፡ አይሆንም ፡ መጠማጥ ፡ ይበላሃል ፡ ይቅርብህ ፡ አለው ። እሱም ፡ ግድ ፡ የለህም ፡ አይበላኝም ፡ ቢለው ፡ በል ፡ እንዳሰኘህ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በኋላ ፡ እንዳትጸጸት ፡ ብሎ ፡ መከረው ። አቶ ፡ ዶሮም ፡ ኳክ ፡ ሲል ፡ መጠማጥ ፡ መጥቶ ፡ ይዞት ፡ ሄደ ።

ጦጢትም ፡ እንደዚሁ ፡ አያ ፡ ድ'ኻ ፡ ጥጃ ፡ እረ ፡ እባክህ ፡ እኔንም ፡ ነፋኝ ፡ ፈቃድ ፡ አድርግልኝና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ጮኬ ፡ ተንፈስ ፡ ልበል ፡ አለችና ፡ ለመነችው ። እረ ፡ ተዪ ፡ እባክሽ ፡ አንቺ ፡ እንኳ ፡ ቻል ፡ አድርጊው ፤ ነብር ፡ መጥቶ ፡ ይበላሻል ፡ አላት ። ምን ፡ ላድርግ ፡ አልችል ፡ አልኩ ፡ እከ ፡ እንደ ፡ በላ ፡ ይብላኝ ፡ ብትለው ፡ በዪ ፡ አንቺው ፡ ነበርሽ ፡ የቀረሽው ፡ ሞት ሽን ፡ ከፈለግሽ ፡ ጩኺ ፡ አለና ፡ ፈቀደላት ። ስትጮኽ ፡ ያ ፡ ነብር ፡ ሰምቶ ፡ መጣና ፡ ለመብላት ፤ ቢያባርራት ፡ ከንዱ ፡ ዛፍ ፡ አንዱ ፡ ላይ ፡ እያለች ፡ በማ ወክ ፡ አቃተችው ። እሱም ፡ ሰለቸውና ፡ ጥሏት ፡ ሄደ ።

አያ ፡ ድ'ኻ ፡ ጥጃ ፡ እንግዲህ ፡ ሁለታችን ፡ ብቻ ፡ ቀረን ፡ ተነሥተን ፡ ወደ ፡ ሀገራችን ፡ እንሂድምን ፡ አለችው ። እሺ ፡ ከሆነማ ፡ ሁላችንም ፡ በሰው ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ወጣን ፡ ከምንቀር ፡ ብንመለስ ፡ መቼ ፡ እጠላለሁ ፡ ብሎ ፡ ተነ ሥተው ፡ ሲሄዱ ፡ አያ ፡ ድ'ኻ ፡ ጥጃ ፡ ወናርዮ ፡ መሄድ ፡ አቅቶት ፡ በፋፍ ፡ ላይ ፡ ሲሄዱ ፡ አዳለጠውና ፡ ወርዶ ፡ ከፈፋ ፡ ውስጥ ፡ ተወተፈ ።

ጦጢትም ፡ እንደምታወጣው ፡ ተቸግራ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ስትንቈራጠጥ ፡ ብዙ ፡ ነጋዴዎች ፡ ማር ፡ በጭልጊ ፡ ጭነው ፡ መጡ ። ጌቶቼ ፡ አቶ ፡ ድኻ ፡ ጥጃ ፡ ገደል ፡ ገብቶብኛልና ፡ እባካችሁ ፡ አውጡልኝ ፡ አለቻቸው ። እኛ ፡ መንገደኞች ፡ ነን ፡ ጊዜውም ፡ መሽቶብናል ፡ ማራችንንስ ፡ ማን ፡ ይጠብቅልናል ፡ አሏት ። ለዚህማ ፡ እኔ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ሥራ ፡ ይገድ ፡ ነው ፡ የምታስቡት ፡ እኔ ፡ እጠብቃለሁ ፡ አለቻቸው ። እንግዲያውስ ፡ እናወጣዋለን ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ገደሉ ፡ ወረዱ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እርሷ ፡ ያንን ፡ ማራቸውን ፡ ከፍታ ፡ ሆዷ ፡ የቻለውን ፡ ያኽል ፡ በላችና ፡ ጭልጊውንና ፡ ገንቦውን ፡ ዐፈሩንም ፡ ዐዛባውንም ፡ ድንጋዩንም ፡ ሞልታ ፡ እንዳይታወቅባት ፡ ከላይ ፡ ማር ፡ አድርጋ ፡ መርጋ ፡ ቈየቻቸው ። ነጋዴዎቹም ፡ እንደ ፡ ሰጡት ፡ ቃል ፡ ጓደኛዋን ፡ አወጡላትና ፡ አቶ ፡ ድኻ ፡ ጥጃን ፡ ይዛ ፡ መንገዷን ፡ ቀጠለች ። ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ ከነጋዴዎቹ ፡ አንደኛው ፡ እረ ፡ ይህ ፡ ማር ፡ ምነው ፡ ከበደኝ ፡ አለ ። አንዱ ፡



ማራቸውን ፡ ከፍታ ፡ ሆዷ ፡ የቻለውን ፡ ያህል ፡ በላችና ፡ ዐፈሩንም ፡ ዐዛባውንም ፡ ሞልታ ፡ መርጋ ፡ ቈየቻቸው ።

ደግሞ ፡ እረ ፡ ታልክስ ፡ እኔንም ፡ ገማኝ ፡ አለና ፡ ወዲያው ፡ ከፍተው ፡ ቢያዩ ፡ ዐዛባ ፡ ድንጋይና ፡ ዐፈር ፡ ሆነባቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንደኛው ፡ ይህንን ፡ ያደረገች ፡ ያቺ ፡ ጦጣ ፡ መሆኗ ፡ የተረጋገጠ ፡ ነውና ፡ ሄደን ፡ እንያዛት ፡ አለ ። ሌላው ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እናውቃታለን ፡ ሲል ፡ መለሰ ። እሷማ ፡ ኸራቷ ፡ ቈራጣ ፡ ባለምልክት ፡ ናት ፡ አታመልጠንም ፡ ሲባባሉ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሰምቶ ፡ ኖሮ ፡ ሮጦ ፡ ሄደና ፡ ለሚጢት ፡ ጦጢት ፡ በኸራትሽ ፡ ምልክት ፡ ሊይዙሽ ፡ ነውና ፡ ተጠንቀቂ ፡ ብሎ ፡ ነገራት ። እሷም ፡ ወዲያው ፡ ቶሎ ፡ ብላ ፡ ወደ ፡ ጓደኞቿ ፡ ሄደች ።



ዘመዶቿም ፡ ወይዘሮ ፡ ጦጢት ፡ ኸራትሽን ፡ ምን ፡ ጐረደው ፡ አሏት ። አጤ ፡ ቢወዱኝ ፡ ቈረጡልኝ ፡ አለቻቸው ። ከመካከላቸው ፡ አንዱ ፡ እንግዲያውማ ፡ እባክሽ ፡ የኔንም ፡ ቊረጪልኝ ፡ አለቻት ። ሌሎቹም ፡ እንዲሁ ፡ እየተከታተሉ ፡ ቊረጪልን ፡ ሲሉ ፡ አጥብቀው ፡ ለመኗት ። እሷም ፡ ካስቸገራችሁኝ ፡ ፈቃዳችሁን ፡ እፈጽማለሁ ፡ ብላ ፡ የሁሉንም ፡ ጦጣ ፡ ኸራታቸውን ፡ ቈረጠች ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እነዚያ ፡ ነጋዴዎች ፡ መሣሪያቸውን ፡ ይዘው ፡ ቢሄዱ ፡ ጦጣዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ኸራተ ፡ ቈራጣ ፡ ሆነው ፡ አገኟቸው ። ስለዚህም ፡ ማንኛው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለይተው ፡ ለማወቅ ፡ ስለ ፡ ተቸገሩ ፡ የሀገሩ ፡ ጦጣ ፡ ሁሉ ፡ እንዲሰበሰብ ፡ ላገሩ ፡ ገዥው ፡ ልመና ፡ አቀረቡ ። እሱም ፡ እንዳመለከቱት ፡ ሁሉ ፡ በቀበሌው ፡ የሚገኘው ፡ ጦጣ ፡ በሙሉ ፡ እንዲከት ፡ አዘዘ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ነጋዴዎቹ ፡ ከወንዝ ፡ ዳር ፡ ወስዷቸውና ፡ ይኸንን ፡ የዘለለ ፡ ማራችንን ፡ አልበላብንም ፡ ያቃተው ፡ ግን ፡ የዘረፈን ፡ መሆኑ ፡ ነውና ፡ እንቈራኘዋለን ፡ ሲሉ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሰጡ ። ወዲያው ፡ ዝላይ ፡ ተዠምሮ ፡ ያልበላ ፡ ያልበላው ፡ ሁሉ ፡ ቸረር ፡ እያለ ፡ ሲሻገር ፡ ሌባዋ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀርታ ፡ ነበርና ፡ እዘላለሁ ፡ ስትል ፡ ወረደችና ፡ ከውሃው ፡ ውጥስ ፡ ወደቀች ። እሷም ፡ የናቴ ፡ ቀሚስ ፡ አወላከፈኝ ፡ አለችና ፡ ሁለተኛ ፡ ለመዝለል ፡ ሞከረች ። አሁንም ፡ መዝለል ፡ አቅቷት ፡ ከውስጡ ፡ ረብ ፡ አለች ። ውይ ፡ እቴ ፡ ይኸ ፡ ያባቴ ፡ ጋቢ ፡ አወላከፈኝ ፡ ብላ ፡ ብታመካኝም ፡ አጥፊዋ ፡ እሷ ፡ መሆኗ ፡ ታወቀና ፡ ተይዛ ፡ የፊጥኝ ፡ ታሰረች ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወስደው ፡ በቀላድ ፡ ከግንድ ፡ ጋራ ፡ ጠፈሩና ፡ ለመደብደቢያ ፡ የደሬ ፡ ፍልጥ ፡ ሊያመጡ ፡ ሄዱ ። እዚያው ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ አህያ ፡ መጣና ፡ ወይዘሮ ፡ ጦጢት ፡ ምን ፡ ሆነሽ ፡ ታስረሻል ፡ ሲል ፡ ጠየቃት ። ብዪ ፡ ጠጪ ፡ ቢሉኝ ፡ አልበላ ፡ አልጠጣ ፡ ብዬ ፡ ነዋ ! እባክህ ፡ አንተ ፡ ብላልኝ ፡ ጠጣልኝና ፡ አስፈታኝ ፡ አለችው ። እባክሽን ፡ እንኳን ፡ አንቺን ፡ ላስፈታ ፡ እኔ ለራሴ ፡ የሰው ፡ ነዶ ፡ ዘርጥፌ ፡ ዕዳ ፡ ገብቻለሁ ፡ አለና ፡ ጥሏት ፡ ሄደ ።

አያ ፡ ኸርቦ ፡ ደግሞ ፡ እንኰዬ ፡ ጦጢት ፡ ምን ፡ ሆነሽ ፡ ታስረሻል ፡ በማለት ፡ ጠየቃት ። አያ ፡ ኸርቦ ፡ ምኑ ፡ ቅጡ ፡ የኔ ፡ ነገር ፡ ብዪ ፡ ጠጪ ፡ ቢሉኝ ፡ አልበላም ፡ አ ልጠጣም ፡ ብዬ ፡ ነዋ ! አንተ ፡ እባክህ ፡ ብላልኝ ፡ ጠጣልኝ ፡ አለችው ። እኔ ፡ ለራሴ ፡ የሰው ፡ ወደል ፡ አህያ ፡ በልቼ ፡ ለማምለጥ ፡ በመሸሽ ፡ ላይ ፡ ነኝና ፡ አንቺን ፡ የማስፈታበት ፡ ጊዜም ፡ አላገኝ ፡ ብሏት ፡ አለፈ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አያ ፡ ዝንጀሮ ፡ ጉንበስ ፡ ጉንበስ ፡ ሲል ፡ መጣና
ወይዘሮ ፡ ጦጢት ፡ ምን ፡ ሆንሽ ፡ ታሰርሽ ፡ ምነው ፡ ምን ፡ አገኘሽ ፡ አላት
እባክህን ፡ ወንድሜ ፡ የናትና ፡ ያባቴን ፡ ተዝካር ፡ ብዬ ፡ ጠጪ ፡ ቢሉኝ



እቢም ፡ የእናቴ ፡ ቀሚስ ፡ አወላክፈኝ ፡ አለችና ፡ ሁለተኛ ፡ ለመዝለል ፡ ሞከረች።

አልበላም ፡ አልጠጣም ፡ ብዬ ፡ ነዋ! አለችው ። ታዲያ ፡ ምን ፡ ቸገረሽ
አትበዪም ፡ አትጠጪም ፡ ነበር! ፡ ቢላት ፡ እኔ ፡ ብቻዬን ፡ አላልቅ ፡ አለኛ
አለችው ። እንግዲያው ፡ እኔ ፡ እበላልሻለሁ ፡ እጠጣልሻለሁ ፡ እሰሪኝ
አላት ። ደግ ፡ መልካም ፡ በል ፡ እኔን ፡ ፍታኝና ፡ ልሰርህ ፡ ስትል ፡ መለ
ችለት ። ፈታትና ፡ እሱን ፡ ከዚያ ፡ ግንድ ፡ ጋራ ፡ የፈጥኝ ፡ ጠፍራ ፡ እን
ዲህ ፡ መጥተው ፡ ሲጠይቁህ ፡ እበላለሁ ፡ እጠጣለሁ ፡ በል ፡ ብላ ፡ አስጠ
ቀቀችው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ ወጥታ ፡ ቍጭ ፡ አለች ።

እነዚያም ፡ ሰዎች ፡ ፍልጣቸውን ፡ አዘጋጅተው ፡ ተሸክመው
ቢመጡ ፡ በጦጣዋ ፡ ቦታ ፡ ዝንጀሮ ፡ ተተክቶ ፡ አገኙት ። አንተ ፡ ምን
ታደርጋለህ ፡ ቢሉት ፡ እንኩዬ ፡ ጦጢት ፡ አልበላም ፡ አልጠጣም ፡ ብዬ
ነው ፡ የታሰርኩት ፡ ብትለኝ ፡ እኔ ፡ እበላልሻለሁ ፡ እጠጣልሻለሁ ፡ ስላል
ኳት ፡ አስራኝ ፡ ሄደች ፡ አላቸው ። እረ ፡ የታባክንስ ፡ ብለው ፡ በዚያ
በደሬ ፡ ፍልጥ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቢያቀምሱት ፡ እበላለሁ ፡ እጠጣለሁ
እያለ ፡ ይለፈልፍ ፡ ገመር ። እሷም ፡ ከንዱ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ወደንዱ ፡ ቅር
ንጫፍ ፡ እየዘለለች ፡ የጦጣ ፡ ብልጣብልጥ ፡ የዝንጆሮ ፡ ቅልጣቅልጥ
ተው ፡ በለው ፡ በደሬ ፡ ፍልጥ ፡ እያለች ፡ ሥጋው ፡ አልቆ ፡ ዐጥንቱ
እስኪታይ ፡ ድረስ ፡ አስደበደበችው ።





እንኩዬ ፡ ጦጢት ፡ አልበላም ፡ አልጠጣም ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ የታሰርኩት ፡ ብትለኝ ፡ እኔ ፡ እበላልሻለሁ ፡ እጠጣልሻለሁ ፡ ስላልኳት ፡ አስራኝ ፡ ሄደች ።

በመጨረሻው ፡ ሞተ ፡ ብለው ፡ ገመዳቸውን ፡ ፈተው ፡ ጥለውት ፡ ሄዱ ። እሱም ፡ ነፍስ ፡ ሲዘራ ፡ የተደበደበው ፡ ተሰማውና ፡ እንኩዬ ፡ ጦጢት ፡ እረ ፡ አመመኝ ፡ ምን ፡ ይሻለኛል ፡ አላት ። ሂድ ፡ እዚያ ፡ ከማሩ ፡ ላይ ፡ ተንከባለል ፡ አለችው ። እያዘገመ ፡ ተጕዞ ፡ ቢንከባለልበት ፡ ሰማ ፡ ኖሮ ፡ ለበለበው ፡ ደግሞ ፡ እንኩዬ ፡ ጦጢት ፡ እረ ፡ ባሰብኝ ፡ አለና ፡ ነገራት ። እንግዲያው ፡ ሂደህ ፡ እዚያ ፡ እሜንደሩ ፡ አጠገብ ፡ ሁነህ ፡ ና ፡ ቡች ፡ ና ፡ ና ፡ ና ፡ እያልክ ፡ ተጣራ ፡ ውሾቹ ፡ መጥተው ፡ ቍስልህን ፡ ይልሱልሃልና ፡ ትድናለህ ፡ አለችው ።

እሱም ፡ እንደ ፡ መከረችው ፡ ሂዶ ፡ ና ፡ ቡች ፡ ና ፡ ቡች ፡ እያለ ፡ በተጣራ ፡ ጊዜ ፡ የመንደር ፡ ውሾች ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፡ መጥተው ፡ ሸረከክተውና ፡ ገነጣጥለው ፡ ጨጓራውን ፡ ዘርግፈው ፡ ጣሉት ፡ ይባላል ።

፨ እንኳን ፡ ደግ ፡ ለሠራ ፡ ለክፉ ፡ አድራጊም ፡ ቢሆን ፡ ቀና ፡ መሆን ፡ የተገባ ፡ ነው ። ደፋርና ፡ ጢስ ፡ መውጫ ፡ አያጣም ፤ ሆዱን ፡ ያለ ፡ ሆዱን ፡ ተወጋ ፡ እየተባለ ፡ ከባቶቻችን ፡ የሚነገረው ፡ በጦጣዋና ፡ በዝንጀሮው ፡ የተፈጸመውን ፡ ድርጊት ፡ ሊያሳስበን ፡ ይችላል ።

# አንበሳና፡የሰው፡ልጅ።

ሁለት፡ሰዎች፡ልጅ፡ይዘው፡በንድ፡ውድማ፡ውስጥ፡ሲጓዙ፡ወን በዴዎች፡ለገንዘባቸው፡መዝረፍ፡ሲሉ፡ገደሏቸው። ልጁን፡ግን፡ባባ ትና፡እናቱ፡ሬሳ፡አጠገብ፡ወድቆ፡ከነሕይወቱ፡አንበሳ፡ስላገኘው፡ወደ፡ ማረፊያው፡ወስዶ፡አስቀምጦ፡ማናቸውንም፡ለምግብ፡የሚሆነውን፡ ሁሉ፡እያደነ፡አብልቶ፡አጠጥቶ፡አሳደገው።

ልጁን፡ግን፡አንበሳ፡ባባትና፡ እናቱ፡ሬሳ፡አጠገብ፡ወድቆ፡ ከነሕይወቱ፡ስላገኘው፡ወደ፡ ማረፊያው፡ወስዶ፡አብልቶ፡ አጠጥቶ፡አሳደገው።



ልጁ፡ነፍስ፡ካወቀ፡በኋላ፡ወደ፡መንደር፡ሄዶ፡ከሰዎች፡መገና ኘት፡ዠመረ። ከዕለታት፡አንድ፡ቀንም፡መንደረተኞቹ፡ካንበሳው፡ ጋራ፡እንደ፡ምን፡ተስማምተው፡እንደ፡ኖሩ፡ስለ፡ጠየቁት፡ደግነቱን፡ በመልካም፡አኳኋን፡እንዳሳደገውና፡የሚያፈቅረው፡መሆኑንም፡ ጭምር፡ገልጾ፡አስረዳቸው። ከቶ፡ምንም፡ነውር፡አላገኘህበትምን፡ ብለው፡እንደ፡ገና፡ቢመረምሩት፡ልጁ፡አንድ፡ነውር፡ብቻ፡አግኝቼበ ታለሁ፡ይኸውም፡አቅፎኝ፡ሲተኛ፡የሚሸተኝ፡የብብቱ፡ክርፋት፡ነው፡ ብሎ፡ነገራቸው። በዚህም፡ጊዜ፡ሰዓቱ፡ምሽት፡ስለ፡ነበር፡አንበሳው፡ በቤቱ፡ኀሮ፡ሆኖ፡አዳምጦ፡ሰምቷቸው፡ኖሮ፡በልጁ፡ንግግር፡ቅር፡ተ ገበው፡እንዲያውም፡ቂም፡ያዘበት፡ልጁ፡ግን፡ካሳደገኝ፡አባቴ፡ዘንድ፡



ልመለስ፡ብሎ፡ያነጋገሩትን፡ሰዎች፡ተሰናብቶ፡በቶሎ፡ሄደ። እቤቱ፡እንደ፡ደረሰም፡አንበሳው፡ልጄ፡ከወዴት፡መጣህ፡ምነው፡ መሸብህሳ፡ብሎ፡ጠየቀው፡አባቴ፡አደን፡ለማደን፡ጥቂት፡ርቄ፡ሄጄ፡ ስለ፡ነበር፡ነው። ከዚያም፡ጥቂት፡እንደ፡ቈዩ፡አንበሳው፡ጦር፡ አንሥቶ፡እንካ፡ውጋኝ፡አለው።



ግድ፡ካልወጋኸኝ፡ብሎ፡ ቢያስጨንቀው፡ጦር፡አን ሥቶ፡ወጋው።

ልጁ፡ከወደቅሁበት፡አንሥተህ፡አብልተህ፡አጠጥተህ፡ለዚህ፡ እስከበቃ፡ድረስ፡አሳድገኸኝ፡እንዴት፡አንተን፡አባቴን፡እወጋለሁ፡ አለው። ግድ፡ካልወጋኸኝ፡ብሎ፡ቢያስጨንቀውና፡ቢያስገድደው፡ ጦሩን፡አንሥቶ፡ወጋው።

እንግዲህ፡እኔ፡አንተን፡በዱር፡እየተዘዋወርኩ፡እያደንኩ፡እን ዳሳደግሁ፡ይኸ፡ቍስሌ፡እስቲድን፡ድረስ፡እያደንክ፡አስታመኝ፡ አለው። ልጁም፡በትጋት፡እያደነ፡አስታሞ፡አዳነው። አንበሳውም፡ ቍስሉ፡መዳኑን፡ካየ፡በኋላ፡ሰማህ፡ልጄ፡በጦር፡የወጋኸኝ፡ቍስ ል፡ዳነ፡ነገር፡ግን፡ከዘመድህ፡ከሰው፡ጋራ፡በተገናኘህ፡ጊዜ፡የተ ናገርከው፡የስድብህ፡ቍስል፡ከልቤ፡አልጠፋም። ስለዚህ፡ከእንግዲ ህ፡ወዲያ፡አብረን፡ልንኖር፡አይቻልምና፡እኔም፡በጫካዬ፡አንተ ም፡ወደ፡ዘመዶችህ፡ሂድ፡ብሎ፡አሰናበተው፡ይባላል።

በጦር፡ከተወጋ፡በነገር፡የተወጋ፡ይብሳል።

# የዶሮ፡ዘመቻ።

አቶ ፡ ዶሮ ፡ ሥንቁን ፡ አሠንቆ ፡ ወደ ፡ ዘመቻ ፡ ሲሄድ ፡ አይጥ ፡ አገኘችውና ፡ ወንድሜ ፡ ወዴት ፡ ትጓዛለህ ፡ ብላ ፡ ጠየቀችው ። ዘመቻ፡ አላት ። በምን ፡ አቅምህ ፡ ልትዋጋ ፡ ብትለው ፡ አዳር ፡ በመላ ፡ ሲል ፡ መለሰላት ። እኔም ፡ ሥንቅ ፡ የለኝም ፡ እንጂ ፡ አብረን ፡ እንሄድ ፡ ነበር ፡ አለች ። አቶ ፡ ዶሮ ፡ ላንድ ፡ ያሉት ፡ ለሁለት ፡ ይበቃልና ፡ ከፈቀድሽ ፡ እንሂድ ፡ አላት ።

ተስማምተው ፡ ሁለቱ ፡ መንገደኞች ፡ ተያይዘው ፡ ሲገሠግሡ ፡ እባብ ፡ አገኛቸውና ፡ አቶ ፡ ዶሮ ፡ ወዴት ፡ ትሄዳላችሁ ፡ ሲል ፡ ጠየቃቸው ። ዘመቻ ፡ ቢሉት ፡ በየትኛው ፡ ዐቅማችሁ ፡ አላቸው ። ዶሮ ፡ አዳር ፡ በመላ ፡ ሲል ፡ መልስ ፡ ሰጠው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወይ ፡ ነዶ ፡ እኔም ፡ ሥንቅ ፡ የለኝም ፡ እንጂ ፡ አብሬያችሁ ፡ እሄድ ፡ ነበር ፡ ሲል ፡ ተናገረ ። ለሁለት ፡ ያሉት ፡ ለሦስት ፡ ይበቃል ፡ እንሂድ ፡ ብለው ፡ ሦስቱም ፡ አብረው ፡ ሲጓዙ ፡ አቶ ፡ እርኩም ፡ ከመንገድ ፡ አገኛቸው ። እሱም ፡ ወዴት ፡ ትሄዳላችሁ ፡ አቶ ፡ ዶሮ ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቅ ፡ ዘመቻ ፡ አለው ። ወይ ፡ ጥጋብ ፡ ወይ ፡ ድፍረት ፡ ከናንተው ፡ ዐቅም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ትሄዳላችሁ ፡ ቢለው ፡ አዳር ፡ በመላ ፡ ሲል ፡ መለሰለት ። እንግዲያውስ ፡ ሥንቅ ፡ የለኝም ፡ እንጂ ፡ እኔም ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ ብሄድ ፡ እወድ ፡ ነበር ፡ አላቸው ። አቶ ፡ እርኩም ፡ ሆይ ፡ ለሦስት ፡ ያሉት ፡ ላራት ፡ ይበቃል ፡ እንሂድ ፡ አሉት ። አራቱ ፡ ደግሞ ፡ አብረው ፡ ሲሄዱ ፡ አንበሳ ፡ ከመንገድ ፡ አገኛቸውና ፡ አቶ ፡ ዶሮ ፡ ወዴት ፡ ትሄዳላችሁ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ዶሮም ፡ ዘመቻ ፡ አለው ። በምን ፡ ዐቅማችሁ ፡ ቢላቸው ፡ አቶ ፡ ዶሮ ፡ አንበሳ ፡ ሆይ ፡ አዳር ፡ በመላ ፡ በማለት ፡ መለሰለት ። አንበሳም ፡ ሥንቅ ፡ የለኝም ፡ እንጂ ፡ አብሬያችሁ ፡ እሄድ ፡ ነበረ ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ ላራት ፡ ያሉት ፡ ላምስት ፡ ይበቃልና ፡ አቶ ፡ አንበሳ ፡ እንሂድ ፡ ብለውት ፡ አብረው ፡ ተጓዙ ።

ሲሄዱ ፡ ውለው ፡ የማታ ፡ ማታ ፡ ከላሞች ፡ በረት ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ርቦናልና ፡ ለራታችን ፡ እንዲሆነን ፡ ከዚህ ፡ ገብተን ፡ እንስረቅ ፡ እንስረቅ ፡ ተባብለው ፡ መከሩ ። አራቱ ፡ እንዴት ፡ ይመቸናል ፡ ቢሉ ፡ አቶ ፡ ዶሮ ፡ አይጥ ፡ ሂደሽ ፡ የከብቶቹን ፡ ማሰሪያቸውን ፡ በጥርስሽ ፡ በጥሽው ፡ እባብ ፡ ሂደህ ፡ ሰዎቹን ፡ በመርዝህ ፡ ንደፋቸው ፤ አንበሳና ፡ እርኩም ፡ ደግሞ ፡ በውጪ ፡ ሁኑችሁ ፡ አግሡ ፡ አላቸው ። ሁሉም ፡ በታ



ዘዙበት ፡ ሥራቸውን ፡ ጀመሩ ፤ ከብቶቹም ፡ ማሰሪያቸው ፡ ስለ ፡ ተበጠሰ ፡ ደንብረው ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ሄዱ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ይኸ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ይኸ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ አምስቱም ፡ ጥል ፡ አበቀሉ ።



ላራት ፡ ያሉት ፡ ላምስት ፡ ይበቃልና ፡ አቶ ፡ አንበሳ ፡ እንሂድ ፡ ብለው ፡ አብረው ፡ ተጓዙ ።

አቶ ፡ ዶሮ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጠቡ ፡ የሚቆምበትን ፡ መገላገያ ፡ መንገድ ፡ አሰበና ፡ ጓዴ ፡ እባብ ፡ አንበሳን ፡ በመርዝህ ፡ ግደለው ፡ አለው ። አንበሳው ፡ ሲሞት ፡ ደግሞ ፡ እርኩምን ፡ እባብን ፡ ዋጠው ፡ አለው ። እባ



እርኩምን ፡ እንቅልፍ ፡ ሲይዘው ፡ ክንፍ ፡ ክንፉን ፡ በጥሽው ፡ አላት ።

ብም ፡ ሲዋጥ ፡ አይጥን ፡ እንግዲህ ፡ እንቅልፍ ፡ ሲይዘው ፡ አይተሽ ፡ የእርኩምን ፡ ክንፍ ፡ ክንፉን ፡ በጥሽው ፡ አላት ። በዚህ ፡ ዘዴ ፡ ሁሉንም ፡ ከስፈጀ ፡ በኋላ ፡ አይጥን ፡ አንድ ፡ ከብት ፡ ጥለን ፡ ሥጋ ፡ እንብላ ፡ አላት ፤ ይሁን ፡ ተባብለው ፡ ተስማምተው ፡ አርደው ፡ ከጨረሱ ፡

በኋላ ፡ አቶ ፡ ዶሮ ፡ ቁሽትና ፡ ኰላሊት ፡ አቀረበና ፡ ምረጭ ፡ አላት ። እሷም ፡ ኰላሊት ፡ ይሻለኛል ፡ አለችው ። ደግ ፡ መልካም ፡ አለና ፡ እሱኑ ፡ ሰጥቷት ፡ ብትውጠው ፡ ጉረሮዋን ፡ አንቋት ፡ ሞተች ፡ ይባላል ።

፨ የዶሮን ፡ ብልኀት ፡ መመልከት ፡ ትልቅ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ይሰጣል ። ባስተዋይነቱ ፡ አንበሳን ፡ የሚያኽል ፡ ባላጋራና ፡ ሌሎቹንም ፡ አጥፍቶ ፡ ከብቱን ፡ ሁሉ ፡ ለራሱ ፡ አስቀረ ። ስለዚህ ፡ አጠረ ፡ ቀጠነ ፡ ብሎ ፡ ትን ኽን ፡ መናቅ ፡ አይገባም ።

---

## ያውሬ ፡ ሁሉ ፡ ገበያ ።

የምድር ፡ አውሬ ፡ ሁሉ ፡ መሰብሰቢያና ፡ መነጋገጃ ፡ አንድ ፡ ገበያ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አውሬ ፡ ሁሉ ፡ አገበያ ፡ ሲውል ፡ እያ ፡ ኸ፡ርቦ ፡ ግን ፡ ሳይሄድ ፡ ቀረ ። የማታ ፡ ማታ ፡ ገበያተኛ ፡ ሲመለስ ፡ ከጕሬው ፡ ወጣና ፡ ከመንገድ ፡ ዳር ፡ ተቀመጠ ። ገበያ ፡ ምላሽ ፡ ሲሆን ፡ ኰተቷን ፡ በገርባዋ ፡ አዝላ ፡ እንኰዬ ፡ ዝንጀሮ ፡ መጣች ። እያ ፡ ኸ፡ርቦም ፡ እንኰዬ ፡ ዝን ጀሮ ፡ እንደምን ፡ ዋልሽ ፡ ገበያውስ ፡ እንዴት ፡ ዋለ ፡ ምን ፡ ረከሷል ፡ ምንስ ፡ ተወደ፡ል ፡ ብሎ ፡ ጠየቃት ። ወንድሜ ፡ እኔ ፡ መሽቶብኛል ፡ እቤት ፡ ገብቼ ፡ ገና ፡ ራቴን ፡ እጋግራለሁ ፡ እንኰዬ ፡ ጦጢት ፡ እኋላ ፡ አለችልህ ፡ እሷን ፡ ጠይቃት ፡ ብላው ፡ ሄደች ።

እንኰዬ ፡ ጦጢትም ፡ ወዲያው ፡ ስለ ፡ መጣች ፡ ገበያው ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዋለ ፡ አላት ። እባክህ ፡ እያ ፡ ኸ፡ርቦ ፡ እኔ ፡ መሽቶብኛል ፡ ገና ፡ እቤቴ ፡ ገብቼ ፡ ወደ ፡ ውሃ ፡ እወርዳለሁ ፡ እንኰዬ ፡ ሚዳቋ ፡ ከኋላ ፡ አለችልህ ፡ እሷን ፡ ጠይቃት ፡ ብላው ፡ አለፈች ።

ሦስተኛ ፡ ሚዳቋ ፡ ቅራቅንበዋን ፡ አዝላ ፡ በዚሁ ፡ እያ ፡ ኸ፡ርቦ ፡ ባለበት ፡ መንገድ ፡ መጣች ። እያ ፡ ኸ፡ርቦም ፡ ሚዳቋ ፡ እባክሽ ፡ ገበያው ፡ እንደ ፡ ምን ፡



ዋለ ፡ አላት ። እንኰዬ አህዩት ፡ እኋላ ፡ አለችልህ ፡ እሷን ፡ ጠይቅ ! እኔ ፡ እነእንኰዬ ፡ ዝንጀሮ ፡ ስላመለጡኝ ፡ እቸኰላለሁ ፡ ብላው ፡ ሄደች ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አህዩት ፡ ከኋላ ፡ ስትንቀረደድ ፡ መጣች ። አህዩት ፡ ዛሬ ፡ ገበያ ፡ እንዴት ፡ ዋለ ፡ ምንስ ፡ ርካሽ ፡ ነው ፡ ምንስ ፡ ውድ ፡ ሆነ ፡ አላት ። እባክህ ፡ እያ ፡ ኸ፡ርቦ ፡ ደክሞኛል ! እስቲ ፡ አረፍ ፡ ብዬ ፡ ላውራልህ ። ይህ ፡ በዚህ ፡ ያኽል ፡ ይህ ፡ በዚህ ፡ ያኽል ፡ ሲገዛ ፡ ዋለ ፡ እያለች ፡ ስታወራለት ፡ አህዩት ፡ እረ ፡ ከሆነስ ፡ ሆነና ፡ እኔ ፡ የምዘለውን ፡ ለመዝ ለል ፡ ትችያለሽን ፡ አላት ። እረ ፡ ንሺ ፡ ሰዎች ! አሳምሬ ! አለችው ። እሱም ፡ የሞት ፡ ሞቱን ፡ እንጣጥ ፡ ብሎ ፡ ተሻገር ፡ እሷን ፡ ደግሞ ፡ በዪ ፡ እስቲ ፡ ዝለዪ ፡ አላት ። እንጣጥ ፡ ስትል ፡ ወረደችና ፡ እፈፋ ፡ ውስጥ ፡ ውትፍ ፡ ብላ ፡ ቀረች ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እያ ፡ ኸ፡ርቦ ፡ ሆዬ ፡ ወርዶ ፡ ሆዷን ፡ ዘርግፎ ፡ ሲበላ ፡ እንኰዬ ፡ ውሺት ፡ እኋላ ፡ ነበረችና ፡ ደም ፡ ደም ፡ ሲሸ ታት ፡ ጊዜ ፡ አፋፍ ፡ ብቅ ፡ ብላ ፡ ብትመለከት ፡ አህዩትን ፡ ጥሎ ፡ ሲበላ ፡ አየችው ። አበላሉም ፡ ስለ ፡ አስጕመዣት ፡ ለሐጫ ፡ ወርዶ ፡ ከራሱ ፡ ላይ ፡ ጠብ ፡ አለበት ። ቀና ፡ ብሎ ፡ ቢያይ ፡ ውሺት ፡ ከበላዩ ፡ ቆማለች ። በዪ ፡ እኮ ፡ ነዪ ፡ ውረጂና ፡ እየመተርሽ ፡ አብሊኝ ! አላት ፡ እሷም ፡ እሺ ፡ ጌታዬ ፡ ብላ ፡ ወረደችና ፡ እየመተረች ፡ ስታበላ ፡ ቄይታ ፡ በመኻሉ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ዘወር ፡ ባለላት ፡ ሰዓት ፡ የአህዩትን ፡ ልብ ፡ ስልቅጥ ፡ አደ ረገችው ። መለስ ፡ አለና ፡ ቢያይ ፡ ልቧን ፡ አጣው ፡ ውሺት ፡ ልቧ ፡ ወዴት ፡



በዪ ፡ እኮ ፡ ነዪ ፡ ውረጂና ፡
እየመተርሽ ፡ አብሊኝ !

ሄደ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃት ። ልብ ፡ ባይኖራት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ልብማ ፡ ካላት ፡ አንተ ፡ ዘንድ ፡ መጥታ ፡ መቼ ፡ ትቀመጥ ፡ ነበር ፡ አለችው ። እሱም ፡ በፊት ፡ አይቶታልና ፡ ታመጪ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አምጪ ፡ አለዚያ ፡ አንቺን ም ፡ እበላሻለሁ ፡ አላት ። ምነው ፡ አያ ፡ ዥቦ ፡ እኔን ፡ በቅቤና ፡ በድልኽ ፡ አጣፍጠህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ አህዩት ፡ ደረቁን ፡ ትበላኛለህን ፡ አለ ችው ። ሆዳሜ ፡ እውነት ፡ መሰለውና ፡ ቅቤውና ፡ ድልኹ ፡ ከየት ፡ ይመ ጣል ፡ አላት ። ከመቤቴና ፡ ከጌታዬ ፡ ቤት ፡ እኔ ፡ ሂጄ ፡


—አመጣዋለኊ ፡ ስትል ፡ መለሰችለት ።

—ሄደሽ ፡ የጠፋሽ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማ ፡ ብዬ ፡ እጠራሻለሁ ፡

—እንኰዬ ፡ ልብ ፡ አጥቼ ፡

—በዬ ፡ እንግዲያውስ ፡ ሄደሽ ፡ አምጪ ፡ አላትና ፡ እሺ ፡ ብላ ፡ ሄዳ ፡ ቅርት ፡ ብትል ፡ እረ ፡ እንኰዬ ፡ ልብ ፡ አጥቼ ፡ እያለ ፡ ተጣራ ። ከመቤቴና ፡ ከጌታዬ ፡ ቤት ፡ ለምን ፡ ወጥቼ ፡ በማለት ፡ የስድብ ፡ ጕርፍ ፡ ታወርድበት ፡ ዠመር ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ተናደደና ፡ አንቺም ፡ እጐድፍ ፡ እኔም ፡ እጐ ድፍ ፡ እንገናኝ ፡ የለምን ፡ ብሎ ፡ ዝቶ ፡ ተመለሰ ።

ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ የውሻ ፡ ነገር ፡ መለቃቀም ፡ ትወዳ ለችና ፡ ስትልከሰከስ ፡ ሳይገባ ፡ የቀረ ፡ ከብት ፡ ወይም ፡ ምናምን ፡ ነገር ፡ ቢያጋጥመኝ ፡ ብሎ ፡ ሲሄድ ፡ አያ ፡ ዥቦ ፡ እጐድፍ ፡ አገኛት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ደነገጠችና ፡ ዐይኗ ፡ ፈጠጠ ። እሱም ፡ ውሺት ፡ እረ ፡ ዐይንሽ ፡ በምን ፡ እንደ



እስቲ ፡ እባክሽ ፡ እንደዚህ ፡ ከማረ ፡ እኔንም ፡ ንቀሺኝ ፡ አላቅ ።



ዚህ ፡ አማረልሽ ፡ አላት ። ጌታዬ ፤ በአሥር ፡ የአጋም ፡ እሾክ ፡ ተነቅሼ ፡ ነዋ ፡ አለችው ። እስቲ ፡ እባክሽን ፡ እንደዚህ ፡ ከማረ ፡ እኔንም ፡ ንቀሽኝ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃት ። እሷም ፡ ሄደችና ፡ ከጌታዋ ፡ አጥር ፡ ላይ ፡ ዐሥሩን ፡ የአጋም ፡ እሾኽ ፡ ሰብራ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አሥራ ፡ አመጣችና ፡ ሁለቱ ንም ፡ ዐይኑን ፡ ትቸከችከው ፡ ዠመር ። እንኰዬ ፡ ውሺት ፡ እረ ፡ እባክሽ ፡ አመመኝ ፡ አላት ። ተው ፡ ዝም ፡ በል ፡ ሲያጌጡ ፡ ይመላለጡ ፡ ነው ፡ ማማር ፡ እንዲያው ፡ ይገኝ ፡ ይመስልሃል ፡ ብላ ፡ ሁለቱንም ፡ ዐይኖቹን ፡ አጠፋቻቸው ። በመጨረሻውም ፡ እንግዲህ ፡ ዝም ፡ ብለህ ፡ ከዚህ ፡ ቈየኝ ፡ አለችው ። እሱም ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ካሳየችው ፡ ቦታ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ ጤፍ ፡ ወቂዎች ፡ ሆ ፡ ሆ ፡ ሲሉ ፡ ሰማ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እንኰዬ ፡ ውሺትን ፡ እረ ፡ ይኽ ፡ የምሰማው ፡ ሆታ ፡ ምንድነው ፡ እባክሽ ፡ አለና ፡ ጠየቃት ። ወንድሜ ፡ ዘመዶችህ ፡ ሠንጋ ፡ ጥለው ፡ በጕድጓ ፡ ከዳቢት ፡ ይማታሉ ! አለችው ። እንግዲያው ፡ እባክሽ ፡ እኔንም ፡ አድርሺኝ ፡ አላትና ፡ እየመ ራች ፡ ወስዳ ፡ ከጤፍ ፡ ወቂዎች ፡ መከከል ፡ አገባችው ። ወዲያው ፡ ጤፍ ፡



ይህ ፡ ዥብ ፡ ከወዴት ፡ መጣ ፡ እያሉ ፡ . . . ለመግደል ፡ ሲረ ረጡ ፡ እሷ ፡ የገበሬዎቹን ፡ ዳቦ ፡ ይዛ ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ ሄደች ።

ወቂዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ይኽ ፡ ዥብ ፡ ከወዴት ፡ መጣ ፡ እያሉ ፡ መውቂያ ፡ ሙጪ ሞውን ፡ እየመዘዙ ፡ ዥቡን ፡ ለመግደል ፡ ሲረራረጡ ፡ እሷ ፡ የገበሪዎቹን ፡ ዳቦ ፡ ይዛ ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ ተመለሰች ፡ ይባላል ።

፡ አህያና ፡ ዥብ ፡ በተላላነታቸው ፡ ከጕዳት ላይ ፡ ወደቁ ፡ ውሻ ፡ ግን ፡ በብልኀነቱና ፡ በትዕግሥቱ ፡ ከፈተና ፡ አልፎ ፡ ለመጠቀም ፡ በቃ ። ስለ ዚህ ፡ ትዕግሥት ፡ ትልቅ ፡ ገንዘብ ፡ መሆኑን ፡ መረዳት ፡ ነው ።

# የኽርብና ፡ የነብር ፡ ንስሓ ፡ አባት ፡ መያዝ ።

ነብርና ፡ ኽርብ ፡ ጕሬዛን ፡ የንስሓ ፡ አባት ፡ ያዙ ፡ ይባላል ። ነብርና ፡ ኽርብ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ባንድነት ፡ ንስሓቸውን ፡ ሊና ዘዙ ፡ ከጕሬዛ ፡ ዘንድ ፡ ሄዱና ፡ አንድ ፡ በአንድ ፡ ዘርዝረው ፡ የሠሩ ትን ፡ በደል ፡ ሁሉ ፡ ተናገሩ ። ጕሬዛም ፡ እኔ ፡ ለራሴ ፡ ደካማ ፡ የእግዚ አብሔር ፡ ሰው ፡ እንደናንተ ፡ ያለ ፡ ወንበዴ ፡ ሽፍታ ፡ አልችልም ፡ ሌላ ፡ የንስሐ ፡ አባት ፡ ያዙ ፡ አሰናብቻችኋለሁ ፡ አላቸው ። አያ ፡ ኽርቦም ፡ አቶ ፡ ነብሮም ፡ ምነው ፡ ምነው ፡ እኛ ፡ አክብረን ፡ ሽማግሌ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ የንስሓ ፡ አባት ፡ ብናደርገው ፡ ወንበዴዎች ፡ ሽፍቶች ፡ ይበለን ! የት ፡ አባቱ ፡ በል ፡ አትጥለውም ፡ ተባባሉና ፡ ነብሮ ፡ ጕሮሮውን ፡ አንቆ ፡ ሲያደርግ ፡ አያ ፡ ኽርቦ ፡ ደግሞ ፡ እብሽሽቱ ፡ ገብቶ ፡ ግንጥልጥል ፡ አደረገው ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ጕሬዛን ፡ ከገደሉ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ተመካከሩና ፡ የዝንጀሮ ፡ ንስሓ ፡ አባት ፡ ለመያዝ ፡ ተነሥተው ፡ ሄዱ ።

እንደ ፡ ተገናኙም ፡ በሉ ፡ ንስሐችሁን ፡ ንገሩኝ ፡ አለና ፡ ጠየቃ ቸው ። አያ ፡ ኽርቦም ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ከጕሬዎ ፡ ወጥቼ ፡ ስሰማራ ፡ ድን ገት ፡ የሰው ፡ አህያ ፡ እያጋጠመኝ ፡ በልቻለሁ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ግፍ ፡ አል ሠራሁም ፡ አለው ። አቶ ፡ ነብሮም ፡ እንደዚሁ ፡ እኔም ፡ ጫካ ፡ ለጫካ ፡ ስዞር ፡ ድንገት ፡ የሰው ፡ ፍዬል ፡ እያገኘሁ ፡ በልቻለሁ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ በደል ፡ የለኝም ፡ ብሎ ፡ ነገረው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዝንጀሮ ፡ ሥራችሁ ፡ ይኸ ፡ ከሆነማ ፡ እናንተ ፡ መቼ ፡ ትቻላላችሁ ፡ እኔ ፡ የብዙ ፡ ልጆች ፡ አባት ፡ ነኝ ፡ ኃጢአታችሁ ፡ ከባድ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የናንተን ፡ ንስሓ ፡ ማስተስረያ ፡ ጊዜ ፡ አላገኝምና ፡ ሌላ ፡ አባት ፡ ፈልጉ ፡ አላቸው ። አሁንም ፡ አያ ፡ ኽርብና ፡ አቶ ፡ ነብሮ ፡ ምክር ፡ ከደረጉ ፡ በኋላ ፡ ዝንጀሮን ፡ ይህ ፡ አታላይ ፡ ሲያላግጥብን ፡ ዝም ፡ ትለዋለህ ፡ በመባባል ፡ ለቀም ፡ አድር ገው ፡ ያዙት ። ምነው ፡ ጌቶቼ ፡ ምን ፡ አጠፋሁ ፡ እያለ ፡ ቢለፈልፍም ፡ ጥርቅም ፡ አድርገው ፡ በጥብቅ ፡ አሠሩት ። እሱም ፡ እንዳለቀቁት ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ግደሉኝ ፡ እንጂ ፡ መደብደብና ፡ መታሰር ፡ አልወድም ፡ አላቸው ። አንተን ፡ ማን ፡ ይገድላል ፡ ማሰር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሲሉ ፡ መለሱለት ። ዝንጀሮም ፡ መታሰርማ ፡ ደህና ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ገደል ፡ እንዳትስ ዱኝ ፡ ብቻ ፡ አማጥኛችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ ለመናቸው ። አያ ፡ ኽርብና ፡ አቶ ፡ ነብ ሮም ፡ ደግሞ ፡ አንተ ፡ እንዳልክ ፡ ሆነና ፡ እረ ፡ በል ፡ ያዘው ፡ ይህንን ፡ አሽፈ የኛን ፡ ንስሓ ፡ ያበረከተበትን ፡ ምክንያት ፡ ይንገረን ፡ አሉና ፡ በትራቸው ፡ አስ



ኪሰባበር ፡ ይዥልጡት ፡ ዥመር ። እሱም ፡ ጌቶቼ ፡ እባካችሁ ፡ በከንቱ ፡ አትድከሙ ፡ ክንዳችሁንም ፡ አይመማችሁ ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ ሆንኩ ፡ በትር ፡ ልማዴ ፡ ነው ፤ ይልቅስ ፡ ከገደል ፡ ሳይሆን ፡ ከውላላ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ወስዳችሁ ፡ ጣሉኝ ፡ አለና ፡ ለመናቸው ። ደግሞ ፡ አንተ ፡ እንደ ፡ ፈለግህና ፡ እንደ ፡ መረ ጥክ ፡ ሆነና ፡ ብለው ፡ አንጠልጥለው ፡ ወስደው ፡ ከገደሉ ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ አደረሱትና ፡ ገደል ፡ ልንጥልህ ፡ ነው ፡ እንግዲህ ፡ ንስሓችንን ፡ አስወርድል ን ፡ አሉት ። አዬ ፡ እኔማ ፡ ያልኳችሁን ፡ እንቢ ፡ ብላችሁ ፡ አስራችሁ ፡ አምጥ ታችሁኝ ፡ የለምን ፡ ስለዚህ ፡ አሁን ፡ ገደል ፡ መጣሌ ፡ ላይቀርልኝ ፡ ምንም ፡



አቶ ፡ ነብሮና ፡ አያ ፡ ኽርቦም ፡ አንተ ፡ ለመዳን ፡ ባትፈልግ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የታሰረበትን ፡ ፈተው ፡ ገደል ፡ ጣሉት ።

ቢሆን ፡ ሞቴ ፡ ናትና ፡ አልነግራችሁም ፡ ሲል ፡ መለሰላቸው ። ተው ፡ ለቀቅ ንህ ፡ ቢሉትም ፡ ሊላትምሩኝ ፡ ምን ፡ ያደርግልኛል ፡ እንቢ ፡ አለና ፡ እቅ ጩን ፡ አስረዳቸው ። አቶ ፡ ነብሮና ፡ አያ ፡ ኽርቦም ፡ አንተ ፡ ለመዳን ፡ ባትፈልግ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የታሰረበትን ፡ ፈተው ፡ ገደል ፡ ጣሉት ። ዝን ጀሮም ፡ ከገደሉ ፡ ተንከባሎ ፡ ወርዶ ፡ እሦስተኛው ፡ ዕርከን ፡ ላይ ፡ ሲደርስ ፡ ከቋጥኝ ፡ ላይ ፡ ቍጭ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ እያየ ፡ ድዱን ፡ ገልብጦ ፡ ስቆብ ቸውና ፡ አልምጦባቸው ፡ ከዘመዶቹ ፡ ተቀላቀለ ።

ደግሞ ፡ ሦስተኛ ፡ አቶ ፡ ነብር ፡ አያ ፡ ኽርቦን ፡ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ይሻለ ናል ፡ ትላለህ ፡ ሲል ፡ ምክር ፡ ጠየቀው ። እሱም ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ዐውቄ ፡ ከኔ ፡

ይልቅ ፡ አንተ ፡ አትሻልምን ፡ አለው ። ወዲያውኑ ፡ ከሚመከከሩበት ፡
ቦታ ፡ እንዳሉ ፡ ድንገት ፡ አንድ ፡ ወደል ፡ አህያ ፡ አገኛቸው ። አያ ፡ ኸቦና ፡
አቶ ፡ ነብሮም ፡ ከተቀመጡበት ፡ ብድግ ፡ ብለው ፡ እንዴት ፡ ዋልክ ፡ ሲሉ ፡
ሰላምታ ፡ አቀረቡለት ። እሱም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡
እረ ፡ ለመሆኑ ፡ ከወዴት ፡ ትመጣላችሁ ፡ አላቸው ። ዝንጀሮ ፡ ገድለን ፡
አሉት ። ምክንያቱን ፡ ለማወቅ ፡ ፈልጎ ፡ እባካችሁ ፡ ምን ፡ ቢያደርጋችሁ ፡
ነው ፡ አስረዱኝ ፡ ሲል ፡ ጠየቃቸው ። የነፍስ ፡ አባት ፡ ይዘነው ፡ የሠራነውን ፡
በደል ፡ ብንናዘዝለት ፡ ንስሓችንን ፡ ስላበረከተብን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

አህያም ፡ ለመሆኑ ፡ ምንድን ፡ ኖሯል ፡ ንስሓችሁ ፡ አለና ፡ ጠየቃ
ቸው ። አያ ፡ ኸቦ ፡ ያንተኑ ፡ ጓደኛ ፡ በልቼ ፡ ነዋ ! ፡ ሉካማ ፡ የሠራሁት ፡
ምን ፡ ኖሮ ፡ ነው ፡ አለ ። እረ ፡ ለመሆኑ ፡ ስንት ፡ አህያ ፡ ነው ፡ የበላኸው ፡ ቢለ
ው ፡ ዐሥር ፡ ሲል ፡ መለሰለት ። ታዲያ ፡ ዐሥሩ ፡ አንድ ፡ ካልሞላሁ ፡ ምን ፡
ንስሓ ፡ አለብህ ፡ አለው ። አያ ፡ ኸቦም ፡ እንግዲያው ፡ አንተኑ ፡ ደግሜ ፡
ንስሓ ፡ እገባለኋ ፡ አለው ። አህያውም ፡ ያለፈውን ፡ ንስሓህን ፡ ተወጥተህ ፡
እኔን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አንድ ፡ አትልምን ፡ የማለት ፡ ምክር ፡ ቢያቀርብለት ፡
ሐሳቡ ፡ መልከም ፡ ነው ፡ ያለፈውን ፡ ኀጢአቴን ፡ ለማስተስረይ ፡ ከማን ፡
ዘንድ ፡ መሄድ ፡ ይሻለኛል ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ቁመታቸው ፡ አጠር ፡ መል
ከቸው ፡ ጠየም ፡ አፍንጫቸው ፡ ጐመድ ፡ ከራሳቸው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ጥም
ጥማቸው ፡ ከበድ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ታገኛላችሁ ። እኔም ፡ አሁን ፡ ከዚያው ፡
መምጣቴ ፡ ነው ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ አድርጋችሁ ፡ ሂዱ ፡ መንገዱም ፡ ቢጠፋ
ባችሁ ፡ እኔ ፡ ከዚሁ ፡ ሆኜ ፡ አመለክታችኋለሁ ፡ አላቸው ።

እነሱም ፡ እንደ ፡ ተነገራቸው ፡ ተነሥተው ፡ ቢሄዱ ፡ ለምድር ፡ ለሰ
ማይ ፡ የከበዱ ፡ አባውንት ፡ ጥምጥማቸው ፡ ያማረ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ጠጣ ፡
ከሾላ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ አገኙዋቸው ። አቶ ፡ ነብሮና ፡ አያ ፡ ኸቦም ፡
መሬት ፡ በመሳም ፡ እጅ ፡ ነሥተው ፡ አባታችን ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዋሉ ፡ አሏቸው ።
ጠጣም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ እንዴት ፡ ዋላችሁ ፡ ልጆቼ ፡ ከወ
ዴት ፡ መጥታችኋል ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። ከሩቅ ፡ አገር ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡
መለሱለት ። ምነው ፡ በደኅናችሁ ፡ ነውን ፡ ቢላቸው ፡ የንስሓ ፡ ልጆች ፡
እንድንሆንም ፡ እርስዎም ፡ አባት ፡ እንዲሆኑን ፡ ብለን ፡ ነበር ። መልከም ፡
ምን ፡ ከፋኝ ፡ በሉ ፡ ትንሽ ፡ ዐረፍ ፡ በሉ ፡ አላቸው ። አቶ ፡ ነብሮና ፡ አያ ፡
ኸቦም ፡ ንስሓችንን ፡ ሳንናገር ፡ አንቀመጥም ፡ ብለው ፡ አስቸገሩት ። በዚህ ፡
ጊዜ ፡ እንግዲያውስ ፡ ደግ ፡ ነው ፡ የሠራችሁትን ፡ ኀጢአት ፡ ዘርዝሩችሁ ፡



ንገሩኝ ፡ አላቸው ። ሁለቱም ፡ ለየብቻቸው ፡ ንስሓቸውን ፡ ተናዘዙ ። እሱም ፡
ለዚህ ፡ ነው ፤ እንደዚህ ፡ የተጨነቃችሁት ፡ በሉ ፡ እንኳን ፡ መጣችሁልኝ ፤
አንድ ፡ ዕቃ ፡ እዋሻ ፡ ውስጥ ፡ አስቀምጬው ፡ የሚያወጣልኝ ፡ አጥቼ ፡
በጣም ፡ ተቸግሬ ፡ ነበረ ፡ ብሎ ፡ መጫኛውን ፡ ይዞ ፡ አቶ ፡ ነብሮንና ፡ አያ ፡
ኸቦን ፡ አስከትሎ ፡ ወደ ፡ ዋሻው ፡ ሄደ ። ከገደሉም ፡ አፋፍ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡
እንደ ፡ ምን ፡ አድርገን ፡ ነው ፡ የምንወርደው ፡ ብለው ፡ ጠጣን ፡ ጠየቁት ።
እሱም ፡ አያ ፡ ኸቦን ፡ አንተ ፡ ጐበዝም ፡ ደፋርም ፡ ነህ ፡ ስለዚህ ፡ እኔና ፡ አቶ ፡
ነብሮ ፡ ወገብህን ፡ በመጫኛ ፡ አስረን ፡ እንስድሃለን ፡ አንተም ፡ በእግርህ ፡
እየቈነጠጥህ ፡ ትረዳናለህና ፡ ቅር ፡ አይበልህ ። እኔ ፡ እንዳልወርድ ፡ ዐቅም ፡
የለኝ ፡ ደግሞም ፡ ሽማግሌ ፡ ነኝ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ጠንካራ ፡ ነህ ፡ ዕቃውም ፡
ከበድ ፡ ያለ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ትችለዋለህ ፡ ብሎ ፡ ባስረዳው ፡ ጊዜ ፡ እሺ ፡ በማ
ለት ፡ ትእዛዙን ፡ ተቀበለ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አያ ፡ ኸቦን ፡ ወገቡን ፡ ጥርቅም ፡
አድርገው ፡ በመጫኛ ፡ አስረው ፡ ለቀቁት ። እሱም ፡ ከተባለው ፡ ቦታ ፡ በደ
ረሰ ፡ ጊዜ ፡ እረ ፡ ዕቃም ፡ የለ ፡ መልሳችሁ ፡ አውጡኝ ፡ አላቸው ። እነ
ሱም ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ጠጋ ፡ ብለህ ፡ ባታይ ፡ ነው ፡ በቅጡ ፡ መርምር ፡
ብለው ፡ ተቈጡት ።

አንገቱን ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ፡ አድርጎ ፡ በሚመለከትበት ፡ ሰዓት ፡ ጠጣ ፡
እኛ ፡ ብቻችንን ፡ መጫኛውን ፡ ለመሳብና ፡ እሱን ፡ ማውጣት ፡ አንችልም ፡
ስለዚህ ፡ የንስሓ ፡ ልጆቼን ፡ ሰብስቤ ፡ እመጣና ፡ እናወጣዋለን ፤ አሁን ፡
ወደ ፡ ቤት ፡ እንሂድ ፡ አለው ። አቶ ፡ ነብሮም ፡ እውነትዎ ፡ ነው ፡ አባቴ ፡
ይኸንን ፡ ጥንበ ፡ በላ ፡ ማን ፡ ይችላል ፡ ብለው ፡ ነው ፡ አለውና ፡ መጫ
ኛውን ፡ ለቀው ፡ ወደ ፡ ጠጣው ፡ ቤት ፡ ተነሥተው ፡ ሄዱ ።

ከቤትም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ላቶ ፡ ነብሮ ፡ ግብዣ ፡ አደረገና ፡ ለመግ
ደል ፡ ስላሰበው ፡ እሎሎ ፡ አግሎ ፡ ሞራ ፡ አልብሶ ፡ እስቲ ፡ እንድትበረታ ፡
ይኸንን ፡ የተጠበሰ ፡ ሥጋ ፡ ትንሽ ፡ ብላ ፡ በኋላ ፡ ሄደን ፡ አያ ፡ ኸቦን ፡ እና
ወጣዋለን ፡ አለው ። አቶ ፡ ነብሮም ፡ የሥጋው ፡ ወዝ ፡ በጣም ፡ የሚያስጐ
መኝ ፡ ሆኖ ፡ ስላየው ፡ አነሣና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ዋጥ ፡ አደረገው ። ወዲያው ፡
ከባሕር ፡ ሆዱ ፡ ገብቶ ፡ አንጀቱን ፡ እኵማትሮ ፡ እዚያው ፡ ድብን ፡ አድርጎ ፡
ገደለው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጠጣ ፡ ያቶ ፡ ነብሮን ፡ ሬሳ ፡ ደላጎ ፡ ሸፈነና ፡ አያ ፡
ኸቦ ፡ ዘንድ ፡ ሄደ ።

ከአፋፍ ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ እንደምን ፡ ዋልህ ፡ በማለት ፡ ቢጠይቀው ፡
የሠራችሁኝን ፡ ሥራ ፡ አልረሳውም ፡ ቈይ ፡ ግድ ፡ የለም ፡ ሲል ፡ ዛተበት ።



አባታችን ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዋሉ ፡



እረ ፡ ዕቃም ፡ የለ ፡ መልሳችሁ ፡ አውጡኝ ።

ጠጣም ፡ የኔን ፡ ጭንቅ ፡ አንተ ፡ አላየህልኝም ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። ምነው ፡
ምን ፡ አገኘዎ ፡ ቢለው ፡ እረ ፡ ተወኝ ፡ ወንድሜ ፡ የገዛ ፡ ጓደኛህ ፡ ከዚህ ፡
እልፍ ፡ ባልን ፡ ጊዜ ፡ ሊገድለኝ ፡ አምላክ ፡ አላወጣኝም ፡ አለው ። ምክንያ
ቱም ፡ ባንተው ፡ ነገር ፡ ነው ፤ እኔ ፡ እናውጣው ፡ ስል ፡ እሱ ፡ ደግሞ ፡ አይ
ሆንም ፡ ብሎ ፡ ብርቱ ፡ ክርክር ፡ አድርገን ፡ ከጥል ፡ በመድረሳችን ፡ ነው ።

አይ ፡ አይ ፡ እሱ ፡ ዱሮውንም ፡ ጨካኝ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ መቼ ፡ ባሕሬውን ፡
አጣሁት ፡ ዐውቀዋለሁ ። አሁን ፡ ለመሆኑ ፡ ምን ፡ ይሻለኛል ፡ ይላሉ ፡ አባቴ ፡
አለ ። ጠጣም ፡ ሆዴ ፡ አልጨክን ፡ ስላለኝ ፡ ተደብቄ ፡ ላወጣህ ፡ መጣሁ ፡
አሁን ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ እሱ ፡ ወደማያገኝህ ፡ ሀገር ፡ ትሄድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
ላውጣህና ፡ ጥፋ ፡ አለው ። አያ ፡ ኸርቦም ፡ ከዚህ ፡ ብቻ ፡ ልውጣ ፡ እንጂ ፡
ተንሥቼ ፡ እልም ፡ ብዬ ፡ እጠፋለሁ ፡ ሲል ፡ መለሰለት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጠጣው ፡
ከገደሉ ፡ ውስጥ ፡ አወጣውና ፡ አያ ፡ ኸርቦ ፡ እንግዲህ ፡ አደራህን ፡ አጥብ
ቀህ ፡ ተሸሸግ ፡ ያየህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እኔንም ፡ ጭምር ፡ ታስገድለኛለህ ፡
አለው ። እሱም ፡ እረ ፡ አባቴ ፡ እንኳን ፡ ከዚህ ፡ የወጣሁ ፡ እንጂ ፡ ሁለተኛ ፡
በዚህ ፡ ቀበሌ ፡ ይገኛል ፡ ብለው ፡ አይጠርጥሩኝ ፡ አለ ። ጠጣም ፡



መለስ ፡ አድርጎ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ለጊዜው ፡ ሩቅ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርምና ፡
ከቤት ፡ ሄደን ፡ ምሳህን ፡ በልተህ ፡ ትሄዳለህ ፡ አለው ። አያ ፡ ኸርቦም ፡
የሆዱ ፡ ነገር ፡ ስለሚብሰበት ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ተከተለው ።

እቤትም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ዐጥንት ፡ ሰጠውና ፡ አንተ ፡ ይኽንን ፡
ብላ ፡ እኔ ፡ ኸራትህን ፡ ልቀመልህ ፡ ግን ፡ ገልመጥ ፡ እንዳትል ፡ አለው ።
እሱም ፡ ያሉኝን ፡ እፈጽማለሁ ፡ ብሎ ፡ ዐጥንቱን ፡ ይዞ ፡ ሲጋግጥ ፡
ጠጣ ፡ ኸማት ፡ አቅርቦ ፡ ያያ ፡ ኸርቦን ፡ ኸራት ፡ ከነብሮ ፡ የፊት ፡ እግር ፡
ጋራ ፡ ግጥም ፡ አድርጎ ፡ ይሰፋ ፡ ዠመር ። ወዲያው ፡ እረ ፡ አመመኝ ፡
ብሎ ፡ ጮኸ ። እንግዲያው ፡ ዐጥንቱን ፡ መልሳ ፡ አለው ። ሆዱ ፡ እያማ
ማው ፡ ሕመሙን ፡ ታግሦ ፡ ዝም ፡ ሲል ፡ ጥርቅም ፡ አድርጎ ፡ ሰፍቶ ፡ ከ
ጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ነዎር ፡ ጌታዬ ፡ አቶ ፡ ነብሮ ፡ ከወዴት ፡ መጣህልኝ ፡
ብሎ ፡ አቶ ፡ ጠጣ ፡ ብድግ ፡ አለ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ኸርቦ ፡ መለስ ፡ ብሎ ፡
ቢያይ ፡ እውነትም ፡ አቶ ፡ ነብሮን ፡ አጠገቡ ፡ ሆኖ ፡ አገኘው ። የነከሰ
ውም ፡ መሰለውና ፡ ዘሎ ፡ ሬሳውን ፡ ከማጀት ፡ እየጐተተ ፡ መንጥቆ ፡
አውጥቶ ፡ ነፍሱን ፡ አጥቶ ፡ ሲክነፈነፍ ፡ ገደል ፡ ገብቶ ፡ ሞተ ፡ ይባላል ።

ዘሎ ፡ የነከሰው ፡ መሰለው
ና ፡ ያንን ፡ ያያ ፡ ነብሮን ፡
ሬሳ ፡ ከማጀት ፡ እየጐተተ ፡
መንጥቆ ፡ አውጥቶ ፡ ነፍሱን ፡
አጥቶ ፡ ሲክነፈነፍ ፡ ገደል ፡
ገባ ።



፨ እጸድቅ ፡ ያለ ፡ መንኰሰ ፡ እከስ ፡ ያለ ፡ ታግሦ ፡ እንደሚባለው ፡
ሁሉ ፡ የንስሐ ፡ አባትን ፡ ትእዛዝ ፡ በዛ ፡ ከበደ ፡ ሳይሉ ፡ ኀጢአት ፡ እን
ዳሰረይ ፡ መፈጸም ፡ ይገባል ። ከብዙ ፡ ጉልበት ፡ ትንሽ ፡ ብልኀት ፡ ይበ
ልጣል ።

# አንዲት ፡ ባሏን ፡ የናቀች ፡ ሴት ።


አንዲት ፡ ሴት ፡ አንድ ፡ ባለሚያ ፡ አራሽና ፡ በሰፊው ፡ አምራች ፡ ገበሬ ፡ አግብታ ፡ ሌማቷን ፡ በእንጀራ ፡ ሞልታ ፡ በመብላት ፡ ጠላውን ፡ ጐዝጉዝ ፡ በሚያኽል ፡ ጋን ፡ ጠምቃ ፡ ባቦሬ ፡ እየደነበቀች ፡ በመጠጣት ፡ ተንቀባራ ፡ እብሪት ፡ ስላደረባት ፡ ያለመጠን ፡ ጠገበች ። የስንዴው ፡ እንባበሮ ፡ ልቧን ፡ ደፈነው ፤ የማይሆን ፡ የማይሆንም ፡ ነገር ፡ ያሳስባት ፡ ዠመር ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከመጀነኗና ፡ ከኵራቷ ፡ የተነሣ ፡ በዜያ ፡ ገበሬ ፡ ባሏ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ወንደ ፡ ላጤ ፡ ማንዘራሽ ፡ መንደር ፡ አውሌ ፡ የሆነ ፡ ጐረምሳ ፡ ለመደችና ፡ ልቧ ፡ ጨርሶ ፡ ወደሱ ፡ ሆነ ። ባሏን ፡ ፈጽማ ፡ ናቀችው ፤ እንዲያውም ፡ ከእብሪቷ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ከንቶ ፡ ጋራ ፡ አላድርም ፡ እያለች ፡ የምትተኛው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ለብቻዋ ፡ ሆነ ።

ባለቤቷም ፡ እየተናደደና ፡ እየጨሰ ፡ ታግሦ ፡ ሲኖር ፡ ሳለ ፡ በመጨረሻው ፡ ባሏን ፡ ጥላ ፡ ለመሄድ ፡ ከወንደ ፡ ላጤው ፡ ጋራ ፡ ምክር ፡ አደረገች ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀንም ፡ ሌሊት ፡ በውድቅት ፡ ይህንኑ ፡ የጠላችውን ፡ ባሏን ፡ ከእንቅልፉ ፡ ቀስቅሳ ፡ አንተ ፡ እኔ ፡ ዛሬ ፡ ሕልም ፡ አየሁ ፡ አለችው ። ምን ፡ ሕልም ፡ አየሽ ፡ ምንስ ፡ አለሽ ፡ አለና ፡ ቢጠይቃት ፡ ፈረሰኛው ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ተገልጦ ፡ በፈረሱ ፡ ተቀምጦ ፡ ጦርና ፡ ጐራዴውን ፡ ይዞ ፡ ከፊቴ ፡ ቆሞ ፡ አንቺ ፡ ልጅ ፡ በመልክ ፡ እንዲህ ፡ ስታምሪ ፡ ከዚህ ፡ ከንፍጣም ፡ እንዴት ፡ ትኖሪ ፡ አለና ፡ ነገረኝ ፡ ስትል ፡ የልቧናዋን ፡ እብሪት ፡ አስረዳችው ። እሱም ፡ እባክሽን ፡ እንቴ ፡ ቅዠት ፡ ነው ፡ አርፈሽ ፡ ተኚ ፡ አላት ። እረ ፡ የለም ፡ ወንድሜ ፡ ቅዠትም ፡ አይደለ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ፈረሰኛው ፡ በገሃድ ፡ ተገልጦ ፡ ነው ፡ የነገረኝ ፡ ክለች ፡ በኋላ ፡ ሁለቱም ፡ ተመልሰው ፡ ተኙ ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ወንድዮው ፡ በጣም ፡ ተናዶ ፡ ነበርና ፡ እንቅልፍ ፡ አልወስድ ፡ ብሎት ፡ ሰውነቱ ፡ በንዴት ፡ መጨስ ፡ መቃጠል ፡ መብገንገን ፡ ማረር ፡ ዠመረ ። ጥቂት ፡ ቈይቶም ፡ እሷን ፡ እንቅልፍ ፡ ድብን ፡ አድርጎ ፡ ሲይዛት ፡ አየና ፡ አንቺ ፡ አንቺ ፡ ብሎ ፡ ቀስቀሰና ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ከተኛን ፡ ወዲህ ፡ ምን ፡ ሕልም ፡ አየሽ ፡ አላት ። ከቅድሙስ ፡ ወዲህ ፡ ምንም ፡ አላየሁ ፡ ያው ፡ ነው ፡ በማለት ፡ መለሰችለት ። እንግዲያውስ ፡ እኔ ፡ ግሩም ፡ የሆነ ፡ ሕልም ፡ አይቻለሁ ፡ ተነሥተሽ ፡ እሳት ፡ አንጂና ፡ ልንገርሽ ፡ ትፈችልኛለሽ ፡ አላት ። እሺ ፡ አለችና ፡ ተነሥታ ፡ ያንን ፡ እሳት ፡ አንድዳ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርጎ ፡ ነው ፡ ያሳየህ ፡ ስትል ፡ ጠየቀችው ። እሱም ፡ ብርሃን ፡ ለብሶ ፡ ብርሃን ፡ ተጐናጽፎ ፡ ፊቱ ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ የሚያበራ ፡ ጐልማሳ ፡ መጥቶ ፡ ከፊቴ ፡ ቆሞ ፡



የኔስ ፡ ቅዠት ፡ አይደለም ፡ ቅዠትስ ፡ ያንቺ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ሬቻ ፡ እያገላበጠ ፡ ወቃት ።

ከንቶ ፡ ተኝታ ፡ ሌላ ፡ ታማራት ፡ ተው ፡ ተነሣና ፡ በዱላ ፡ በላት ፡ አለና ፡ ነገረኝ ፡ አላት ። አይ ፡ እባክህ ፡ ቅገርት ፡ ነው ፡ ተኛ ፡ አለችው ። የኔስ ፡ ቅዠትም ፡ አይደለ ፡ ቅዠቱስ ፡ ያንቺ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የጠወለገ ፡ የወይራ ፡ አርጩሜ ፡ አንሥቶ ፡ በደረቅ ፡ ሌሊት ፡ እንደ ፡ ሬቻ ፡ እያገላበጠ ፡ ወቃት ። ገላጋይም ፡ እንዳይመጣ ፡ እኩለ ፡ ሌሊት ፡ ሆነ ፡ ደግሞም ፡ በሩን ፡ አጥብቆ ፡ በመወርወሪያ ፡ ቀርቅሮት ፡ ነበርና ፡ ብትጮኽም ፡ የሚደርስላትና ፡ የሚያድናት ፡ ሰው ፡ አጥታ ፡ ተቸገረች ። ስለዚህ ፡ እንደማይሆንላት ፡ በተረዳችው ፡ ጊዜ ፡ እረ ፡ ተው ፡ እባክህ ፡ በተሰቀለው ፡ የዛሬን ፡ ብቻ ፡ አለችው ። እሱም ፡ ቀና ፡ አለና ፡ ወደ ፡ ጣሪያው ፡ ቢመለከት ፡ የበሬ ፡ ጅራፉን ፡ ከግድግዳው ፡ ላይ ፡ ተሰቅሎ ፡ አየ ። ያንን ፡ አውርዶ ፡ ተለቀቀባት ፤ ልቧም ፡ ጥፍት ፡ እስኪል ፡ ድረስ ፡ ገርፎ ፡ ለቀቃት ፡ ይባላል ።

፨ በተረቱበት ፡ ይረቱበት ፡ እንደሚባለው ፡ ተረት ፡ እሷው ፡ በመጣችው ፡ ቅዠት ፡ እሱ ፡ አንገሯቱን ፡ አራሰበት ። ባልን ፡ ማክበርና ፡ መውደድ ፡ ይገባል ፡ ሴሰኝነትም ፡ በመጽሐፍ ፡ የተከለከለና ፡ ብርቱ ፡ ኀጢአት ፡ መሆኑን ፡ አለመርሳት ፡ ነው ።

# አንበሳና ፡ አንዲት ፡ ሴት ።

አንዲት ፡ ጌኔሆይ ፡ ድንቅነሽ ፡ የምትባል ፡ ሴት ፡ ባሏ ፡ የጎረ ፡ ቤት ፡ ሴት ፡ ወዳጅ ፡ አበጅቶ ፡ በመብልና ፡ በመጠጥ ፡ ጭምር ፡ እየተዳለለ ፡ ልቡ ፡ ስለ ፡ ተማረከ ፡ ጨቅጫቃ ፡ ሆኖባት ፡ ተቸግራ ፡ ትኖር ፡ ነበር ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከመጨነቋ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ምክር ፡ ዐዋቂ ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ ሄዳ ፡ ብትጠይቅ ፡ የአንበሳ ፡ ቅንድብ ፡ ከመጣሽ ፡ እኔ ፡ መድኀኒት ፡ አደርግልሻለሁ ፡ አላት ። ጌኔሆይ ፡ ድንቅነሽም ፡ ይኸንንማ ፡ ከወዴት ፡ አባቴ ፡ አግኝቼ ፡ አለችው ። ዐዋቂውም ፡ እንግዲያውማ ፡ ምን ፡ ላደርግ ፡ እችላለሁ ፡ ያለሱ ፡ አይሆንም ፡ አላት ። ጌኔሆይ ፡ ድንቅነሽ ፡ ይኸንን ፡ በመስማቷ ፡ እየተከከዘች ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ ስትመለስ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ወዳጅዋ ፡ የሆነችውን ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ አገኘችና ፡ ከወዴት ፡ ትመጫለሽ ፡ አለቻት ። እሷም ፡ የባሌ ፡ ባሕርይ ፡ ስለ ፡ ተለዋወጠብኝ ፡ ዐዋቂ ፡ ዘንድ ፡ ብሄድ ፡ ያንበሳ ፡ ቅንድብ ፡ ካላመጣሽ ፡ አይሆንም ፡ አለኝ ፡ ስለዚህ ፡ በጣም ፡ ተቸግሬያለሁና ፡ ከምን ፡ ቦታ ፡ እንደሚገኝ ፡ እባክሽ ፡ ምክር ፡ አካፍሊኝ ፡ ስትል ፡ ጠየቀቻት ። ሴቲቱም ፡ በሬ ፡ አርደሽ ፡ አንድ ፡ አንዱን ፡ ብልት ፡ እየያዝሽ ፡ ከጫካ ፡ ከሄድሽ ፡ አታጭውም ፡ የፈለግሽውንም ፡ ታገኚለሽ ፡ አለቻት ።

ባለጕዳይዋም ፡ ይህነን ፡ ምክር ፡ ተቀብላ ፡ ከግል ፡ ከብቷ ፡ ውስጥ ፡ ደኅናውን ፡ በሬ ፡ መርጣ ፡ አሳርዳ ፡ ታናሹን ፡ በሙዳ ፡ በሙዳ ፡ ከፋፍላ ፡ ተሸክማ ፡ እጫካ ፡ ሄዳ ፡ ስትዞር ፡ ስትዞር ፡ ውላ ፡ አንድ ፡ አንበሳ ፡ አገኘች። ገና ፡ በሩቅ ፡ ሳለ ፡ በቍጣ ፡ አስተያየቱ ፡ በይኑ ፡ መቅላት ፡ በግርማው ፡ ማስፈራት ፡ ደንግጣ ፡ በመንቀጥቀጥ ፡ ቁማ ፡ ቀረች ።

እሱም ፡ ጋማውን ፡ ነስንሶ ፡ ተቈጥቶ ፡ ወደሷ ፡ መንገድ ፡ ጀመረ ። ድንቅነሽም ፡ አጠገቧ ፡ ሊደርስ ፡ ትንሽ ፡ ሲቀረው ፡ ሥጋውን ፡ ጣል ፡ አደረገችለትና ፡ ራቅ ፡ ብላ ፡ ትመለከተው ፡ ጀመር ። የአራዊት ፡ ንጉሥም ፡



ድንቅነሽም ፡ አጠገቧ ፡ ሊደርስ ፡ ትንሽ ፡ ሲቀረው ፡ ሥጋውን ፡ ጣል ፡ አደረገችለትና ፡ ራቅ ፡ ብላ ፡ ትመለከተው ፡ ጀመር ።



ዝም ፡ ብሎ ፡ ሥጋውን ፡ መብላት ፡ ያዘ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጌኔሆይ ፡ ድንቅነሽ ፡ ቶሎ ፡ ብላ ፡ ሥጋውን ፡ በልቶ ፡ ሳይጨርስ ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ ተመለሰች።

በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ልማዷ ፡ ከዚያው ፡ ሥጋ ፡ ይዛለት ፡ ሄደች ። አንበሳውም ፡ ስትመጣ ፡ አያትና ፡ ጠጋ ፡ ጠጋ ፡ ሲላት ፡ የያዘችውን ፡ ሥጋ ፡ ወረወረችለት ። እንደ ፡ ልማድ ፡ አድርጎ ፡ እሷን ፡ እሷን ፡ እያየ ፡ ሥጋውን ፡ መብላት ፡ ጀመረ ። እስኪጨርስም ፡ ድረስ ፡ አጠገቡ ፡ ቆማ ፡ ነበርና ፡ በጠገበ ፡ ጊዜ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ አያት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ ተመለሰች ።

ዳግም ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ልማዷ ፡ ከዚያው ፡ ሥጋ ፡ ይዛለት ፡ ሄደች ። አንበሳውም ፡ ልምድ ፡ አድርጎ ፡ ይጠባበቃት ፡ ነበርና ፡ የርሷን ፡ መምጣት ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ ዐውቋት ፡ ጭራውን ፡ ነሰነሰ ። ጌኔሆይ ፡ ድንቅነሽም ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ እየተመላለሰች ፡ ሥጋው ፡ እስኪያልቅ ፡ ድረስ ፡ ከመገበችው ፡ በኋላ ፡ መፍራቷ ፡ ቀረና ፡ ምግቡን ፡ በእጅዋ ፡ ይዛ ፡ ልታበላውና ፡ ልታጕርሠው ፡ ደፈረች ። በልቶ ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላም ፡ ታከክ ፡ ታከክ ፡ እያለ ፡ በጠጕሩ ፡ ስለሚያሻሻት ፡ ሁለቱም ፡ ተላመዱ ፤ ወዝም ፡ ተጣገቡ ። ስለዚህ ፡ አብራው ፡ ውላ ፡ ማታ ፡ እቤቷ ፡ ሄዳ ፡ አደረችና ፡ በራተኛው ፡ ቀን ፡ እንደዚያው ፡ እንደ ፡ መሰንበቻዋ ፡ ያለውን ፡ ሥጋ ፡ ሁሉ ፡ ልቅም ፡ አድርጋ ፡ ይዛለት ፡ እጫካው ፡ ገባች ። ገና ፡ በሩቅ ፡ ስትመጣ ፡ ባያት ፡ ጊዜም ፡ ከደስታው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ እየፈነደቀ ፡ እየበረቀ ፡ ካጠገቧ ፡ ደረሰ ። ጌኔሆይ ፡ ድንቅነሽም ፡ ባለመፍራት ፡ ዝም ፡ ብላ ፡ እያስተዋለች ፡ ሥጋውን ፡ ሳትሰጥ ፡ አቈየችው ። ቢሆንም ፡ በማዘግየቷ ፡ ሳይቈጣ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ይለማመጣት ፡ ጀመረ ። እሷም ፡ እጅግ ፡ ደጅ ፡ ሳታስጠና ፡ ምግቡን ፡ አቀበለችው ። በልቶ ፡ እንደ ፡ ጠገበ ፡ ከላይዋ ፡ ላይ ፡

ጌኔሆይ ፡ ድንቅነሽም ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ መፍራቷ ፡ ቀረና ፡ ምግቡን ፡ በእጅዋ ፡ ይዛ ፡ ታበላውና ፡ ታጕርሠው ፡ ጀመረች ።



ተደግፎ ፣ ሽልብ ፣ አደረገው ፤ እንቅልፍም ፣ ድብን ፣ አድርጎ ፣ ያዘው ፤ በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ቅንድቡን ፣ ንጭት ፣ አደረገችው ። እሱም ፣ ደንግጦ ፣ ምን ፣ ነካኝ ፣ አለና ፣ ተነሥቶ ፣ ቢያይ ፣ ቀላቢው ፣ ሆነችበት ። ጥቂት ፣ ቄይታም ፣ የመጣችበትን ፣ ጒዳይ ፣ ስለ ፣ ጨረሰች ፣ አንበሳውን ፣ አሻሽታ ፣ አበብላ ፣ አገርማ ፣ ወደ ፣ ቤቷ ፣ ተመለሰች ።



በልቶ ፣ እንደ ፣ ጠገበ ፣ ከላ
ይዋ ፣ ላይ ፣ ተደግፎ ፣ እንቅል
ፍ ፣ ድብን ፣ አድርጎ ፣ ያዘው ።

ሳታርፍ ፣ ወዲያው ፣ እዚያ ፣ ዐዋቂ ፣ ሰው ፣ ዘንድ ፣ ሄደችና ፣ ያልኸኝን ፣ ያንበሳውን ፣ ቅንድብ ፣ አመጣሁ ፣ አለችው ። እሱም ፣ ተገርሞ ፣ እንደ ፣ ምን ፣ አድርገሽ ፣ አገኘሽው ፣ እባክሽ ፣ እስቲ ፣ ንገሪኝ ፣ አላት ። ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ከሥር ፣ ሥምሯ ፣ ምንም ፣ ሳይቀራት ፣ ሁሉንም ፣ ዘርዝራ ፣ አስረዳችው ። ሰውዮውም ፣ በጣም ፣ አድርጎ ፣ ተደነቀ ፣ ተገረመም ።

እሱ ፣ ግን ፣ አስቀድሞ ፣ ይህንን ፣ አምጪ ፣ ያላት ፣ አታገኝም ፣ በማለት ፣ ነበርና ፣ መሸነፉን ፣ ባወቀ ፣ ጊዜ ፣ አንቺ ፣ የአራዊትን ፣ ንጉሥ ፣ ያገረምሽ ፣ ለባልሽ ፣ ምን ፣ ያቅተኛል ፣ ብለሽ ፣ ነው ፣ እኔ ፣ ዘንድ ፣ የመጣሽው ፣ አሁንም ፣ አንበሳውን ፣ እንደ ፣ አለሰለሽው ፣ ባልሽንም ፣ አባብለሽ ፣ ተለማምጠሽ ፣ ማሸነፍ ፣ ትችያለሽ ፣ ምግብ ፣ እንኳን ፣ ሰው ፣ አውሬ ፣ ያለምዳል ፣ ወንድም ፣ ጕኑን ፣ ቢጠብቁለት ፣ ምግቡንም ፣ ቢያጓድሉበት ፣ ይወዳል ፣ ከዚህም ፣ በቀር ፣ ሌላ ፣ መድኀኒት ፣ የለውም ፣ ብሎ ፣ መከራት ። ጌኤሆይ ፣ ድንቅነሽም ፣ ተመልሳ ፣ ቃሉን ፣ ተቀብላ ፣ መልክም ፣ ምግብና ፣ መጠጥ ፣ እያዘጋጀች ፣ በመስጠት ፣ እየተለማመጠች ፣ ሲቈጣትም ፣ እየቻለች ፣ ተስማምታ ፣ ቤቷን ፣ ንብረቷን ፣ አደርጅታ ፣ በሰላምና ፣ በጤና ፣ ከባሏ ፣ ጋራ ፣ ኖረች ፣ ይባላል ።

፨ ልጆቼ ፣ ሆይ ፣ ሞኝን ፣ እንዳይጠላህ ፣ አትምከረው ፣ ብልኅ ፣ ግን ፣ በጥበብ ፣ ላይ ፣ ጥበብ ፣ መጨመር ፣ ስለሚሻ ፣ ምክርህንና ፣ ተግሣጽህን ፣ በደስታ ፣ ይቀበልሃል ፣ ተብሎ ፣ በተነገረው ፣ ለመጠቀም ፣ አትበዝኑ ።



# የሦስት ፡ ሌቦች ፡ ምክር ።

ሦስት ፣ ሌቦች ፣ ለስርቆት ፣ ተመካከረው ፣ ወደ ፣ አንድ ፣ ሀገር ፣ ሄዱ ። ከሚሰርቁበትም ፣ ቤት ፣ በደረሱ ፣ ጊዜ ፣ ምን ፣ ይሻለናል ፣ ተባብለው ፣ ዘዴ ፣ ፈጠሩ ። ከዚህም ፣ ለመስረቅ ፣ ካሰቡበት ፣ ቤት ፣ ድግስ ፣ ስለ ፣ ነበረ ፣ ከሦስቱ ፣ አንዱ ፣ አዝማሪ ፣ ሆኖ ፣ ሊገባና ፣ የተሰበሰበውን ፣ ሰው ፣ ሊያጫውት ፣ በዚያ ፣ ጊዜም ፣ ሁለቱ ፣ ከብቶቹን ፣ ይዘው ፣ ሊሄዱ ፣ ምክር ፣ አደረጉ ።

እነሱም ፣ ስም ፣ ለስም ፣ አይተዋወቁ ፣ ኖሮ ፣ ያ ፣ አዝማሪ ፣ የሆነው ፣ በኋላ ፣ ማ ፣ ብዬ ፣ ልጥራችሁ ፣ አላቸው ፤ ከሁለቱ ፣ አንደኛው ፣ ተገኙ ፣ በለኝ ፣ አለው ። ከዚህ ፣ በኋላ ፣ አዝማሪው ፣ ገብቶ ፣ ጨዋታውን ፣ ዠመረ ። ባለቤቶቹም ፣ የእውነት ፣ መስሏቸው ፣ አፋቸውን ፣ ከፍተው ፣ ሲያዳምጡ ፣ እንደዚህ ፣ ሲል ፣ ዘፈነ ።

ወንዱ ፣ ሽማግሌ ፤
ሴቲቱም ፣ አሮጊት ፤
አጥሩም ፣ ከመሸሻ ፤
ውሻዋም ፣ ቡችላ ፤
ነዪ ፣ ኸቲ ፣ ነዪ ፣ ኸቲ ፤
ነዪ ፣ እኒ ፣ ኒ ፤



ያቺ ፣ ውሻ ፣ ዐይን ፣ ዐይኑን ፣
እያየች ፣ ትጠብቀው ፣ ዠመር ።

በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ያች ፣ ውሻ ፣ የጠራት ፣ መስሏት ፣ ጭራዋን ፣ እየቈላች ፣ ዐይን ፣ ዐይኑን ፣ እያየች ፣ ትጠብቀው ፣ ዠመር ። በፊት ፣ ግን ፣ ቡፍ ፣ ቡፍ ፣ እያለች ፣ አስቸግራው ፣ ነበር ። በጨዋታው ፣ ሰዓት ፣ እነዚያ ፣ ሁለቱ ፣ ሌቦች ፣ ከብቶቹን ፣ ይዘው ፣ ሄደው ፣ ኖሮ ፣ እረኛው ፣ እደጅ ፣ ወጥቶ ፣ ከበረቱ ፣ ውስጥ ፣ አንድም ፣ ከብት ፣ ስላጣ ፣ ተመልሶ ፣ ሲሮጥ ፣ ገብቶ ፣ እረ ፣ በበረቱ ፣ አንድም ፣ ከብት ፣ የለ ፣ ብሎ ፣ ተናገረ ፤ ባለቤቶቹም ፣ ደነገጡ ፣ ጩኸትም ፣ ሆነ ፣ አገሩ ፣ ሁሉ ፣ ተሸበረ ። ይህን ፣ ጊዜ ፣ ያ ፣ ሌባ ፣ አዝማሪ ፣ አትጩኹ ፣ እያንዳንዳችን ፣ በያለበት ፣ ተበታትነን ፣ እንሂ

ድና ፡ እንፈልግ ፡ እናንተም ፡ ያገኛችሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተገኙ ፡ በሉና ፡ ንገሩኝ ፡ እኔም ፡ ባገኛቸው ፡ ተገኙ ፡ እላችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ ከጠገባቸው ፡ ሄደ ። እልፍ ፡ አለናም ፡ ከተራራ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ እረ ፡ ተገኙ ፡ እያለ ፡ ይጣራ ፡ ዠመር ። እነዚያም ፡ ከብቶቻቸው ፡ የጠፉባቸው ፡ ሰዎች ፡ ደስታ ፡ ይዟቸው ፡ በሩጫ ፡ አጠገቡ ፡ ደረሱ ። እሱ ፡ ግን ፡ የጠራው ፡ ባልደረባውን ፡ ነበርና ፡ ባለቤቶቹም ፡ የታሉ ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ፡ እኔ ፡ የት ፡ አየኋቸው ፡ አላየሁም ፡ አለና ፡ መለሰላቸው ። ታዲያ ፡ ለምን ፡ ተገኙ ፡ አልክና ፡ አታለልከን ፡ ብለው ፡ ያዙት ። ለጊዜው ፡ በውስጡ ፡ ተንኰል ፡ ነገር ፡ በመኖሩ ፡ ደነገጠ ፡ ይዘውትም ፡ እመልከኛ ፡ ዘንድ ፡ ሄደው ፡ ጌታችን ፡ ሆይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሳይዎ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ በመገርመሪያው ፡ ከቤታችን ፡ ሲመጣ ፡ ከመሸ ፡ ሰዓት ፡ ከተላለፈ ፡ በላይ ፡ ነው ፡ ደግሞ ፡ ከብቶቻችን ፡ ስለ ፡ ጠፉብን ፡ እኔም ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ እፈልጋለሁ ፡ በተገኙም ፡ ጊዜ ፡ እጠራችኋለሁ ፡ እናንተም ፡ ስታገኙ ፡ ተገኙ ፡ በሉኝ ፡ ብሎን ፡ ተነሥተን ፡ ስንፈልግ ፡ ተገኙ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ። አጠገቡ ፡ ብንደርስ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ከብት ፡ አልነበረም ፡ ስለዚህ ፡ ከብቶቻችንን ፡ የወሰደ ፡ እሱ ፡ ነውና ፡ ይክፈለን ፡ ብለን ፡ ነው ፡ ያመጣነው ፡ በማለት ፡ አመለከቱ ። ዳኛውም ፡ የነሱን ፡ ነገር ፡ አቁሞ ፡ በተራው ፡ ሰውዮውን ፡ እህ ፡ ወንድሜ ፡ ይህ ፡ የሚሉት ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ መሆኑን ፡ ታምናለህ ፡ ወይስ ፡ ትክዳለህ ፡ መልሱን ፡ ስጠን ፡ አለና ፡ ጠየቀው ።

ሰውዮውም ፡ እኔ ፡ ለራሴ ፡ ከብት ፡ የሚባል ፡ አላየሁም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ልጄን ፡ መጣራቴ ፡ ነበረ ፡ የልጁ ፡ ስም ፡ ተገኙ ፡ ነው ። ተገኙ ፡ ያልኩበት ፡ ምክንያቱም ፡ ልጆቼ ፡ ሁሉ ፡ አልቀውብኝ ፡ በመጨረሻ ፡ ስለ ፡ ወለድኩት ፡ ነው ፡ ስለዚህም ፡ ተገኙ ፡ ብዬ ፡ ልጄን ፡ ብጠራ ፡ ደብድበው ፡ አስረው ፡ ይኸው ፡ እንደሚያዩት ፡ ከርስዎ ፡ ዘንድ ፡ አምጥተው ፡ እንደ ፡ ወንጀለኛ ፡ አቁመውኛል ፡ ሲል ፡ መለሰለት ።

መልከኛውም ፡ ነገሩን ፡ አዳምጦ ፡ ሰምቶ ፡ ተገኙ ፡ ብሎ ፡ ልጁን ፡ በጠራ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ደብድባችሁ ፡ አስራችሁ ፡ ያመጣችሁት ፡ ይኸ ፡ በደልና ፡ ጥፋት ፡ የናንተው ፡ ነው ፡ ለሱም ፡ ትክሳላችሁ ፡ እናንተም ፡ ትቀጣላችሁ ፡ በማለት ፡ ፈረደባቸው ። የከብቶቹ ፡ ባለቤቶችም ፡ መቀጫቸውን ፡ ተቀጥተው ፡ ለሰውዮውም ፡ ክሰው ፡ የበለጠ ፡ ኪሳራ ፡ አግኝቷቸው ፡ በንዴት ፡ ላይ ፡ ንዴት ፡ ጨምረው ፡ እያዘኑና ፡ እያለቀሱ ፡ ወደየቤታቸው ፡ ሄዱ ።



ያም ፡ ሰው ፡ ከዚያ ፡ ተነሥቶ ፡ ባልደረቦቹን ፡ እየዞረ ፡ ቢፈልግ ፡ ስለ ፡ አጣቸው ፡ አዬ ፡ እንግዲህ ፡ ምን ፡ አደርጋለሁ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመለሰ ።

እነኛም ፡ ሰርቀው ፡ ይዘው ፡ የሄዱት ፡ ሁለቱ ፡ ሌቦች ፡ በከብቶቹ ፡ የመመቀኛኘት ፡ መንፈስ ፡ አደረባቸው ። አንዱ ፡ አንዱን ፡ ብገድለው ፡ ሀብቱ ፡ ለኔ ፡ ይሆን ፡ የለምን ፡ ብሎ ፡ አሰበ ። ሁለተኛውም ፡ እንደዚሁ ፡ ያለ ፡ ሐሳብ ፡ አደረበት ። በዚህ ፡ ተንኰል ፡ እየተሳሰቡ ፡ አብረው ፡ ሲጓዙ ፡ ሳለ ፡ ከብት ፡ ጥለን ፡ እንብላ ፡ እንጂ ፡ በረኃብ ፡ እናልቃለን ፡ ተባብለው ፡ አንድ ፡ መሲና ፡ አረዱ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አንዳችን ፡ ላሟን ፡ ስንገፍ ፡ አንዳችን ፡ እገበያ ፡ ሄደን ፡ እንጀራ ፡ እንግዛ ፡ ያለንጀራ ፡ ምን ፡ እናደርገዋለን ፡ ተባብለው ፡ ከሁለቱ ፡ አንደኛው ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ሄደ ። እገበያም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ውሻ ፡ በቍልቍለት ፡ የማትጎትተው ፡ እንጀራና ፡ ሽልጦ ፡ አገኘና ፡ ገዝቶ ፡ ለራሱ ፡ እበቃው ፡ ድረስ ፡ በላና ፡ በባልንጀራው ፡ ድርሻ ፡ ላይ ፡ መርዝ ፡ ጨመረና ፡ ፈትፍቶ ፡ እየተቻኰለ ፡ እሱ ፡ ሲሞትልኝ ፡ ከብቶቹን ፡ እኔ ፡ እወስዳለሁ ፡ በማለት ፡ በሩጫ ፡ ተመለሰ ። ጓደኛውም ፡ እንደሱው ፡ ሲመጣ ፡ ገድዬ ፡ ከብቶቹን ፡ በሙሉ ፡ እወስዳለሁ ፡ ሲል ፡ በልቡ ፡ ተንኰል ፡ አስቦ ፡ ኖሮ ፡ ላሟን ፡ ገፎ ፡ ሥጋዋን ፡ ዕንጨት ፡ ላይ ፡ ሰቅሎ ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ ከመንገዱ ፡ ላይ ፡ ሲጠባበቀው ፡ ቈየ ፡ እንጀራ ፡ ያመጣውን ፡ ጓደኛውን ፡ ገና ፡ አጠገቡ ፡ ሳይደርስ ፡ በሩቁ ፡ ለምንድነው ፡ እስካሁን ፡ የቈየኸው ፡ ብሎ ፡ ተቈጣው ፡ ያም ፡ መንገዱ ፡ ሩቅ ፡ ስለ ፡ ሆነብኝ ፡ ነውና ፡ አትቈጣኝ ፡ ቢለውም ፡ ሰበብ ፡ ፈልጓልና ፡ ቃሉን ፡ አጕልቶ ፡ አክሮ ፡ ከተሳደበ ፡ በኋላ ፡ በያዘው ፡ ጐራዴ ፡ አንገቱን ፡ ቀልቶ ፡ ጣለው ። ቀጥሎም ፡ ያመጣለትን ፡ እንጀራና ፡ ሽልጦ ፡ ወስዶ ፡ በላ ። ነገር ፡ ግን ፡ መርዝ ፡ ነበረበትና ፡ እፍታም ፡ ሳይቈይ ፡ ወዲያው ፡ ድብን ፡ አለ ። ሁለቱም ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ በተንኰል ፡ በምቀኝነት ፡ ባልደከሙበት ፡ ባለፉበት ፡ በሰው ፡ ከብት ፡ ያረዱትን ፡ እንኳ ፡ ሳይበሉለት ፡ ተላለቁ ።

አዝማሪ ፡ የሆነው ፡ ባልደረባቸው ፡ እረ ፡ ዛሬ ፡ ዕዳ ፡ ከሜዳ ፡ ሲለኝ ፡ አደራ ፡ አለና ፡ ለሚስቱ ፡ አጫወታት ። እሷም ፡ አይ ፡ ቅዠት ፡ ነው ፡ አለችው ። እሱ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ያየሁት ፡ ሕልም ፡ ዕለቱን ፡ ነው ፡ የሚደርሰው ፡ አላት ። እንግዲያስ ፡ ከቤትህ ፡ ተጠንቀቀህ ፡ ዋል ፡ ብትለው ፡ እኔ ፡ የዛሬን ፡ ቀን ፡ የማሳልፈው ፡ በጫካ ፡ ነውና ፡ ይልቅስ ፡ ምሳዬን ፡ ቶሎ ፡ ስጪኝ ፡ ልሂድ ፡ አላት ። እንደ ፡ በላም ፡ ተነሥቶ ፡ ከዱር ፡ ገባና ፡ ጥቂት ፡ ጥሻ ፡ ለጥሻ ፡ ሲሹለከለክ ፡ ቈይቶ ፡ ላሞቹ ፡ አሉበት ፡ ሥጋው ፡ ታርዶ ፡ ከተሰቀለበት ፡ ዛፍ ፡ አቅራቢያ ፡ ቍጭ ፡ አለ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በድንገት ፡

የከብቶቹ ፡ ባለቤቶች ፡ ደረሱና ፡ ቀና ፡ ቢሉ ፡ ሥጋ ፡ ተሰቅሎ ፡ ወደ ፡ ጫካው ፡ ቢመለከቱ ፡ ያ ፡ ያስቀጣቸው ፡ ሰው ፡ ተደብቆ ፡ አገኙ ።

እሱ ፡ ግን ፡ ከብቶቹ ፡ የማን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ አላወቀም ፤ ሥጋውንም ፡ አላየም ፡ ነበር ። እነኛ ፡ ባለከብቶቹ ፡ ግን ፡ ኡኡታቸውን ፡ አቀለጡት ። አገር ፡ ተሰብስቦ ፡ ምን ፡ ሆናችሁ ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቃቸው ፡ ይኸ ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ከብቶቻችን ፡ በጠፉብን ፡ ሰዓት ፡ እኛ ፡ ቤት ፡ መጥቶ ፡ ነበረ ፤ ኡኡ ፡ ብለን ፡ አገር ፡ እንዳይረዳን ፡ አትጩኹ ፡ እኔ ፡ እፈልግላችኋለሁ ፤ በተገኙም ፡ ጊዜ ፡ ተገኙ ፡ ብዬ ፡ እጠራችኋለሁ ፡ ብሎን ፡ ስንፈልግ ፡ እልፍ ፡ አለና ፡ እረ ፡ ተገኙ ፡ ብሎ ፡ ጠራን ፤ እኛም ፡ ደስ ፡ ብሎን ፡ አጠገቡ ፡ ደርሰን ፤ ብንጠይቀው ፡ አላገኘሁም ፡ አለን ። ይኸንንም ፡ በመናገሩ ፡ ከሰን ፡ እዳኛ ፡ ብናቀርበው ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ክዶ ፡ አስቀጥቶን ፡ ነበር ፤ አሁን ፡ ግን ፡ እከብቶቻችን ፡ አጠገብ ፡ ተቀምጦ ፡ አንዷን ፡ ላም ፡ አርዶ ፡ ሥጋውን ፡ ሰቅሎ ፡ አገኘነው ። ስለዚህ ፡ ሐሰት ፡ ያለው ፡ እውነት ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷልና ፡ አይቀጡ ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣልናል ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ። ሕዝቡም ፡ ይህነን ፡ ጉዳይ ፡ የሚፈታው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ዳኛ ፡ ሂዱ ፡ ብሎ ፡ አቈራኝቶ ፡ ላካቸው ።

ዳኛው ፡ ከሥር ፡ ገምሮ ፡ የነገሩን ፡ አመጣጥ ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ በሌባው ፡ ላይ ፡ የብዙ ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ ፈረደበት ። ባለቤቶቹም ፡ ከብቶቻቸውን ፡ ይዘው ፡ በታረደችውም ፡ ላሚቱ ፡ ዋጋ ፡ ተቀብለው ፡ በደ



የከብቶቹ ፡ ባለቤቶች ፡ ደረሱና ፡ ቀና ፡ ቢሉ ፡ ሥጋ ፡ ተሰቅሎ ፡ ወደ ፡ ጫካ ፡ ቢመለከቱ ፡ ያ ፡ ያስቀጣቸው ፡ ሰው ተደብቆ ፡ አገኙት ።

ኅና ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ተመልሰው ገቡ ። አታላዩ ፡ ሌባ ፡ ግን ፡ በእስር ፡ ቤት ፡ ሳለ ፡ ታሞ ፡ ሞተ ፡ ይባላል ፡



፨ አታላይ ፡ ሌላውን ፡ ያታለለ ፡ ይመስለዋል ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ የሚጐዳው ፡ እሱው ፡ ራሱ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፤ የተንኰሉን ፡ ሥራ ፡ የወጠነው ፡ ተገኙ ፡ የተባለው ፡ የግብር ፡ አበሮቹን ፡ ሁሉ ፡ ዕዳ ፡ ከፋይ ፡ ሆነ ።

ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ተንኰለኛንና ፡ አታላይን ፡ ጓደኛ ፡ አለማድረግ ፡ ይጠቅማል ።

---

## ሌቶች ፡ ሹመት ፡ እንደ ፡ ለመኑ ።

ሌቶች ፡ ተሰብስበው ፡ መሳፍንት ፡ መኳንንትና ፡ አገረ ፡ ገዢዎችም ፡ ሁሉ ፡ ባሉበት ፡ እኛስ ፡ ብንሆን ፡ ሰዎች ፡ አይደለንም ፡ ምነው ፡ አገር ፡ ግዛት ፡ ሹመት ፡ አሰይጠን ፡ ሲሉ ፡ አመለከቱ ። የተሰበሰቡት ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ስለ ፡ ተጨነቁ ፡ ምክር ፡ አደረጉ ። ብንሾማቸው ፡ ሥርዐትና ፡ ፍርድ ፡ አያውቁ ፡ አይሆንም ፡ ብንላቸው ፡ በየቤታችን ፡ ይበድሉናል ፡ የሚል ፡ ክርክር ፡ ተነሣ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወፍ ፡ እንያዝና ፡ በገልግል ፡ ቈልፈን ፡ ከንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ እንላካቸው ፤ ያደረሱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይሾሙ ፡ ካላደረሱ ፡ ግን ፡ ይቅርባቸው ፡ ብለው ፡ ወሰኑ ። ለንጉሡም ፡ ይህንኑ ፡ ሐሳብ ፡ ገለጹለት ። ወዲያው ፡ ይዘው ፡ በገልግል ፡ ከተው ፡ ይህንን ፡ ዕቃ ፡ ለንጉሡ ፡ አድርሱ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ምስጢር ፡ ነውና ፡ ከፍታችሁ ፡ እንዳታዩት ፡ ብለው ፡ አስጠንቅቀው ፡ ላኳቸው ።

እነሱም ፡ የተሰጣቸውን ፡ ዕቃ ፡ ይዘው ፡ ሲሄዱ ፡ ሳለ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ በውስጡ ፡ ያለው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማወቅ ፡ ጓጉ ። በመካከላቸው ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ አይሆንም ፡ ባይ ፡ ጠፍቶ ፡ ባደራ ፡ የተቀበሉትን ፡ አገልግል ፡ ከፈቱት ። ያችም ፡ ወፍ ፡ ቱር ፡ ብላ ፡ ወጥታ ፡ አመለጠች ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የሚያደርጉትን ፡ አጥተው ፡ በጣም ፡ ተቸገሩ ፤ በመጨረሻው ፡ በወፏ ፡ ምትክ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ጨምረው ፡ ቈልፈው ፡ አገልግሉን ፡ ወስደው ፡ ለንጉሡ ፡ አቀረቡለት ። ንጉሡም ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ አስቀድሞ ፡ ከመሳፍንቱ ፡ ከመኳንንቱ ፡ ከገረ ፡ ገዢዎቹና ፡ ከሹማምቶቹ ፡ ጋራ ፡ የተነጋገረበት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ ላኩልኝ ፡ ያልኳቸው ፡ ይህ ፡ አይደለም ፡ ወፍ ፡ እንጂ ፡ ወዴት ፡ አለች ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ ነገሩን ፡ እንዳወቀባቸው ፡ ተረድተው ፡ እውነቱን ፡ አውጥተው ፡ በመንገድ ፡ የሠሩትን ፡ ሥራ ፡ ገልጠው ፡ ነገሩት ። ንጉሡም ፡

እንግዲያውማ ፡ በዚህ ፡ በትንሹ ፡ ነገር ፡ ያልተጠነቀቃችሁና ፡ ምስጢር ፡ የገለጻችሁ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ኀላፊነት ፡ እንዴት ፡ ሊጣልባችሁ ፡ ይቻላል ፡ ብሎ ፡ የጠየቁትን ፡ ሹመት ፡ ከለከላቸው ፡ ይባላል ።



እትዬ ፡ እትዬ ፡ ተባብሉና ፡ አገልግሉን ፡ ከፈት ፡ ቢያደርጉት ፡ ያቺ ፡ ወፍ ፡ ቱር ብላ ፡ ወጣች ።

፨ ከሴቶች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከወንዶችም ፡ ውስጥ ፡ አንዳንዶች ፡ ምስጢር ፡ የማይችሉ ፡ ይገኛሉ ፡ ስለዚህ ፡ ሴት ፡ ወንድ ፡ ሳንል ፡ ምስጢር ፡ አለመቻል ፡ በደል ፡ መሆኑን ፡ መገንዘብ ፡ ይገባናል ።

## በነውር ፡ የተሰደዱ ፡ ሦስት ፡ ጓደኞች ።

አንደኛው ፡ በብዙ ፡ የሚበላ ፡ ሆዳም ፡ ሁለተኛው ፡ ሌባ ፡ ሦስተኛው ፡ ሰባቂ ፡ የሆኑ ፡ ከተወለዱበት ፡ አገር ፡ ለጌታ ፡ አዳር ፡ ሄደው ፡ ትልቅ ፡ ቤት ፡ ብዙ ፡ ከብት ፡ ባዩ ፡ ቍጥር ፡ ባለቤቶቹን ፡ በሎሌነት ፡ ቅጠሩን ፡ ብለው ፡ ይለምኑ ፡ ጀመር ። ምን ፡ ምን ፡ ሥራ ፡ ታውቃላችሁ ፡ ጠባያችሁስ ፡ ምንድነው ፡ ቢሏቸው ፡ ሞያችን ፡ እርሻ ፡ ማረስ ፡ የጕልበት ፡ ሥራ ፡ ማናቸውንም ፡ መሥራት ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ ማስተዳደር ፡ ነው ፡ ጠባያችን ፡ ግን ፡ አንደኛው ፡ በብዙ ፡ የሚበላ ፡ ሆዳም ፡ ሁለተኛው ፡ ሌባ ፡ ሦስተኛው ፡ ሰባቂ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ያለባቸውን ፡ ነውር ፡ ከመናገር ፡ አልሸሸጉም ። እንዲህም ፡ በማለት ፡ ለብዙዎች ፡ ጌቶች ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ቢያስታውቁ ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ነውር ፡ አለብን ፡ እያላችሁ ፡ ማን ፡ ይቀጥራችኋል ፡ አንፈልግም ፡ እያሉ ፡ ከመለሷቸው ፡ በኋላ ፡




አንድ ፡ ንብረቱ ፡ የበዛ ፡ ቤቱ ፡ የሰፋ ፡ ያስተዳደር ፡ ዐቅድ ፡ ዐዋቂ ፡ ነኝ ፡ ባይ ፡ ጌታ ፡ እኔ ፡ አሳድራችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ ተቀብሎ ፡ ብዙ ፡ የሚበላውን ፡ ሆዳም ፡ አዛዥ ፡ ሌባውን ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ሰባቂውን ፡ የልፍኝ ፡ አሽከር ፡ አድርጎ ፡ ቀጠራቸው ። ይህንንም ፡ ማድረጉ ፡ ሆዳሙ ፡ አዛዥ ፡ ሲሆን ፡ እንጀራው ፡ ሥጋው ፡ ጠጁ ፡ ጠላው ፡ ማናቸውም ፡ የምግብ ፡ ድርጅት ፡ በሱ ፡ ኀላፊነት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የሚሠራው ፡ ዐይኑ ፡ ይጠግብና ፡ ከሥሥት ፡ ይድናል ፡ ምናልባትም ፡ ልቡ ፡ ቢጓጓ ፡ አንሥቼ ፡ ልብላ ፡ ቢል ፡ እንዲቀርብ ፡ በተጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ ከዝግጅቱ ፡ ጐድሎ ፡ ቢገኝ ፡ እነወራለሁ ፡ እቀጣለሁ ፡ ሲል ፡ ከምግቡ ፡ ሆዱን ፡ ይቈጥባል ። ሌባውም ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በመዝገብ ፡ ከተረከበው ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ ገንዘብ ፡ ቢጐድልበት ፡ በኀላፊነት ፡ ተረክቧልና ፡ እቀጣለሁ ፡ እዋረዳለሁ ፡ በማለት ፡ በምነቱ ፡ ጠንክሮ ፡ ይጠብቃል ። ሰባቂውም ፡ ባለሟል ፡ ሲሆን ፡ ያለሱ ፡ እልፍኝ ፡ ገቢ ፡ ምሥጢር ፡ ሰሚ ፡ የለምና ፡ ምሥጢሩ ፡ እውጭ ፡ ወጥቶ ፡ ሰው ፡ ሰምቶት ፡ ቢገኝ ፡ እቀጣለሁ ፡ ብሎ ፡ አፉን ፡ ጠብቆ ፡ ይኖራል ፡ በማለት ፡ ነው ።

እንደ ፡ ተባለውም ፡ ሆዳሙና ፡ ሌባው ፡ በተሰጣቸው ፡ ሥራ ፡ እምነታቸውን ፡ ጠብቀው ፡ አደራቸውን ፡ አጥብቀው ፡ ማገልገል ፡ ያዙ ።

በተቀጠሩ ፡ በወሩ ፡ ጌታቸው ፡ እርሻ ፡ ሊያሳርሱ ፡ እመቤታቸው ፡ ደግሞ ፡ ፈትል ፡ ሊያስፈትሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ድግስ ፡ ይሰናዳ ፡ ጀመር ። በመጨረሻው ፡ ሥራው ፡ ለነገ ፡ ሊሆን ፡ ሌሊቱን ፡ የሠንጋ ፡ ቍርበታቸውን ፡ አንጥፈው ፡ ተኝተው ፡ እንቅልፍ ፡ ወስዷቸው ፡ ሳለ ፡ ያ ፡ ሰባቂ ፡ አሽከር ፡ ሙቅ ፡ ውሃ ፡ በመቤቱና ፡ በጌታው ፡ መከከል ፡ ዝግ ፡ ብሎ ፡ ቡልኳቸውን ፡ ገለጥ ፡ አድርጎ ፡ አፈሰሰ ። እነሱም ፡ በነቁ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ የሠንጋው ፡ ቍርበት ፡ ለመምጠጥ ፡ ባለመቻሉ ፡ ውሃው ፡ ከሁለቱ ፡ መከከል ፡ አቍሮ ፡ ሞቃቸው ። እመቤቲቱ ፡ እሳቸው ፡ ናቸው ፡ የሸኑት ፡ ጌትዮውም ፡ እሷ ፡ ናት ፡ የሸነችው ፡ በማለት ፡ ተማምተው ፡ ሳይነጋገሩ ፡ ሴቲቱ ፡ ተነሥተው ፡ ቍርበቱን ፡ ገልብጠው ፡ በጨርቅ ፡ አድርቀው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ተመልሰው ፡ ተኙ ። ከነጋም ፡ ወዲህ ፡ ሥራቸውን ፡ በማሰብ ፡ ወንዱ ፡ በማለዳ ፡ ወደ ፡ እርሻቸው ፡ ሲሰማሩ ፡ እመቤትዮዋም ፡ ደግሞ ፡ የቤት ፡ ሥራቸውን ፡ ለማከናወን ፡ ተዘጋጁ ። ቀኑ ፡ ጠም ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ባልዮው ፡ ጥላቸውን ፡ በጫማቸው ፡ ሰፍረው ፡ ሰዓቱን ፡ ካወቁ ፡ በኋላ ፡ አሽከራቸውን ፡ ሂደህ ፡ ምሳ ፡ እንዲመጣ ፡ አድርግ ፡ ብለው ፡ ላኩት ። እሱም ፡ የፍጥነት ፡ ነገር ፡ መቼም ፡ ይሆንለታልና ፡ ሲሮጥ ፡ ሂዶ ፡ እመቤቱ ፡ ከተወለድኩ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡ አጋጥሞኝ ፡ አያውቅም ፡ ገርሮ ፡

ሁሉን ፡ ይሰማል ፡ ዛሬ ፡ ጕድ ፡ ሰምቼ ፡ መጣሁ ፡ አላቸው ። ሴቲቱም
ምንድነው ፡ ልጄ ፡ በማለት ፡ ጠየቁት ። ጌቶች ፡ የርስዎን ፡ ስም ፡ ሲ
ጠፉ ፡ ዋሏ ።



በመቤቱና ፡ በጌታው ፡ መካ
ከል ፡ ዝግ ፡ ብሎ ፡ ብልኳቸው
ን ፡ ገለጥ ፡ አድርጎ ፡ አፈሰሰ ።

ምን ፡ ምን ፡ እያሉ ፤

ሽንቷን ፡ ሸንችብኝ ፡ እያሉ ፡ ነዋ ፤ ዛሬ ፡ በደበው ፡ ላይ ፡ ከዚህ
ሌላ ፡ ምንም ፡ አይጫወቱ ፡ ብሎ ፡ አክብዶ ፡ ነገራቸው ። ሴትዮዋም
ይኸንን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ተናደዱ ፡ አረሩ ፡ ከሰሉ ፡ ጨሱ ፤ እንዲያውም
አንቱ ፡ የሚሏቸውን ፡ ባላቸውን ፡ አንተ ፡ ብለው ፡ እሱ ፡ የሸነውን
በኔ ፡ ያመካኛል ፡ እያሉ ፡ በመናደድ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ሳሉ ፡ ምሳ ፡ ላኸ
ልን ፡ ብለው ፡ ነበረ ፡ አላቸው ። እረ ፡ የምን ፡ ምሳ ፡ ነው ፡ ደግሞ ፡ ብለው
በንዴት ፡ ቃል ፡ ተናገሩት ። አሽከርየውም ፡ ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ተመልሶ
ሄደ ። ጌታው ፡ ምሳውስ ፡ ብለው ፡ ቢጠይቁት ፡ እዩዩ ፡ የምን ፡ ምሳ
ነው ፡ ጌታዬ ፡ እሳቸው ፡ ለራሳቸው ፡ የርስዎን ፡ ስም ፡ እያብጠለጠሉ
ከሴቶቹ ፡ ጋራ ፡ መሣቅ ፡ ብቻ ፡ ሆኖልዎታል ። እኔ ፡ ስለ ፡ ርስዎ ፡ በን
ዴት ፡ ተቃጥዬ ፡ ልሞት ፡ ነበር ፡ አላቸው ።

—ምን ፡ እያሉ ፡ ነው ፡ እባክህ ፤

—ሽንታቸውን ፡ ከልጋ ፡ ላይ ፡ ሸኑ ፡ እያሉ ፡ ነዋ ፡ ጌታዬ ። ሰውየውም
ተናደው ፡ ሲገሠግሡ ፡ ሄደው ፡ እቤት ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ ለመዱብዱብ
የራስጌ ፡ ቈመጣቸው ፡ ይዘው ፡ ከመኝታ ፡ ቤት ፡ ከሰገነት ፡ ውስጥ ፡ ገ
ተው ፡ ሚስታቸውን ፡ ቢጠሯቸው ፡ በነገሩ ፡ አኰርፈው ፡ ከመ ፡ ጤፍ
ሳይቈጥሯቸው ፡ ችላ ፡ አሏቸውና ፡ ቈዩ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባለቤትየው
ሽጕጣቸውን ፡ አጕርሠው ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ ሚስታቸውን ፡ ደረታቸውን
ብለው ፡ ገለበጧቸው ።




አሽከሩም ፡ ገና ፡ ጌትየው ፡ ሲገቡ ፡ አይቶ ፡ እየሮጠ ፡ ሄዶ ፡ ለሴት
የዋ ፡ ዘመዶችና ፡ ወገኖች ፡ እረ ፡ እናንተ ፡ ለመሆኑ ፡ ምን ፡ ዓለመኞች ፡
ናችሁ ፡ አለና ፡ በብስጭት ፡ ተናገራቸው ። ምነው ፡ አሉት ።

—እመቤቴን ፡ ጌቶች ፡ ገደሏቸው ።

—ለምን ፡ በምን ፡ የተነሣ ።

—ለድግሱ ፡ ጠላ ፡ አልተሸከምሽም ፡ ብለው ፡ ነዋ ፤ እኛ ፡ እያለን ፡
አሳቸው ፡ ለዚህ ፡ መታሰባቸው ፡ አይገርምም ። ታዲያ ፡ አሁን ፡ ስትመጣ ፡
ነፍሷ ፡ ወጥቷልን ።

ጌታው ፡ በቀጥታ ፡ መሄዳቸውን ፡ እንጂ ፡ እመቤቲቱ ፡ መገደላቸውን ፡
አላወቅም ፡ ነበረና ፡ እኔ ፡ ስመጣ ፡ ግን ፡ ያጣጥሩ ፡ ነበር ፡ አላቸው ። ሰዎ
ቹም ፡ ቶሎ ፡ ብለው ፡ የጦር ፡ መሣሪያቸውን ፡ አዘጋጅተው ፡ ሲነሡ ፡ አየና ፡
ቀድሞ ፡ ሲሮጥ ፡ ሄዶ ፡ ላሳዳሪው ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ እንግዲህ ፡ መሰደዳችን ፡
አልቀረም ፡ ስለዚህ ፡ ይህንን ፡ የተደገሰውን ፡ ድግስ ፡ የርስዎን ፡ ዘመዶ
ችና ፡ ወገኖች ፡ ዝርያዎችንም ፡ ሰብስበን ፡ ተካፍለነው ፡ ብንሄድ ፡ አይሻ
ልም ፡ ብሎ ፡ አማከራቸው ። ጌትየውም ፡ አዎ ፡ እውነትህ ፡ ነው ፤ በል ፡
ግራዝማች ፡ አብጤንና ፡ አቶ ፡ ሽሽጉን ፡ ከነጭፍሮቻቸው ፡ ጥራ ፡ አሉት ።




በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባለቤትየው ፡
ሽጕጣቸውን ፡ አጕርሠው ፡
እንደ ፡ ደረሱ ፡ ሚስታቸውን ፡
ደረታቸውን ፡ ብለው ፡ ገለበ
ጧቸው ።

እሱም ፡ ሮጦ ፡ ከተባሉት ፡ ሰዎች ፡ ቤት ፡ ሲቃ ፡ እንደ ፡ ያዘው ፡ ጥልቅ ፡
አለ ። አቶ ፡ ሽሽጉም ፡ ደነገጡና ፡ ምነው ፡ ምን ፡ ሆንክ ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ።

—የመቤቱ ፡ ወገኖችና ፡ ዘመዶች ፡ ጌቶችን ፡ ገደሏቸው ።

—ነፍሳቸው ፡ ወጥቷል ።

እኔ ፡ ወደዚህ ፡ ነፍሴን ፡ አጥቼ ፡ ስሮጥ ፡ መቼም ፡ ውጪ ፡ ነፍስ ፡ ግቢ ፡ ነፍስ ፡ ሆኖ ፡ እያጣጣሩ ፡ ተኝተው ፡ ይታኰሱ ፡ ነበር ፡ አላቸው ። አቶ ፡ ሽሽጉም ፡ ግራዝማች ፡ አብጤን ፡ አስጠርተው ፡ በነፍሳቸው ፡ እን ድረስ ፡ ብለው ፡ የጦር ፡ መሣሪያቸውን ፡ ይዘው ፡ ሰናፈላቸውን ፡ ባጭር ፡ ታጥቀው ፡ በፍጥነት ፡ እየገሠገሡ ፡ ሄደው ፡ የሴትዮዋ ፡ ዘመዶች ፡ ሰውዮ ውን ፡ ገድለው ፡ የጎታቸውን ፡ ሬሳ ፡ ለመውሰድ ፡ ሲያገላብጡ ፡ ደረሱባ ቸው ። ምነው ፡ ደግሞ ፡ እናንተም ፡ መጣችሁ ፡ አለና ፡ አንዱ ፡ ተኩሰባቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሁሉም ፡ ባለመሣሪያ ፡ ነበሩና ፡ ተጣመዱ ። ከወን ድዮው ፡ ወገን ፡ ኀምሳ ፡ ከሴትዮዋ ፡ ሠላሳ ፡ በድምሩ ፡ ከነባለቤቶቹ ፡ ሰማኒያ ፡ ሁለት ፡ አጫረሰና ፡ የጌታውን ፡ ቤት ፡ ይዞ ፡ ተቀመጠ ።


ምነው ፡ ደግሞ ፡ እናንተም ፡ መጣችሁ ፡ አለና ፡ አንዱ ፡ ተኩሰባቸው ።

ጌታው ፡ ሚካኤልን ፡ ማኅበር ፡ ይጠጡ ፡ ነበርና ፡ ጥዋው ፡ ለሱ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የጌታውን ፡ ዕጣ ፡ ለመክፈል ፡ ጠላውን ፡ አስጠምቆ ፡ ማናቸውንም ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ከዘጋጀ ፡ በኋላ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ የሚያስወጣ ፡ መንገድ ፡ በሠረገላ ፡ ቈፍሮ ፡ ሲጠባበቅ ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ ሠላሳ ፡ ሆነው ፡ መጡ ። እነሱም ፡ በባልንጀራቸውና ፡ በወንድማቸው ፡ መሞት ፡ ተናደው ፡ ኖሮ ፡ ያንን ፡ ክፉ ፡ አሽከር ፡ ለመግደል ፡ ዘግተው ፡ ቤቱን ፡ እሳት ፡ ለኰሱበት ። ጊዜው ፡ ነፋስ ፡ ነበርና ፡ ቃጠሎውን ፡ ስላፋ ጠነው ፡ ቤቱ ፡ በቶሎ ፡ አመድ ፡ ሆነ ። ይህ ፡ አሽከር ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ባዘጋጀው ፡ መሿለኪያ ፡ ውስጥ ፡ በድብቅ ፡ ቈይቶ ፡ ነበርና ፡ ቤቱ ፡ ተቃጥሎ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ምንም ፡ ሳይነካው ፡ ከመዱ ፡ መካከል ፡ በደኅና ፡ ብቅ ፡ አለ ።



እነዚህም ፡ ማኅበረተኞች ፡ አይተው ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዳንክ ፡ ቤት ፡ ዘግ ተን ፡ እሳት ፡ ለቀንብህ ፡ አልነበረምን ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ። እሱም ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ለወደደው ፡ ከእሳት ፡ ያወጣል ፡ ከነደደው ፤ ማኅበሩንስ ፡ መጠጣታችን ፡ ስንኳን ፡ ከዚህ ፡ ከምድሩ ፡ እሳት ፡ ይቅርና ፡ ከሰማዩ ፡ ለመዳን ፡ አይደለምን ፡ ይኸው ፡ ሚካኤልን ፡ በማመኔና ፡ በማክበሬ ፡ ከእ ሳት ፡ አዳነኝ ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ ይህንን ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ ያጋደለውን ፡ ቀጣፊ ፡ ያዳነ ፡ እኛንማ ፡ በቅን ፡ ዘላለም ፡ ስንጠጣውና ፡ ስናከብረው ፡ የም ንኖረውን ፡ እንኳን ፡ ሊፈጀን ፡ ሞቅስ ፡ መቼ ፡ ይለናል ፡ ብለው ፡ በል ፡ እንግዲህ ፡ ይህንን ፡ ቤት ፡ ዝጋብንና ፡ እሳት ፡ ልቀቅበት ፡ ብለው ፡ ሠላሳ ውም ፡ ማኅበረተኞች ፡ ካንድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ተቃጥለው ፡ አለቁ ፡ ይባላል ።


በል ፡ እንግዲህ ፡ ይህንን ፡ ቤት ፡ ዝጋብንና ፡ እሳት ፡ ልቀቅበት ፡ ብለው ፡ ሠላሳ ውም ፡ ተቃጥለው ፡ አለቁ ።

እሱንም ፡ የጌታውን ፡ ሀብት ፡ ከያዘ ፡ በኋላ ፡ በነገር ፡ እየወጋ ፡ ከሚ ያናድዳቸው ፡ አንዱ ፡ ሳያስበው ፡ ድንገት ፡ በጥይት ፡ ገደለው ።

※ ይዋል ፡ ይደር ፡ እንጂ ፡ ሳይደክሙ ፡ በተንኰል ፡ የሰበሰቡት ፡ ሀብት ፡ በመጨረሻው ፡ ከኰዳት ፡ ላይ ፡ መጣሉ ፡ አይቀርምና ፡ ከእንደዚህ ፡ ያለ ፡ አድራጎት ፡ መራገድ ፡ ነው ።

ለሰባቂ ፡ ዡሮህን ፡ አትስጠው ፡ የተባለውንም ፡ ማሰብ ፡ ይገባል ።